የዳኞችና የአቃቤ ህጎች ባሙሽ
ስትም ባር

አዘጋጆች

መካሻ አበራ

ኡርጌሳ ገነሞ

ማውጫ

መግቢያ 4

ክፍል አንድ፣

ስለስነምግባርና የሙያ ስነምግባር በጠቅላላው

1.1. መግቢያ..5

1.2. የኤቲክስ ስነቃል አመጣጥና ትርጉም..6

1.3. አንድን ባህርይ ወይም ድርጊት ትክክል ወይም ስህተት ብሎ ለመፈረጅ መለኪያው ምንድነው?...8

1.4. የሙያ ስነምግባር ምንድነው?.. 12

1.5. የዳኞችና የአቃቤ ህግ የሙያ ሥነምግባር አስፈላጊነት........................... 14

ክፍል ሁለት

የዳኝነት/ዓቃብያነ ሕግ የሙያ ሥነምግባር በጠቅላላው

2.1. መግቢያ 18

2.1.1. የዳኞችና የዓቃብያነ ሕግን የሙያ ሥነምግባርን ለማዘጋጀት በአለምአቀፍ ደረጃ ያለተሞክሮ፡-.. 20

2.1.2. በአገራችን ኢትዮጵያ የዳኞችና የአቃቤ ህጎችን የሙያ ስነምግባር ለማዘጋጀት የተሰሩ ስራዎች.. 26

2.2. የዳኞች የሙያ ሥነምግባር መርሆዎች...29

2.2.1. የፍ/ቤትን ነጻነት መሻትና ማረጋገጥን በተመለከተ(Independence)...... 29

2.2.2. በአድሎአዊነት ያለመስራት(Impartiality) 45

2.2.3. የፍርድ ስራን በሀቀኝነት ስለማከናወን (Integrity)..................................53

2.2.4. ቅንነት (PROPRIETY)............ 57

2.2.5. የባለጉዳዮችን መብት በእኩልነት ስለመጠበቅ (Equality).......................63

2.2.6. በዳኝነት ስራ ትጋትና ጥረት ማሳየት (due deligence)...........................67

2.3. የአቃቤ ህግ የስነምግባር መርሆዎች... 77

2.3.1. መልካም ሙያዊ ተግባር...77

2.3.2. *የሙያ ነጻነት*...*79*
2.3.3. የዐቃቤ ህግነት ስራን ያለ አድሎአዊነት ማከናወን...................................80
2.3.4. ዐቃቢያነ ህጎች በወንጀል የፍርድ ሂደት ሊኖራቸው የሚገባ ሚና.............82
2.3.5. ከሌሎች የፍትህ አካላት ጋር በቀና የትብብር መንፈስ ተቀናጅቶ
ስለመስራት..85
2.3.6. ስልጣንና ተሰሚነት..86
2.3.7. አቃቤ ህጎች አጠቃላይ በግል ኑሮአቸው ሊያከብሩት የሚገባ ስነምግባር......87

ክፍል ሶስት

ስለጠበቆችና የህግ አስከባሪዎች የስነምግባር ደንቦች አንዳንድ ነጥቦች

3.1. የጠበቆች የሙያ ስነ ምግባር መርሆዎች..89
3.2. የሕግ አስከባሪ አካላት የስነምግባር መመሪያዎችን በተመለከተ
ያሉ ዓለምአቀፍ መርሆዎች..95
ዋቢ ጽሁፎች...102
አባሪዎች 103

መግቢያ

ሰልጣኞች በማሰልጠኛ ማእከሉ የሚሰጠውን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኂላ የፍትህ ዘርፉን ትቀላቀላላችሁ፡፡ አንዳንዶቻችሁ ዳኞች ስትሆኑ አንዳንዶቻችሁ ደግሞ አቃቤ ህግ ትሆናላችሁ፡፡ በዚያን ወቅት ከአንድ ዳኛ ወይም አቃቤ ህግ የሚጠበቀውን የስነምግባር ደረጃ አውቃችሁ መገኘት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ የትምህርት ክፍል ስለዳኞችና አቃቤ ህጎች ሙያዊ የስነምግባር መርሆዎች እንማራለን፡፡

ይህ የማስተማሪያ ሰነድ በሶስት ክፍል ተከፍሎ ቀርቧል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል ስለስነምግባርና ስለሙያ ስነምግባር ጽንሰሀሳብ በጥቅሉ የቀረበበት ሲሆን ክፍል ሁለት ዋናው የዚህ ማስተማሪያ ሰነድ ክፍል ሲሆን ዳኞችና አቃቤ ህጎች ሊያከብሯቸው ስለሚገቡ የስነምግባር መርሆዎች በዝርዝር ቀርቧል፡፡ በክፍል ሶስት ከጠበቆችና ከህግ አስከባሪዎች ስለሚጠበቁ የስነምግባር ደረጃዎች በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በዚህ የስልጠና ሰነድ የተካተቱትን ትምህርቶች ለማብላላትና ለመረዳት እንዲቻል በርካታ የመወያያ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ሰልጣኖች በእነዚህ የመወያያ ጥያቄዎች ላይ በጥልቀትና በስፋት እንድትወያዩበት ይጠበቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰልጣኞች በምትገኙበት ክልል የጸደቁ የስነምግባር ደንቦች ከአሉ በትምህርት ጊዜው እነዚህን የስነምግባር ደንቦች በዚህ ማስተማሪያ ሰነድ ከቀረቡት ሀሳቦች ጋር በማነጻጸር ውይይት እንደምታደርጉበት ይጠበቃል፡፡

ክፍል አንድ
ስለስነምግባር ባሙያ ስነምግባር በንቅላላው

ዝርዝር አላማዎች

ሰልጣኞች ይህንን ክፍል ሲያጠናቅቁ ፣

1. ስነምግባር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡
2. ስነምግባራዊ ወይም ትክክለኛ ነው ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ባህርይ ነው ለማለት ለማለት መለኪያ መስፈርቶችን ያስረዳሉ፡፡
3. ሙያ ማለት ምን እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡
4. የሙያ ስነምግባር ምን ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡
5. ዳኞችና አቃቤ ህጎች የሙያ ስነምግባር የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

1.1. መግቢያ

ሁላችንም እንደምናውቀው የሰው ህሊና እውነትን ፍለጋ ሁልጊዜም እንደወጣና እንደወረደ ነው፡፡ ቀድሞ ይታመንበት የነበረውን ሁሉ ከመቀበላችን በፊት እስቲ እንመርምረው ይህ እኮ እውነት ላይሆን ይችላል በሚል መንገድ ጥያቄ የምናነሳ ጥቂት አይደለንም፡፡ ከምንሰማው ሁሉ እውነተኛው የትኛው ይሆን? በማለት ከጥርጣሬ ማእበል ውስጥ ገብተን ስንጨነቅ መገኘታችን እውቅ ነው፡፡

ሰዎች በቀን ተቀን ህይወታችን ምርጫችን የተለያየ ነው፡፡ አንዳንዱ ከረባት አድርጎ መገኘት ሲመርጥ ሌላው ደግሞ ቀለል ያለ ልብስ መልበስ ይመርጣል፡፡ አንዳንዶቻችን ቅመም የበዛበትን ምግብ ስንመርጥ አንዳንዶቻችን ደግሞ ምርጫችን አይሆንም፡፡ እንዲህ እያለ በፖለቲካ አመለካከት፣ በሀይማኖት፣ ወዘተ ዋጋ የምንሰጣቸው ነገሮች ይለያያሉ፡፡

የዚህ የልዩነታችን ምክንያት ምንድነው? አንዱ ዋጋ የሚሰጠውን ሌላው ዋጋ የማይሰጠው ለምንድነው? አንዳንዱ ፍትህን ለማስከበር መስዋእትነት ሲከፍል ሌላው ደግሞ ጉዳዩን በቸልተኝነት የሚያየው ለምንድነው? በመሰረቱ ለምንሰጠው ዋጋ ከዚህ በፊት ያሳለፍነው የህይወት ተሞክሮና ልምድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሰው ዋጋ የሚሰጠውና መልካምና ክፉ የሚለው ነገር የግድ ያስፈልገዋል ወይ? ብለው የሚጠይቁ አሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይህ ሰው ህሊና የለውም ሲባል እንሰማለን፡፡ እውነት አንዳንድ ጊዜ እንደሚባለው አንዳንድ ሰዎች ህሊና የላቸውም የሚባለው እውነት ነው?

History reveals that no society has ever been without some value system and every individual has some code of values. the issue, therefore, is not whether we are to have value but what those values will be-whether they will advance or retard life, whether they will be consistent or not.[1]

ይህ አባባል እውነት ነው፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ ምርጫ ያለው ስነምግባር ያስፈልጋል ወይም አያስፈልግም? የሚለው ላይ ሳይሆን ምን አይነት ስነምግባር ያስፈልገኛል? በሚለው ላይ ነው፡፡

እንግዲያስ የአንድ ተግባር ትክክለኛነቱና መጥፎነቱ የሚለየው በምንድነው? አንደኛውን ትክክል ሌላኛውን መጥፎ ብለን የምንጠራው በምን ምክንያት ነው? በህይወታችን ዋጋ ልንሰጠው የሚገባው ነገር ምንድነው? በሙያችን ዋጋ ልንሰጠው የሚገባው ነገር ምንድነው? አገራችንን ህዝባችንን በሚመለከት ዋጋ ልንሰጠው የሚገባና ልንተገብረው የሚገባው ነገር ምንድነው? እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ ጉዳዩን አጥንቶ አንድ መስመር ማስያዝ ይገባል፡፡ ኤቲክስ የሚባለውም ይህንን ጉዳይ የሚያጠና የፍልስፍና ዘርፍ ነው፡፡

1.2. <u>የኤቲክስ ስነቃል አመጣጥና ትርጉም</u>

ethics የእንግሊዝኛ ቃል ሲሆን የመጣውም ethos ከሚል የግሪክ ቃል ነው፡፡ በግሪክ ቋንቋ ethos ሰዎች በጋራ የሚኖሩበት ቦታ የሚል ትርጓሜ የነበረው ሲሆን ይህን ፍቺ በማስፋት ልምድ ጸባይ አነጋገር ባህርይ የአስተሳሰብና የአነጋገር ዘይቤ የሚሉ ትርጉሞችን እንደያዘ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

[1] Vincent Barry, philosophy a Text with Readings(2nd,1983),p.93

በጥንታዊቷ ሮም በላቲን ቋንቋ የግሪኩ ቃል የethos አቻ ቃል mos የተባለው የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም ከሞላ ጎደል ከ ethos ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በተጨማሪ ህግ ደንብ ያለባበስ ስርአት ወዘተ የሚሉ ትርጉሞችን ይይዛል፡፡ morality የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የተገኘውም ከዚሁ mos ከተባለው የላቲን ቃል ነው፡፡ ስለሆነም ሞራል እና ኤቲክስ ተመሳሳይ ሀሳብን ለመግለጽ በመቀያየር የምንጠቀማቸው ናቸው፡፡[2]

የኢንካርታ ኢንሳይክሎፒዲያ 2004 በእንግሊዝኛው አጠራር ኤቲክስን ሲተረጉም በግርድፉ ጠባይ፣ ልምድ፣ የሰው ልጅ ባህርይ የሚመራባቸው መርሆዎች ወይም እሴቶች ማለት ነው በማለት ይተረጉማል፡፡

የብላክስ ሎው ዲክሽነሪ ኤቲክስን እንደሚከተለው ይተረጉማል፡፡
"[o]f or relating to moral action, conduct, motive or character; ethical emotion; also treating of moral feelings, duties or conducts; containing precepts, duties or moral. professionally right befitting; conforming to professional standard of conduct.

ከላይ ያየናቸው ትርጉሞች ውስጥ ኤቲክስ የሰውን ተግባር ባህሪና ጠባይ ትክክልና ስህተት በማለት የሚገልጽ እንደሆነና ባህሪያችን/ ድርጊታችን መቼ ተቀባይነት እንደሚያገኝ ወይም እንደሚያጣ የሚያመለክት ስታንዳርድ ወይም የህጎች ስብስብ እንደሆነ የአንድን ግለሰብ ወይም የሙያ አባላትን ባህሪያት የሚገዙ መርሆዎች እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ ኤቲክስ ማለት ጥሩ እና መጥፎ በጎ እና እኩይ ሀሳብ ንግግርና ድርጊትን የሚገልጽ ስርአት ነው ብንል ከእውነት አንርቅም፡፡ አንድ ሀሳብ ወይም ድርጊት መልካም ወይም መጥፎ ትክክል ወይም ስህተት ዋጋ ያለው ወይም ዋጋ የሌለው ፍትሀዊ ወይም ኢፍትሀዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚጠቅም መለኪያ ነው፡፡

ይህ ኤቲክስ የተባለው ቃል በአማርኛ ስነምግባር ተብሎ ይታወቃል፡፡

---

[2] ዝኒ ከማሁ ገጽ 95

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ያዘጋጀው መዝገበ ቃላት ስነምግባርን መልካም ጸባይ ወይም አድራጎት፣ ከአንድ የሙያ መስክ ከባለሙያው የሚጠበቅ አድራጎት ወይም አሰራር በማለት ይተረጉመዋል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ኤቲክስን ስነምግባር በሚለው የአማርኛ ቃል ተክተን እንጠቀማለን፡፡

1.3. <u>አንድን ባህርይ ወይም ድርጊት ትክክል ወይም ስህተት ብሎ ለመፈረጅ መለኪያው ምንድነው</u>?

አንድን ነገር ትክክል ነው ወይም አይደለም ብለን የምንጠራው በምን ምክንያት ነው? ለሚለው ጥያቄ በዘርፉ ጥልቅ ምርምር ያደረጉ የተለያዩ ሊቃውንት ምላሽ ለመስጠት ቢሞክሩም አንድና ተመሳሳይ ምላሽ ላይ ግን አልደረሱም፡፡ ብዙዎቹ ሊቃውንት እንደሚስማሙት እነዚህ ሀሳቦች በሁለት ዋና ክፍሎች ተከፍለው ይቀርባሉ፡፡

በአንደኛው ክፍል የሚጠቃለሉት አንድ ስራ ደግ ወይም መጥፎ መሆኑ የሚታወቀው በውጤቱ ነው ሲሉ፣ በሁለተኛው ክፍል የሚጠቃለሉት ደግሞ ውጤቱ መታየት የለበትም የሚል ሀሳብ ያለቸው ናቸው፡፡[3]

በመጀመሪያው ክፍል ውስጥ ለሁለት የተከፈሉ ሀሳቦችን እናገኛለን፡፡

1. አንደኛው ሄዶኒዝም ሲሆን የቃሉም ቀጥተኛ ፍቺ ደስታ ማለት ነው፡፡ በዚህ አስተሳሰብ የሚፈጸመው ስራ ለፈጻሚው ደስታንና ምቾትን ማስገኘት አለበት በሚል ያስቀምጠዋል፡፡ አንድ ሰው ማንኛውንም ስራ በሚፈጽምበት ሰአት ለስራው አላማ ሊሆን የሚገባው አንድ ነገር ብቻ ከፊቱ እንዲደቀን ያስፈልጋል፡፡ እሱም ተደስቶ መኖር ነው፡፡ በአንዳንዶቹ አስተያየት ከፊታችን የምናገኛት ደስታ ቶሎ የምታልፍ ከሆነ እሷ ቀርታ ወደፊት የተሻለና ዘላቂ ደስታ የምታስገኝ ላይ ብናተኩር ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ እንዲሁም ከስጋዊ ደስታ ይልቅ መንፈሳዊ ደስታን መምረጥ የተሻለ ነው በማለት የሚገልጹም አሉ፡፡ እነዚህን ሁሉ አንድ

[3] ዝኒ ከማሁ ገጽ 98

የሚያደርገቸው ግን አንድ ሰው ማንኛውንም ስራ ሲፈጽም አላማው ማድረግ ያለበት የራሱን ደስታ ነው ማለታቸው ነው፡፡

2. ሁለተኛው ዩቲሊቴሪያኒዝም ሲሆን ማናቸውም ስራ ጥቅም የሚያስገኝና አንዳች አገልግሎትም የሚያበረክት ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም በአንድ ሰው ስራ ላይ ፍርድ ከመስጠታችን በፊት ከስራው የሚገኘውን ውጤት መመልከትና ጥቅምና ጉዳት እንዳለው አስቀድሞ ማመዛዘን ያሻል፡፡ ለምሳሌ ድሆችን መርዳት ርስ በርስም መዋደድና መከባበር ለማህበራዊ ኑሮ አስፈላጊዎች በመሆናቸው ጠቃሚ ናቸው ማለት ነው፡፡ የእዚህ ተቃዋሚ የሚሆነው ደግሞ የማህበረሰቡን ሰላምና ስምምነት የሚያደፈርስ ስለሚሆን መጥፎ ሊባል ይገባል፡፡ እንዲሁም አንድ ስራ ጥሩ ሊባል የሚችለው ጥቅም ሲኖረው ብቻ ሳይሆን በሚቻል አኳኋን አብዛኛውን ሰዎች የሚጠቅም ሲሆን ነው፡፡ ያለበለዚያ አንዱን ሰው ብቻ ጠቅሞ ሌላወን የሚጎዳ ከሆነ መልካም ስራ ሊባል አይችልም ይላሉ፡፡

በሁለተኛው ክፍል ውስጥም የተለያዩ ሀሳቦች አሉ፡፡

1. በአንድ በኩል ሞራል ማለት በተፈጥሮ ህግ የተመለከተ ሲሆን፣ ይህም ከሀይማኖት መጻህፍት ወይም መጻህፍት በምርምር የሚገኝ ነው፡፡ በዚህ አስተሳሰብ ሁልጊዜም የፈጣሪን ፈቃድ/ የተፈጥሮ ህግ የሚለንን ማድረግ አለብን የሚል ነው፡፡ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን ፈጣሪ ያዘዘውን ካደረግን ትክክል አደረግን ማለት ነው፡፡ ሰው እነዚህን ማክበር ያለበት የተፈጥሮ ህግ ስለሆነ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

2. ሁለተኛው ሀሳብ የሚለው ደግሞ የሚታየው የሰውየው ሀሳብና ለአንድ ተገቢ ለሆነ ስራ የሚያሳየው ሙሉ ፈቃደኝነት ወይም መልካም መንፈስ ብቻ እንጂ የስራው ውጤት ዋጋ የሌለውና ትርፍ የሆነ የውጭ ነገር ነው የሚል አስተያየትን የሚደግፍ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ በሽተኛ በጠና ታሞ ወደሆስፒታል ይሄዳል፡፡ ሀኪሙ ተጨንቆና ተጠቦ ሊያድነው ይሞክራል፡፡ ይሁንና ያንን ሁሉ ጥረት አድርጎ ላይሳካለት ይችላል፡፡ ሀኪሙ ውጤት አላገኘም ተብሎ ስራው

ላይመሰገን ነው? ይህ መሆን የለበትም። ዋናው መታየት ያለበት የአድራጊው መልካም ፈቃድ ብቻ ነው የሚል ነው።

እነዚህ የተለያዩ መለኪያዎች ቢኖሩም በብዙዎቹ መልካም በሚባሉ ተግባራቶች ላይ ስምምነት አላቸው። በተጨባጭ በቀን ተቀን የምንመራባቸውን የሞራል ህጎች ብንመለከትም የእነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች አስተዋጽኦ ውጤቶች ናቸው። ዞሮ ዞሮ በአለም ላይ የምናገኛቸው የስነምግባር ድንጋጌዎች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የእነዚህ አመለካከቶች ነጸብራቅ ናቸው ቢባል ምክንያታዊ ነው። የትኛው የበለጠ ነው የሚለውን እያንዳንዱ አንባቢ ለራሱ ተመራምሮ እንዲደርስበት ትተነዋል።

<u>*የመወያያ ጥያቄዎች*</u>

1. አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ማንም ሰው ቢሆን የመጨረሻ መጨረሻ የራሱን ደስታ ፈልጎ ነው ምንም ነገር የሚያደርገው። አንዳንዱ አጭር ተመልካች በመሆኑ ለጊዜያዊ ደስታ ሲል ዘላቂ ደስታውን ይሰዋል። አንዳንዱ ዘላቂ ደስታ ለማግኘት ሲል ጊዜያዊ ደስታውን ይሰዋል። ለምሳሌ ትክክለኛ ነገርን ማድረግ እራስን ከማስደሰት አልፎ ሌሎችም ሰዎች የሚጠቀሙበት ይሆናል ብለው ይከራከራሉ። ከዚህ ሀሳብ ጋር ምን ያህል ይስማማሉ?

2. ከመዋሸት እውነት መናገር ይመረጣል። ካሳ ቤቱ ተኝቶ ሳለ ጓደኛው ስልክ ይደውልለታል። ይሁንና በዚያን ሰአት ደክሞት ስለነበረ መልስ ለመስጠትም አልፈለገም። በሌላ ቀን ጓደኛው አግኝቶት ስልክ ደውዬልህ ነበር ምነው? ብሎ ይጠይቀዋል። ካሳ ደክሞኝ ስለነበረ አላነሳሁትም ቢለው ጓደኛው እንደሚቀየመው ያውቃል። ስለሆነም እሱ ከሚቀየመኝ ብሎ እቤት ስላልነበርኩ ነው በማለት ይመልስለታል። ካሳ መዋሸቱ ተገቢ ነው? ወይስ እውነቱን ሊናገር ይገባ ነበር?

3. አንድ ሀብታም ልጃቸው ታግታ አጋቾቿ ልጅቷን ለመልቀቅ ብር አንድ ሚሊዮን እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ። ፖሊሶች ግን ገንዘቡን መስጠት እንደሌለባቸው ከሰጡ ግን እነዚህ ሽብር ፈጣሪዎች በዚህ መልኩ እንደሚገፉበት ይህም ለሌላ የጠለፋ

ስራ እንደሚያበረታታቸው ይህም ጉዳቱ የከፋ እንደሚሆን ይመክሯቸዋል። ሰውየው ለልጃቸው ደህንነት አስበው ገንዘቡን ሰጥተው ያስለቀቁ? ወይስ ወደፊት ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጸም የልጃቸውን ህይወት ለአደጋ ያጋልጡ?

4. ዳኛው በምርጫ ጊዜ የመረጠው ፓርቲ ሳያሸንፍ ቀርቶ ያልመረጠው ፓርቲ አሸነፈ። ይህ ፓርቲ ከአሸነፈ በኋላ የሚዲያ ህግ ያወጣል። ዳኛው የሚዲያ ህጉን የዴሞክራሲ መብትን ያጣብባል በማለት አይደግፈውም። የሚዲያ ህጉን ጥሰዋል ተብሎ ክስ በተመሰረተባቸው የሚዲያ ሰዎች ላይ የቀረበውን ክስ በተቻለ መጠን እነሱን እንደሚጠቅም አድርጌ መተርጎም አለብኝ። ምክንያቱም 1) ያልመረጥኩት ፓርቲ የሚያወጣውን ህግ የማክበር የሞራል ግዴታ የለብኝም። 2) ይህ የሚዲያ ህግ እራሱ ዴሞክራሲያዊ መብትን ያጣብባል። ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ አይደለም ይላል። የዳኛውን አቋም እንዴት ትገመግሙታላችሁ?

5. መስፍን ሰው በመደብደብ ተከሶ፣ እስራት ተፈርዶበት እስሩን ጨርሶ ከወጣ በኋላም ወደድብደባ ይመለሳል። በዚህ መልኩ አራት ጊዜ ተከሶ አራት ጊዜ ተፈርዶበት አራት ጊዜም ታስሮ ወጥቷል። ለአምስተኛ ጊዜ በሰው መደብደብ ወንጀል ተከሶ ምርመራው ተጠናቆ ለአቃቤ ህጉ ደረሰው። አቃቤ ህጉ ተከሳሹን ያውቀዋል። ይሁንና መዝገቡን ሲመረምር ማስረጃው በቂ አይደለም። አሁን ካልተከሰሰና እስር ቤት ካልገባ ሌላ ሰው ይደበድባል። ሌላ ጉዳት ነው። ስለሆነም ያላዩም ቢሆን ምስክሮች ፈልጌ ምን እንደሚመሰክሩ ነግሬያቸው ይህ ሰው እስር ቤት መግባት አለበት ብሎ ይወስናል። እንዴት ትገመግሙታላችሁ? አቃቤ ህጉ በቂ ማስረጃ ባይኖረውም ነገር ግን ዳኛውም የታወቀ ተደባዳቢ መሆኑን ስለሚያውቁ እስር ቤት እንዲገባ መወሰናቸው አይቀርም፣ ባይወስኑም እኔ እራሴ በቂ ማስረጃ የለውም ብዬ ይህንን መዝገብ ከምዘጋ የአቅሜን ሞክሬ ፍርድ ቤት እንዳደረገ ያድርገው ብሎ ቢወስንስ? እንዴት ትገመግሙታላችሁ?

6. አራት ለአሰሳ የተላኩ ወታደሮች በጠላት ወታደሮች ቁጥጥር ስር ይወድቃሉ። የጠላት ጦር ሀላፊዎችም ምስጢር እንዲያወጡ ያሰቃዩዋቸዋል። በዚህ ማሰቃየት

ከአቅሙ በላይ የሆነበት አንዱ ምስጢሩን ለማውጣት መዘጋጀቱን ይነግራቸዋል። ይህንን የሰሙት ሶስቱ ለብቻቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይወያያሉ። አንደኛው ምስጢሩ ቢወጣ ከነዋላችን ያሉ የኛ ወታደሮች ህይወት አደጋ ላይ ስለሚወድቅ አንቀን እንግደለው ይላል። ሌላኛው እንዳይናገር እንምከረው፣ እምቢ ካለ ግን ከዚህ በላይ ማድረግ የለብንም። እኛ እስካልተናገርን ድረስ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ አንሆንም አለ። ምን አስተያየት አላችሁ?

1.4. የሙያ ስነምግባር ምንድነው?

በመጀመሪያ ስለሙያ ስነምግባር ከመነጋገራችን በፊት ሙያ ምንድነው? የሚለውን መመለስ ተገቢ ነው።

ሙያ በስልጠና የሚገኝ ንድፈሀሳባዊ እውቀት ችሎታና ክህሎት መሰረት ያደረገ የዳበረ ልምድና የጠለቀ ግንዛቤ የሚጠይቅና ለህብረተሰቡ ተጨባጭ ጠቀሜታ የሚሰጥ ስራ ነው።

ብዙዎች ሙያ አራት መሰረታዊ ባህርያት እንዳሉት ይገልጻሉ።[4]
እነርሱም

- ልዩ የሆነ እውቀት የሚጠይቅ፣
- ወደሙያው ለመግባት የተወሰነ የመግቢያ መስፈርት ያለው፣
- ማህበራዊ እሴት ያለውና ለሌሎች ጥቅም የሚሰራ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ፣
- ስራውን በሚመራና በሚቆጣጠር የስነምግባር ደንብ የሚመራ መሆኑ ናቸው።

ከባለሙያ ልዩ ባህርያት መካከል በመስኩ በሌሎች በቀላሉ ሊተካ የማይችል በረጅም ስልጠናና ጥረት የተገነባ እውቀትና ክህሎት ባለቤት መሆን ማለት ነው።

---

[4] ፌ.ስጸኮ፣ የሙያ ስነምግባር ምንነት (ያልታተመ) ገጽ 5

ሙያተኛ በተወሰነ የስራ መስክ ላይ በከፍተኛ ስልጠና ወይም ትምህርት የተገኘ ልዩ እውቀት ክህሎትና ልምድ ያላቸው እውቀታቸውንና ልምዳቸውን ለህብረተሰቡ ጠቀሜታ ለማዋል ሌሎችን ለመምራትና ለማሰልጠን አቅም ያላቸው ሰዎች መለያ ነው፡፡[5]

<u>የሙያ ስነምግባርስ ምንድነው?</u>

ህብረተሰቡ በተለያየ ደረጃ የሚገጥሙትን ችግሮች ለመፍታት በየዘርፉ የተለየ እውቀትና ችሎታ ያላቸውን ሙያተኞች ይሻል፡፡ ይህ እውቀት በአግባቡ ከተጠቀሙበት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፣ በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ደግሞ ሊጎዳ ይችላል፡፡ ይህንን ደግሞ ህብረተሰቡ ሊቆጣጠር አይችልም፡፡

በዚህ ምክንያት ሙያተኞች ያላቸውን እውቀት ክህሎትና ችሎታ ለህብረተሰቡ ጠቀሜታ እንዲያውሉትና ህብረተሰቡ የጣለባቸውን አመኔታ እንዲጠብቁ በአንድ የሙያ መስክ የተሰማሩ ሙያተኞች የሚመሩበት የሚከተሉትና የሚተዳደሩበት የስነምግባር ደረጃ ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡

ስለሆነም የሙያ ስነምግባር በአንድ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ አባላት በጋራ የሚመሩበት የሚከተሉትና የሚተዳደሩበት ራሳቸውንና ስራቸውን ለመቆጣጠር የሚያግዝ የስነምግባር ደረጃን የሚያመለክት መርህ ወይም ደንብ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በአንድ ሙያ የተሰማሩ ሙያተኞች እውቀታቸውንና ችሎታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ሙያዊ ግዴታቸውንና ሀላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ አቅጣጫ የሚያሲዝና የሚገዙበት ደንብ ማለት ነው፡፡

በጥቅሉ ስንመለከተው የሙያ ስነምግባር ማለት የአንድ ሙያ ባለቤት የሆኑ ሰዎች የዚያን ሙያ የስነምግባር መመሪያዎች ይዘትና አስፈላጊነትን በተመለከተ የደረሱበት ስምምነት ወይም አስተያየት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ከዚህም በመነሳት የሙያ ስነምግባር የተለየ ግብረገባዊእሴት ሳይሆን በአንድ ሙያ ውስጥ የታቀፉ ሰዎች በስራቸው ሂደት የሚመሩበት ትክክለኛ ጠባይ ወይም ተቀባይነት የሌለውን የሚያመለክት ነው ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡

---

[5] ዝኒ ከማሁ ገጽ 6

1.5. የዳኞችና የአቃቤ ህግ የሙያ ሥነምግባር አስፈላጊነት

የሙያ ሥነምግባርን ማክበር ለዳኞችም ሆነ ለአቃብያነ ሕግ እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ዳኞችም ሆኑ አቃብያነ ህግ በዜጎች ነጻነትና ሀብት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ውሣኔዎችን በዕለት ተዕለት የፍትህ አስተዳደር ተግባራቸው ውስጥ ሲያሳልፉ ነው የሚውሉት፡፡ የዜጎች መሠረታዊ ነጻነቶችና መብቶች ላይ የሚወስኑ ሙያተኞች ደግሞ ከሌሎች አካላት ሁሉ በላቀ ደረጃ ሥነምግባርን የተላበሱ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ዳኞችና አቃብያነ ሕግ የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች ሕጉንና ፍሬ ነገሩን በማየት ብቻ በማናቸውም ሌሎች ምክንያቶች ሳይመሩ መወሰን አለባቸው፡፡ ይህ ደግሞ ከዳኞችና ከአቃብያነ ሕግ ከፍ ያለ የሥነምግባር ደረጃን የሚጠይቅ ነው፡፡

አንድ የህግ ምሁር ከህግ ሙያ ጋር በተያያዘ የሙያ ስነምግባር አስፈላጊነትን ለመግለጽ የሚከተለውን አስቀምጠዋል፡፡

"We form a particular group in the community. We comprise a select part of an honorable profession. We are entrusted, day after day, with the exercise of considerable power. Its exercise has dramatic effects upon the lives and fortunes of those who come before us. Citizens cannot be sure that they or their fortunes will not some day depend upon our judgment. They will not wish such power to be reposed in anyone whose honesty, ability or personal standards are questionable. It is necessary for the continuity of the system of law as we know it, that there be standards of conduct, both in and out of court, which are designed to maintain confidence in those expectations."
(2nd ed. (1997) p9).

እነዚህ ተቋማት ጥሩ ሥነምግባር በተላበሱ ሙያተኞች በሚገባ የተደራጁ ካልሆኑ ከአድሎ የጸዳና ፍትሃዊ አገልግሎት ሊያበረክቱ አይችሉም፡፡ ቢችሉም እንኳን በህብረተሰቡ ዘንድ ካልታመኑ ብዙም ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ለዚህ ነው ፍትህ ማድረግ ብቻውን በቂ አይደለም ፍትህ መደረጉን ሌሎችም መገንዘብ መቻል አለባቸው የሚባለው፡፡ የፍትህ ተቋማት ለእውነተኛ ፍትህ የቆሙ መሆኑን ህብረተሰቡ የሚረዳው በነዚህ ተቋማት ያሉ ሙያተኞች ሁሉ በሥነምግባራቸው ላቅ ያሉና ለሌሎችም አርአያ

መሆን የሚችል ባህርይ ወይም በጎ ምግባር በሥራቸውና በሚሰጡት አገልግሎት ሂደት ሲያሳዩ ነው፡፡ ስለዚህም ዜጎች በህግ ልእልና እንዲያምኑና በዴሞክራሲያዊ ባህል አለመግባባቶችን እንዲፈቱ የፍትህ ተቋማት ጥሩ ሥነምግባር ያላቸውን ሙያተኞች ለማፍራት ትኩረት አድርገው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የነዚህ ተቋማት ህልውናና ተቀባይነት በዳኞች ወይም አቃብያነ ሕግ መልካም ሥነምግባር ላይ የተመሰረተ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል በ2007 ባሰራጨው የሙስና ሁኔታ ሪፖርት «ሙስና በአብዛኛው የአለማችን ሀገሮች ለፍትህ መጓደል በተለይም የወንጀል ሰለባዎችና የተከሰሱ ሰዎች ፍትሃዊና ከአድሎ ነጻ በሆነ መልኩ የመዳኘት መብት እንዳይከበር ምክንያት መሆኑን»[6] ያብራራል፡፡ ይህ ሁኔታ በሀገራችንም ቢሆን ተመሣሣይ ገጽታ ያለው በመሆኑ ጥሩ ሥነምግባር ያላቸው የሕግ ሙያተኞችን በመፍጠር በፍትህ ተቋማት አካባቢ የሚታየውን ሙስናና ብልሹ አሠራር ከሥር መሠረቱ ማስወገድን ይጠይቃል፡፡

በተለይም ዳኞች በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የበጎ ምግባርና ግብረገብ መገለጫ እንደመሆናቸው መጠን ህብረተሰቡ መብቶቹ ሳይከበሩ ሲቀሩ ወደ ፍርድ ቤቶች የሚመጣ በመሆኑ ያለ አንዳች አድሎ በመሥራት በህብረተሰቡ ተአማኒነት ማግኘት ይገባቸዋል፡፡ ህብረተሰቡ የፍትህ ተቋማት ከሙስና የፀዱ አይደሉም ብሎ ማመኑ በራሱ በጣም አደገኛ ነው፡፡ በፍትህ ወይም በሕግ ልዕልና ላይ ህብረተሰቡ ጥርጣሬ ካሳደረ ልማትም ሆነ ዴሞክራሲ አይታሰብም፣ ይልቁንም ሙስና ይንሰራፋል፡፡ ለዚህ ነው የሙያ ሥነምግባር ለልማትም ሆነ ለዴሞክራሲ እንዲሁም ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው የሚባለው፡፡ የዳኝነት ሥርዓቱ ባጠቃላይ የህዝብ አደራን የተሸከመ በመሆኑ በፍትህ አስተዳደር ሥራ ላይ የላቀ ሥነምግባር ባላቸው ሙያተኞች የተደራጀ መሆን ይገባዋል፡፡ የሥነምግባር አስፈላጊነትም ከዚህ አንጻር ነው መመዘንና ትኩረት ማግኘት ያለበት፡፡

ዳኞች እና አቃቤ ህጎች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 9/2) መሰረት ህገመንግስቱን የማክበርና የማስከበር ሀላፊነት አለባቸው፡፡

[6] Transparency International, Global Corruption Report 2007

በተለይም በአንቀጽ 13 የተቀመጡትን መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ከማክበር ባሻገር የማስከበር ሀላፊነት ስላላቸው ይህን ህገመንግስታዊ ግዴታዎችን በአግባቡ እንዲወጡ ይህንን ያለአግባቡ ሲሸራረፉ ወይም ስልጣናቸውን ያለአግባብ ሲጠቀሙና ፍርድን ሲያዛቡ ደግሞ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማስቻል ሙያቸው የሚመራበትን የስነምግባር መርሆዎች ጠንቅቀው ማወቅና መተግበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ክፍል ሁለት

የዳኝነት/ዓቃብያነ ሕግ የሙያ ሥነምግባር በጠቅላላው

ዝርዝር አላማዎች

ሰልጣኞች ይህንን ክፍል ሲያጠናቅቁ፣

1. የዳኞችንና የአቃቤ ህጎችን የሙያ ስነምግባር ለመወሰን በአለም አቀፍ ደረጃና በአገር ውስጥ የተከናወኑ ዋና ዋና ክንዋኔዎችን ያስረዳሉ፡፡
2. የዳኝነት ነጻነትን ለማረጋገጥ ከዳኞች የሚጠበቁ ሙያዊ ስነምግባራዊ ባህርያትን መለየትና ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ፡፡
3. ከአድልዎ በጸዳ መልኩ ለመስራት የሚያስችለውን የዳኝነት ባህርይን መለየትና ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ፡፡
4. የፍርድ ስራን በሀቀኝነት ለማከናወን ከዳኛው የሚጠበቁ ሙያዊ ስነምግባራዊ ባህርያትን ተረድተው ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ፡፡
5. ዳኛው ሊያከብራቸው የሚገቡ የቅንነት ባህርይ መገለጫዎችን ተረድተው ተግባራ ማድረግ ይችላሉ፡፡
6. በዳኝነት ስራ የእኩልነት መርህን ተረድተው ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ፡፡
7. በዳኝነት ስራ ትጋትና ጥረት ማሳየት አስፈላጊነትን ይረዳሉ፡፡ በተግባራቸውም ለዚህ ዝግጁ ይሆናሉ፡፡
8. አቃቤ ህግ አመዛዛኝና ከአድልዎ በጸዳ መልኩ መስራት እንደሚገባው ይረዳሉ፡፡ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መነሳሳት ይኖራቸዋል፡፡
9. ፍትሀዊነት የአቃቤህግ ሊያከብረው የሚገባ ባህርይ መሆኑን ተረድተው ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ ይሆናሉ፡፡
10. አቃቤ ህግ ስራውን ለማከናወን ነጻነት እንደሚያስፈልገውና ከነጻነት ጋር በተያያዘ ከአቃቤ ህግ የሚጠበቁ ባህርያትን ይገልጻሉ፡፡
11. ከአቃቤ ህግ ስለሚጠበቅ ተጠያቂነት ይረዳሉ፡፡
12. ምስጢር የመጠበቅ የአቃቤ ህግ ሀላፊነት መሆኑን ተረድተው ያውቃሉ፡፡
13. የሙያ ብቃት ከአቃቤ ህግ የሚጠበቅ ባህርይ መሆኑን ይረዳሉ፡፡

2.1. መግቢያ

ሕግ እንደ አንድ የሙያ ዘርፍ በታሪክ ቀደምትነት ካላቸው ሙያዎች መካከል የሚመደብ ነው፡፡ ታሪክ እንደሚያሳየን ከሆነ ሕግና የሕግ ሙያተኞች ከቀደምት ጊዜ ጀምሮ የተደራጁ ማህበረሰቦች ሁሉ ዓይነተኛ መገለጫ ሆነው መሰንበታቸውን ነው፡፡ ዊድሮው ዊልሰን የተባሉ አንድ ምሁር «....ማንኛውም የፖሊስ ጥያቄ በሂደት የህግ ክርክር የሚያስነሳ ጭብጥ መሆኑ አይቀርም ....»[7] ብለው የተናገሩት በተለይም ዛሬ የዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ለሕግ ልዕልና፣ መልካም አስተዳደርና ሰብዓዊ መብቶች መከበር ከሰጠው ትኩረት አንጻር ስንመዝነው ሕግና ፍትህ በታሪክ ብቻ ሳይሆን ዛሬም የሰው ልጆች መሠረታዊ እሴት መሆናቸውን ነው፡፡ ፕሮፌሰር ሮናልድ አሮንሰንና ዶናልድ ዌክስቴይን የሕግ ሙያተኞች በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ያላቸውን ከፍተኛ ሚና ሲያብራሩ እንዲህ በማለት ነው፡፤

:

> ....(1) lawyers are instrumental in accompanying the purposes of law; the establishment and operation of governmental processes, the protection of individuals from over reaching by government; the accommodation of individual freedom with essential societal peace and order; the assertion and balanced response to often conflicting human wants and desires; the settling and prevention of disputes; the application of general rules and policies to individuals; the invocation of and design of the other means of ordering human conduct in accordance with the perceived goals of society; the administration of justice,[8]

ይህም ወደ አማርኛ ሲመለስ ከሞላ ጎደል የሚከተለውን ግርድፍ ትርጉም ይሰጠናል፡፡ የሕግ ሙያተኞች ለሕጉ ዓላማ በመቆምና ህጉን ተግባራዊ በማድረግ፣ የመንግሥት አወቃቀርንና አሰራርን በመወሰን ረገድ፣ የግለሰቦች መብትና ነጻነት ከመንግሥት ጣልቃ

---

[7] Robert H.Aronson andDonald T.Weckstein, Professional REsponsibility in a Nutshell,(2d,1991)p.2

[8] Id at p.4

ገብነት እንዲጠበቅ በማድረግ በኩል፣ የግለሰብ ነጻነት ከማህበረሰቡ ሰላምና ደህንነት አንጻር ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲከበር ከማድረግ አኳያ፣ እርስ በእርሳቸው የማይጣጣሙ የሰዎችን ፍላጎትና ጥቅም በመለየት ሚዛናዊነት የተላበሰ ምላሽ ከመስጠት አንጻር፣ አለመግባባቶችን ከመፍታትና እንዳይከሰቱ ከመከላከል አንጻር፣ አጠቃላይ ሕጎችና ፖሊሲዎች በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ ተፈጻሚነት አንዲኖራቸው በማድረግ በኩል፣ ከህብረተሰቡ የመጨረሻ ግብ አንጻር የሰዎች ጠባይ የሚመራባቸውን ስለቶች በመቀየስና የተሳካ የፍትህ አስተዳደር እንዲኖር በማድረግ በኩል ወሳኝ ሚና ነው ያላቸው፡፡

የሕግ ሙያተኞች እነዚህን ተግባራት የሚያከናውኑት በዳኝነት፣ በማማከር፣ በማደራደር፣ በማቀድ፣ ጥብቅና በመቆም፣ በማርቀቅ፣ በምርመራ፣ በመክሰስ፣ በማስተማር፣ በመጻፍ፣ በመሚገትና ወዘተ ሥራዎች ላይ በሚያሰማሩበት ጊዜ ነው፡፡ እነዚህን አገልግሎቶች በሚገባ ለማበርከትም የሕግ ሙያተኞች "… በቂ የመሠረታዊ የሕግ ሥነ-ሥርዓት ዕውቀት…" የመግባባትና የሙግት ክህሎት፣ ታማኝነት፣ ታታሪነት፣ ሚስጢራዊነት፣ ቅንነት፣ ሀቀኝነት፣ በንቃት ነገሮችን መከታተልና ውሣኔ የሚሹ ነገሮች ላይ ቆራጥነትን መላበስን፣ ለሕጉ ግቦች ተግባራዊነትና ለሂደቱም መከበር በጽናት መቆምን…"[9] ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም የህግ ሙያተኞች ከላይ የተዘረዘሩትን ባህርያት እንዲያዳብሩና ከመጥፎ ምግባር ራሳቸውን እንዲያርቁ ለማድረግ የሙያ ሥነምግባርን ማወቅና አምነውበት መተግበር ይገባቸዋል፡፡ አጠቃላይ የፍትህ ስርአቱ በጠንካራና አስተማማኝ መሰረት ተገንብቶ በሃገራችን ሊረጋገጥ ለሚፈለገው ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም፣ ዲሞክራሲና የህግ የበላይነት መስፈን ዋስትና ሊሆን የሚችለው በሃቀኝነት በራስ መተማመን ከጉቦ ከአድልዎ እና ከወገናዊነት የጸዱ በስነምግባራቸው ከህብረተሰቡ ከበሬታ የተቸራቸው ዳኞችና አቃቤ ህጎችን ያካተተ ሲሆን ነው፡፡ በዚህ ክፍል የህግ ሙያተኞች የሆኑ ዳኞችና አቃቤ ህጎች ከሙያቸው አንጻር ሊከተሉት ስለሚገባ ስነምግባር እንመለከታለን፡፡

---

[9] Ibid

2.1.1. <u>የዳኞችና የዓቃብያነ ሕግን የሙያ ሥነምግባርን ለማዘጋጀት በአለምአቀፍ ደረጃ ያለተሞክሮ፡-</u>

<u>ዳኞችን በተመለከተ</u>

ጠንካራና ነጻ እንዲሁም ሥነምግባርን የተላበሰ የዳኝነት ሥርዓት ለሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት መኖር፣ ለዴሞክራሲና የህግ ልዕልና የማዕዘን ድንጋይ መሆኑን የዓለም ህብረተሰብ ከተገነዘበ ሰንበትበት ብሏል፡፡ የባንገሎር የዳኝነት ሥነምግባር መርሆዎች ሀተታ ዘምክንያት ሰነድ ይህንን ሀሳብ ከዚህ እንደሚከተለው አብራርቷል፡፡

> A judiciary of undisputed integrity is the bedrock institution essential for ensuring compliance with democracy and the rule of law. Even when all other protections fail, it provides a bulwark to the public against any encroachments on its rights and freedoms under the law.

ከዚህ እንደምንረዳው ፍትሃዊና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚሠራ የዳኝነት ተቋም ለዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት መከበር ወሳኝ መሆኑንና የሕዝብ መሠረታዊ መብትና ነጻነት በሚገፈፍበት ጊዜ ለነዚህ መብቶችና ነጻነቶች መከበር እንደ መጨረሻ ዋስትና የሚያገለግል መሆኑን ነው፡፡ ይህን ትልቅ ኃላፊነት የዳኝነት ተቋሙ ሊሸከም የሚችለው ደግሞ በጥሩ ሥነምግባር የታነጹ ባለሙያዎች ሲኖሩት ብቻ እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

ከዚህ በመነሳት በዓለም አቀፍ ደረጃ ነጻና ጠንካራ የሆነ የዳኝነት አካል እንዲኖርና ይህም የዳኝነት አካል ከተለያዩ ተጽዕኖዎች ተጠብቆ ብቁና ውጤታማ በሆነ መንገድ የዳኝነት አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ የተቋሙን ነጻነት ማረጋገጥን በተመለከተ ዓለምአቀፍ መርሆዎችን ለማቋቋም የተለያዩ ሙከራዎች በተለያዩ ጊዜያት መደረጋቸውን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1981 ዓ.ም. የሲራኩዛ መርሆዎች ተብሎ የሚጠራ ረቂቅ የፍ/ቤቶች ነጻነትን አስመልክቶ የቀረበ ሰነድ ሲኖር ይህም ሰነድ ለፍ/ቤቶች ነጻነትን ማረጋገጥ

እንደሚያስፈልግ የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ ሰነድ የተዘጋጀው በዓለም አቀፍ የወንጀል ሕግ ማህበር፣ በዓለም አቀፍ የሥነ-ሕግ ተመራማሪዎች ማህበር (ኢንተርናሽናል አሶሲዬሽን ኦፍ ጁሪስትስ) በዳኞችና የሕግ ባለሙያዎች ነጻነት ማዕከል (ሴንተር ፎር ኢንዲፔንደንስ ኦፍ ጀጅስኤንድ ሎየርስ) ነው፡፡

ከዚህም በመቀጠል እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1982 ዓ.ም. ደግሞ የዓለም አቀፍ የባር አሶሲዬሽን ሚኒመም እስታንዳርድስ ኦፍ ጁዲሺያል ኢንዲፔንደንስ ተብሎ የሚጠራውን የዳኝነት ነጻነት መደበኛ ደንብ አጽድቋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1985 ዓ.ም. ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የዳኝነት ነጻነት መሠረታዊ መርሆዎች የሚለውን ሰነድ አጽድቆ አገሮች በዚሁ መሠረት ለፍ/ቤቶች ነጻነት የህግ ዋስትና እንዲሰጡና የዳኝነት ነጻነትን እንዲያከብሩና እንዲጠብቁ አሳስቧል፡፡[10] ሰነዱ በመግቢያው ላይም ዳኞች በዜጎች ሕይወት፣ ነጻነት፣ መብት፣ ግዴታና ንብረት ላይ የመጨረሻ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን ስላላቸው ሥራቸውን በሙሉ በነጻነት ማከናወናቸው የግድ እንደሆነ በማስቀመጥ ዳኞች የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች በሚመረምሩበት ወቅት በምንም ምክንያት ከየትኛውም አቅጣጫ ለሚመጡ ቀጥተኛ ወይንም ቀጥተኛ ላልሆኑ ተጽኖዎች፣ ማባበያዎች፣ ግፊቶች፣ ማስፈራራቶችና ጣልቃ ገብነቶች ሳይበገሩ ያለ አንዳች ገደብ በፍሬ ነገርና በሕግ ላይ በመመስረት ውሣኔ መስጠት እንዳለባቸው ያስገነዝባል፡፡[11]

ከዚህ ባሻገር እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ2000 ዓ.ም. ሙስናን ለመከላከልና ብሎም ለማስወገድ እንዲሁም የዳኝነት ሥርዓቱን ሚዛናዊነት ለማረጋገጥ የፖሊሲ ማዕቀፍ በተባበሩት መንግሥታት የዳኞችና የሕግ ባለሙያዎች ነጻነት ማዕከል በተጠራ የኤክስፐርቶች ቡድን ቀርቧል፡፡[12] ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ

---

[10] .በ1985 አ.ም በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ የወጣውን የዳኝነት መሰረታዊ መርሆ ሰነድ መግቢያና አንቀጽ 1 ይመልከቱ፡፡
[11] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 2
[12] የባንግሎር የዳኞች ስነምግባር መርሆዎች ሀተታ ዘምክንያት ይመልከቱ

የዓለም ክፍሎች ክፍለ አህጉራዊ የሆኑ የዳኞች ነጻነትን በተመለከት የተደረሱ በርካታ ስምምነቶች[13] እንዳሉ ሳንጠቅስ አናልፍም፡፡

በተለያየ ጊዜያት በዚህ ረገድ ከተደረጉ ዓለምአቀፍ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በተሟላ መልኩ ዳኞች የሚመሩባቸውን የሥነምግባር ደንቦች ለመጀመሪያ ጊዜ በዝርዝር ለማስቀመጥ የተሞከረው በባንግሎር የዳኞች ሥነምግባር መርሆዎች ላይ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በአፕሪል 2000 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት አስረኛው የወንጀል መከላከልና የእስረኞች አያያዝ ኮንግረስ ጉባዔ በሚካሄድበት ወቅት በቪዬና ኦስትሪያ ከአፍሪካ፣ ከኤሲያና ፓሲፊክ አካባቢ የተውጣጡ የ9 ሀገሮች የፍ/ቤቶች ኃላፊዎችና ሲኒየር ዳኞች ተካፋይ በሆኑበት ስብሰባ የራሳቸውን ተቋም ሥርዓት ለማስያዝና ተጠያቂነታቸውን ለማረጋገጥ ዳኞች የሚመሩባቸውን የሥነ-ምግባር መርሆዎች በዓለምአቀፍ ደረጃ ማውጣቱ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ጁዲሺል ኢንቴግሪት ግሩፕ የሚባል ቡድን ተቋቁሞ ዓለምአቀፋዊ ይዘት ያለው ሰነድ አጥንቶ እንዲያቀርብ ኃላፊነት ተሰጥቷል፡፡ ለዚህም ተግባር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ያነሳሳው ዋንኛው ነገር በተለያዩ ሀገሮች ሕዝቡ ከዳኝነት ተቋማት ላይ ያለው እምነት በሙስናና በአድሎዊ አሠራር ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ መምጣቱን የሚያሳዩ የተለያዩ የጥናት ውጤቶች በመበራከታቸው እንደሆነ አንዳንድ ዋቢ ጽሁፎች ያስረዳሉ፡፡ ጁዲሺያል ኢንቴግሪቲ ግሩፕ ተብሎ የሚጠራው ቡድንም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በፌብሩዋሪ 2001 ዓ.ም. በህንድ ባንግሎር በተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እስፖንሰር አድራጊነት ተሰብስቦ በሙያተኞች የቀረበለትን ረቂቅ ደንብ ከመረመረ በኋላ የሥነ-ምግባር ደንቡን ዋንኛ እሴቶችና መርሆዎች በዝርዝር አስቀምጦ የመጀመሪያውን ረቂቅ የባንግሎር የዳኞች ሥነምግባር መርሆዎችን አጽድቋል፡፡ ከዚህም በኋላ ይህ ረቂቅ ደንብ በጁን 2002 ዓለም በአውሮፖ ህብረት የዳኞች የጋራ የምክክር ጉባዔ ላይ ቀርቦ በውይይት እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኖቬምበር 2002 የኮንቲነንታል የሕግ ሥርዓትን የሚከተሉ ሀገሮች(ብራዚል፣

---

[13] ዝኒ ከማሁ ለምሳሌ ያህል የኦገስት 1997ቱ የቤይጂንግ የዳኝነት ነጻነት መሰረታዊ መርሆዎች፣ የላቲመር ሃውስ ጋይድላይንስ ተብሎ የሚጠራው ሰነድና የ1998ቱ የአውሮፓ ህብረት የዳኞች ቻርተር መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡

ቼክ ሪፐብሊክ፣ ግብፅ፣ ፈረንሳይ፣ ሜክሲኮ፣ ሜዛንቢክ፣ ሆላንድ፣ኖርዌይና ፊሊፒንስ) የፍ/ቤት ኃላፊዎች በተሳተፉበት መድረክ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል። በዚህ ውይይትም በአብዛኛዎቹ የሥነምግባር ደንቡ እሴቶችና መርሆዎች ላይ የኮሞን ሎውና የኮንቲነንታል ሎው ሀገር ዳኞች ከስምምነት የደረሱ ሲሆን በጥቂት ጉዳዮች ላይ ብቻ መጠነኛ ልዩነቶች ተስተውሏል። ከታዩት ልዩነቶች መካከል ለአብነት ለመጥቀስ ያህል የሥነምግባር መርሆዎቹ የቅደም ተከተል ሁኔታ፣ የሥነምግባር ደንቡ መጠሪያ ኮድ መባል እንደሚገባው እንዲሁም በሰነዱ መግቢያ ላይ የዳኝነት ሥልጣን ምንጬ የህብረተሰቡ የዳኝነት ተቋሙን ሞራላዊ ሥልጣንና በሀቀኝነት የመዳኘት ሁኔታን የመቀበሉ ጉዳይ ነው የተባለው የዳኝነት ሥልጣን ምንጭ ሕገ መንግሥት ነው ተብሎ እንዲሻሻል የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት የሚከተሉ ሀገሮች ዳኞች ጠይቀዋል።

ከዚህ በኋላ ነው የባንግሎር መርሆዎች የዳኝነት ነጻነትን፣ ሚዛናዊነትን፣ ምሉዕ ስብዕናን፣ ቅንነትን፣ እኩልነትን፣ ብቃትና ትጋትን እና መሠረታዊ የሥነምግባር እሴቶች በማቀፍ የተቀረጸው ለማለት ይቻላል። በአፕሪል 2003 ይህ ሰነድ ለተባበሩት መንግሥታት ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ቀርቦ ሀገሮችና የተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ ተቋማት የቀረበውን ረቂቅ ሰነድ እንዲያጤኑ ጋብዞ ነበር። በአፕሪል 2006 ዓ.ም. ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት የወንጀል መከላከልና የወንጀል አስተዳደር ኮሚሽን የተባበሩት መንግሥታት ኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮች ካውንስል አባል አገራት ፍ/ቤቶቻቸው ይህን ሰነድ መነሻ በማድረግ የዳኞችን የሥነምግባር ደንብ ከዚህ አንጻር በመቃኘት እንዲያወጡ ወይም እንዲያሻሽሉ የጠየቀ ሲሆን በዚህም መሠረት በጁላይ 2006 የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ካውንስልም የባንግሎር የዳኝነት ሥነምግባር መርሆዎችን በውሣኔ ቁጥር ECOSOC 2006/23 አጽድቋል።[14]

[14] ዝኒ ከማሁ

<u>የአቃብያነት ህግ ባለሙያዎችን በሚመለከት</u>

የዐቃብያነ ሕግ አደረጃጀትና በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ ያላቸው ሚና በየአገሩ የተለያየ ከመሆኑ የተነሳ ረዘም ላለ ጊዜ አንድ ወጥ የሆነ ዓለምአቀፋዊ የሥነምግባር መርህን ለአቃብያነ ሕግ ማውጣቱ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ አቃብያነ ሕግ የሚመሩበት የሥነምግባር ደንብ እንዲወጣ የተለያዩ ግፊት የሚፈጥሩ ሁኔታዎች የታዩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ሁለቱን ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የተለያዩ የዓለም ሀገራት አለምዓቀፋዊ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን መፈረማቸው የሚታወስ ሲሆን እነዚህ ስምምነቶችም በአግባቡ እንዲከበሩ የዐቃብያነ ሕግን የላቀ ተሳትፎና ሚና የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ከተባበሩት መንግሥታት ቻርተርና የሰብዓዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ መግለጫ ባሻገር የዐቃብያነ ህግን ከፍተኛ ተሳትፎ የሚጠይቁ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለምአቀፍ ስምምነት፣ ማሰቃየትንና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው ሰብአዊነት የጎደላቸውና አዋራጅ የሆኑ አያያዞችንና ቅጣቶችን ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት፣ የህጻናት ኮንቬንሽን ወዘተ... መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ስምምነቶች ለሰብዓዊ መብት አያያዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸውን ከፍርድ በፊት የተያዙና የተከሰሱ ሰዎችን መብት ይደነግጋሉ፡፡ ለምሳሌ በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎች በፍጥነት ወደ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ(የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 9(3)) እንዲሁም ፍትሃዊ በሆነ መልኩ የመዳኘትና ራስን የመከላከል መብትን ((የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 14) መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዐቃቤ ሕግ ገለልተኛ አካል እንደመሆኑ መጠን በወንጀል ምርመራ ሂደት የተያዙ ሰዎች ሰብዓዊ መብት በሚጣስበት ጊዜ የመርማሪ አካላትን ሕግ የተላለፈ ርምጃ የማረም ኃላፊነት እንዳለበት ይገነዘባሉ፡፡ ((የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 6/1/ እና 7 ሰብዓዊ መብት ሁሉን አቀፍ መግለጫ አንቀጽ 3 እና 5፣ ማሰቃየትንና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ሰብዓዊነት የጎደላቸውና አዋራጅ የሆኑ አያያዞችንና ቅጣቶችን ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት አንቀጽ 15)፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት የአስገዳጅነት ባህርይ ያላቸው ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች አለምዓቀፋዊ ይዘት

ያላቸው አስገዳጅ ያልሆኑ ድንጋጌዎች መኖራቸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ለምሳሌ እንደ አውሮፖ አቆጣጠር በ1990 ዓ.ም. የፀደቀውን የተባበሩት መንግሥታት የዐቃብያነ ህግ ሚናን በተመለከተ የወጣውን መመሪያ መመልከት ይሻል። ይህ መመሪያም ዓቃብያነ ህግ የሚመሩበትን የተግባር መርሆዎችና የሥነምግባር እሴቶችን የያዘ ነው። በእርግጥ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በመንግሥታት ላይ የአስገዳጅነት ባህርይ ባይኖራቸውም የመንግሥታትን ሀሣብ ስለሚገልጹ በትብብርና በቅን ልቦና መንፈስ በመንግሥታት ላይ ኃላፊነት ሊያስከትሉ ይችላሉ።

በሁለተኛ ደረጃ ዐቃብያነ ሕግ አለም አቀፋዊ ጠባይ ያላቸውን የሥነምግባር ደንቦች ማውጣት አስፈላጊ ያደረገው በአሁኑ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣው ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ወንጀሎች ናቸው። እነዚህን የተደራጁ ወንጀሎች መከላከልም ሆነ መቆጣጠር በተለያዩ ሀገራት ውስጥ የሚገኙ ዐቃብያነ ሕግን ትብብር የሚጠይቁ በመሆኑ ለዚሁ ትግል ፍሬያማነትም የዐቃብያነ ህግን የሥነምግባር ደንብ በጋራ ማበጀቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ ዓይነት አስተሳሰብም በመነሳት የአውሮፓ ህብረትም "Recommendation on the Role of Public Prosecution in the criminal justice system" በመባል የሚታወቅ ዐቃብያነ ህግን ሚናና ሥነምግባር የሚያትት ህግ አውጥቷል። ዐቃብያነ ህግም የጋራ ትብብር እንደሚያስፈልጋቸው በማጤን በዓለም አቀፍ የዐቃብያነ ሕግ ማህበር በኩል እንደ አውሮፖ አቆጣጠር በ1999 ዓ.ም. "Standards of Professional Responsibilitiy and Statement of the Essential duties and Rights of Prosecutors" ተብሎ የሚጠራ የተግባር መመሪያ አውጥቷል። በዚህ የተግባር መመሪያና በተባበሩት መንግሥታት የዐቃብያነ ህግ ሚና መመሪያ ላይ እንደተመለከተው ዐቃብያነ ሕግ የሙያ ተግባራቸውን በሚወጡበት ወቅት ሥራዎቻቸውን በፍጹም ገለልተኝነት፣ ሀቀኝነትና ሚዛናዊነት እንዲሁም በፍጹም ነጻነትና የተጠያቂነት መንፈስ ማከናወን እንደሚገባቸው ያትታሉ።

በመጨረሻም ሳይወሳ መታለፍ የሌለበት ነገር ቢኖር ህግ አስከባሪዎችን በተመለከተ የተባበሩት መንግሥታት "UN Code of Conduct for Law

Enforcement officials" ተብሎ የሚታወቀውን የህግ አስከባሪ ባለሥልጣናት የተግባር መመሪያ በዲሴምበር 1979 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ አጽድቋል፡፡ በዚህ የተግባር መመሪያ መሠረትም የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የሕዝብ አገልጋይ መሆናቸውና ተጠሪነታቸውም ለህብረተሰቡ እንደመሆኑ መጠን ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሙያ ግዴታቸውን በሚገባ መወጣት እንደሚገባቸው ከዚህም ባሻገር በሥራቸው ሂደት ኃይልን የሚጠቀሙት አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ መሆኑንና ጭካኔ የተሞላበት ድርጊትን ከመፈጸም መቆጠብ እንደሚገባቸውና ሲፈጽምም አይተው እንደሆነ ይህንን አዋራጅ የሆነ ቅጣት ወይም አያያዝ ዝም ብለው ማለፍ እንደማይገባቸው ይተነትናል፡፡

2.1.2. በአገራችን ኢትዮጵያ የዳኞችና የአቃቤ ህጎችን የሙያ ስነምግባር ለማዘጋጀት የተሰሩ ስራዎች

ዘመናዊ የህግ ስርአት በኢትዮጵያ ከተጀመረ ከግማሽ ምእት አመት በላይ ሆኖታል፡፡ ይሁንና የሙያውን ስነምግባር በሚመለከት በተለያዩ ህጎች ላይ በተበታተነ መልኩ ሲወጡ የነበሩ እንጂ በአንድ በተጠቃለለ መልክ አይገኙም፡፡ በ1981 የዳኞች የስነምግባር ደንብ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ ሲሆን፣ አቃቤ ህግን የሚመለከቱ የስነምግባር ድንጋጌዎችም በ1991 በወጣው የአቃቤ ህጎች ማቋቋሚያ ደንብ ላይ ተመልክቶ እናገኛለን፡፡

በሌላ በኩል በአገራችን አጠቃላይ የመንግስት አገልግሎትን ለማሻሻል የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ተቀርጾ በርካታ ስራዎች መሰራታቸው ይታወቃል፡፡ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ከተቀረጹት ንኡስ ፕሮግራሞች አንዱ የስነምግባር ንኡስ ፕሮግራም ሲሆን፣ በዚህ ንኡስ ፕሮግራም ተይዘው ከነበሩ ፕሮጀክቶች አንዱ የስነምግባር ደንብ ማዘጋጀት ነው፡፡

የሥነምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፐሮግራም የሥነምግባርን አስፈላጊነት ከሚከተሉት ነጥቦች ጋር በማያያዝ ገልጾታል፡፡[15]

- ሥነምግባር የአንድን ህብረተሰብ ጤናና ደህንነት ለመጠበቅ ወሳኝ መሆኑን፣
- ህጎችና ደንቦችን በማወቅ በሙያ የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ተፈጻሚነታቸውን ለማረጋገጥ ሥነምግባር ጉልህ ድርሻ ያለው መሆኑን፣
- የሙያ ብቃትን ለማስጠበቅና ለማሻሻል ሥነምግባር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን፣
- በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላቅ ያሉ የሥነምግባር ደረጃዎችን ለማስጠበቅና ለማጎልበት የሚረዳ መሆኑን፣
- ሙያዊ ግዴታን በታማኝነት፣በቅንነት፣ ያለአድሎና በተገቢው ጥንቃቄ ለመወጣት የሚያስችል መሆኑን ነው፣

በስነምግባር ንኡስ ፕሮግራም አስራ ሁለት የስነምግባር መርሆዎች የተለዩ ሲሆን፣ እነዚህን መርሆዎች መሰረት በማድረግ ለዳኞችና ለአቃቤህጎች የሚመሩበት ረቂቅ የስነምግባር ደንቦች ተዘጋጅተዋል፡፡ የተወሰኑ ክልሎች ማለትም ትግራይ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ህዝቦች እነዚህን መርሆዎች መሰረት አድርገው የስነምግባር ደንብ ያጸደቁ ሲሆን በፌዴራል ደረጃ ግን በረቂቅነት የሚገኙ ናቸው፡፡ መርሆዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡[16]

7. <u>**የተሟላ ስብእና (integrity)**</u> ይህ መርህ የመንግስት ሰራተኞች ስራቸውን በጥበብ/በስርዓት/በጥንቃቄ፣ በትጋት፣በሙሉ ጉልበት፣ በብቃትና ውጤታማ በሆነ አኳኋን ማከናወን እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡ ዳኞች የፍርድ ቤቱን ነፃነት ማስጠበቅ እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡
8. <u>**ታማኝነት (loyality)**</u> ይህ መርህ የመንግስት ሰራተኞች (ዳኞችም ሆኑ አቃቤያነህጎች) የፌዴራል ሕገ-መንግስቱን የማክበርና የማስከበር ከሙያቸው ይበልጥ ለሕገ-መንግስቱ ታማኝ መሆን እንዳለባቸው የባልደረቦቻቸውን ሕገ - ወጥ ድርጊት መሸፈን እንደሌለባቸው ያካትታል፡፡

---

[15] በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስነምግባር ስልጠና ማንዋል፣ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግንቦት 1999 አዲስ አበባ

[16] የስነምግባር ማሻሻያ ፕሮግራም ቅጽ 2

9. **<u>ግልጽነት (transparency)</u>** በዚህ መርህ ውስጥ በሕግ በተሰጠ ስልጣን መስራት በዚህ ውስጥ ውሳኔዎችን ግልፅ ማድረግ፣ መረጃን በሚስጥር መጠበቅ፣ ለሚሰጡት ውሳኔ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት የሚሉ ይገኙበታል፡፡
10. **<u>ተጠያቂነት (accountablity)</u>** ይህም መርህ በስራ ተጠያቂነት እንዳለ፣ ስልጣን ላለው አካል ስለተሰራ ስራ በእውነት ላይ የተመሰረተ ሪፖርት ማቅረብን የሚመለከት ነው፡፡
11. **<u>ምስጢር ጠባቂነት (secrecy)</u>** በማንኛውም ጊዜና ቦታ የባለጉዳዩችን ሚስጥር መጠበቅ እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡
12. **<u>ህግ አክባሪነት (respecting the law)</u>** የሚለው መርህ ማንም ሰው ከህግ በላይ አለመሆኑንና ህግን ማክበር የሚገባው መሆኑን ያስቀምጣል፡፡
13. **<u>አድልዎ አለመፈጸም (impartiality)</u>** የሚለው መርህ አድልዎ በሌለበት ሁኔታ የመስራት፣ በቀለም፣በዘር፣በብሄር ብሄረሰብ፣በጾታ፣በቋንቋ፣በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ወይም አግባብነት በሌለው ግምት ምክንያት የተለየ እንክብካቤ ወይም ልዩነት ሳያደርጉ በቀረበላቸው ጉዳይ ፍሬ ነገር እና ማስረጃ ላይ ተመስርተው ውሳኔ መስጠት እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡
14. **<u>ቅንነት (honesty)</u>** ይህ መርህ የገቡትን ቃል ማክበር፣ ቅን የመሆን፣ ከማታለል አስገድዶ ከመጠቀም፣ ከሙስና ነፃ የመሆን፣ የመንግስትን የስራ ጊዜ፣ መገልገያና ሀብት ለግል ጥቅም አለማዋልን፣ ሌላውን ሰው ወይም መስሪያ ቤት ለመጠቀም ስጦታ ወይም መስተንግዶ መቀበል እንደማይገባ ይገልጻል፡፡
15. **<u>ሕጋዊ በሆነ ስልጣን መገልገል</u>** የሚል መርህ የመንግስት ሰራተኞች ሕግ ከሚፈቅድላቸው ውጪ በስልጣን አለመገልገልን፣ በማስገደድ ሌሎች ሰዎች ጥቅም እንደሰጧቸው መጠየቅ እንደሌለባቸው፣ ሕግንና ደንብን መሰረት በማድረግ ፍትሃዊና ሚዛናዊ የሆነ ውሳኔ መስጠት እንዳለባቸው ያካትታል፡፡
16. **<u>ለህዝብ ጥቅም መስራት</u>** የሚለው መርህ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛና ሀላፊ የሕዝቡን ጥቅም ብቻ እንጂ የግላቸውን፣ የቤተሰባቸውን ወይም የወዳጆቻቸውን ወይም የሌላ ሰውን ወይም ቡድንን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆን እንደሌለበት፣ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከስራው ጋር ሊጋጩ የሚችሉ ጥቅሞቹን የማሳወቅና የራሱን እንዲሁም የቤተሰቡን የፋይናንስና ሌሎች የግል ጥቅሞቹን የማስመዝገብ ግዴታ እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡

17. **የህዝብ አገልጋይነት(serving the public)** መርህ ባለጉዳዮችን በጥሞና በማዳመጥ፣ በማክበር እና በትህትና ላቀርቡአቸው አቤቱታዎች ወይም ለሌሎች ጥያቄዎቻቸው በወቅቱ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ መስጠትን ያመለክታል።
18. **አርአያነት (examplary)**አርአያ መሆንን ከፍተኛ የሆነ የሙያ ብቃትን ፣የሙያ ማንነትን መዳበርን፣ ተግባብቶ መስራትን ያመለክታል።

መወያያ ጥያቄዎች

ሰልጣኞች በቡድን በመሆን በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርጉ

1. ከዳኞች የሚጠበቁ ሙያዊ ስነምግባሮችን በዝርዝር አስቀምጡ፣
2. ከአቃቤ ህጎች የሚጠበቁ ሙያዊ ስነምግባሮችን በዝርዝር አስቀምጡ፣

የዳኞች የሙያ ሥነምግባር መርሆዎች

2.2.1. የፍ/ቤትን ነጻነት መሻትና ማረጋገጥን በተመለከተ

ከዳኝነት ሥነምግባር መርሆዎች መካከል ቀዳሚነቱን የሚወስደው የዳኝነት ነጻነት ነው።ለህግ የበላይነትና ፍትሀዊ የሆነ የፍትህ ስርአት መኖር የዳኝነት ነጻነት መሰረታዊ ዋስትና ነው። ስለሆነም ዳኞች የዳኝነት ነጻነት በግለሰብ ደረጃም ሆነ በተቋም ደረጃ ተግባራዊ እንዲደረግ መጣር አለባቸው።[17]

የዳኝነት ነጻነትን የራሳቸው ልዩ መብት (Privilege) አድርገው የሚመለከቱ አንዳንድ ዳኞች ሊኖሩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ የዳኝነት ነጻነት ለዳኛው የተሰጠው ልዩ መብት ሳይሆን የዳኝነት ሥልጣንን መያዝ የሚያስከትለው ኃላፊነት ነው። ይህም ኃላፊነት ለአንድ ዳኛ የተሰጠው ዳኛው የዳኝነት ሥራን በታማኝነትና በፍጹም ገለልተኛ በሆነ መልኩ በህጉና በቀረበለት ማስረጃ መሠረት ፍሬ ነገሩን በሚገባ መርምሮ ያለ አንዳች የውጪ ግፊት ወይም ተጽእኖ እና ጣልቃ ገብነት ከውሣኔ እንዲደርስ ነው። የዳኝነት

[17] የባንገሎር የዳንነት ስነምግባር መርሆዎች ሰነድን ይመልከቱ

ነጻነት መሠረታዊ ይዘቱም አንድ ዳኛ ያለ አንዳች ተጽዕኖ የቀረበለትን ጉዳይ በሙሉ ነጻነት እንዲያይና እንዲወስን የሚያደርግ ሲሆን ማንኛውም የውጪ አካል መንግሥትም ሆነ ግፊት የሚያደርጉ ቡድኖች እንዲሁም ግለሰቦች ወይም ሌላ ዳኛም ቢሆን በዳኛው የውሣኔ አሰጣጥ ውስጥ ጣልቃ እንዳይገቡ የሚከለክል ነው፡፡

የዳኝነት ነጻነት በመሠረቱ በአስተሳሰብ ደረጃ እንደ አንድ የአዕምሮ ሁኔታ መኖር የሚገባው ቢሆንም በተቋም ደረጃ ደግሞ የዳኝነት ተቋሙ ከሌሎች አካላት ጋር በሚኖረውና በሚያደርገው ግንኙነት የሚወሰን ነው፡፡ ይህም ማለት ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥራን በሚያከናውኑበት ወቅት ከሌሎች የመንግሥት አካላት ጋሪ ሊኖራቸው የሚገባው ግንኙነት ነጻነታቸውንና በፍርድ ሥራ ሊጎናጸፉ የሚገባቸውን ገለልተኝነት ታሳቢ ያደረገ መሆን ይገባዋል፡፡ ፍርድ ቤት ተቋማዊ ነጻነት ከሌለው የዳኛው የግል ነጻነት የቱንም ያህል ቢኖር እንኳን የፍ/ቤቱን ነጻና ገለልተኛነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባው ነው፡፡ ምክንያቱም ፍ/ቤቱ እንደ ተቋም ነጻ ካልሆነ የዳኝነት ሥራን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለማከናወን ከሚያስፈልጉት ቁም ነገሮች ውስጥ አንደኛውን ያጣ በመሆኑ ነው፡፡

የዳኝነት ነጻነትን የሚያረጋግጡ ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች የዳኝነት ነጻነትን ለማጎልበት በራሳቸው እንደ አንድ በጎ ርምጃ ቢታዩም ብቻቸውን ግን ጠንካራና ነጻ የዳኝነት አካል ይፈጥራል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ የዳኝነት ተቋሙ ዳኞች በየወቅቱ የሚመጡና የሚያልፉ መንግሥታት ታማኝ አገልጋይ እንዳልሆኑና ከዚህ ባለፈ መልኩ የህገ መንግሥታዊ ሥርዓትና የህብረተሰቡ ታማኝ አገልጋይ መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በባንግሎር መርሆዎች ላይ የተጠቀሰው አንድ ጽሑፍ የያዝነውን ጉዳይ በሚገባ ስለሚያብራራው እንዳለ በእንግሊዘኛው አገላለጽ ለመጥቀስ እንወዳለን፡፡

> They see governments come like water and go with the wind. They owe no loyalty to ministers, not even the temporary loyalty, which civil servants owe. Judges are also lions under the throne but that seat is occupied in their eyes not by the prime Minister but

by the law and to that conception that they own allegiance. In that lies their strength and their weakness, their value and their threat.[18]

ይህም ማለት ዳኞች በየወቅቱ ከሚቀያየሩና ከንፋስ ጋር ለሚሄዱ መንግሥታት ሳይሆን ታማኝነታቸው ለሕግና ለሕዝብ ጥቅም መሆን አለበት፡፡ ይህንን በማድረግ ወይም ባለማድረግ ነው ጥንካሬያቸው አሊያም ድክመታቸው የሚለካው፡፡

አንድ የዳኝነት ተቋም ነጻነቱ የሚለካው የዳኞች የሹመት ሥርዓትን፣ የሥራ ዘመናቸውን፣ የአገልግሎት ሁኔታን፣ ከውጪ ተጽኖ የሚጠብቁ ዋስትናዎች መኖርን ፣ እንዲሁም ፍ/ቤቱ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ የመታየቱን ጉዳይ በመመልከት ነው፡፡

የዳኝነት ነጻነትን ከማስከበር አንጻር ከዳኛው ምን አይነት ስነምግባራዊ ደረጃ ይጠበቃል?

1. ዳኛ ለሚሰጠው ውሳኔ በፍሬነገር በቀረበው ማስረጃና በህግ ላይ ብቻ ተመስርቶ መወሰን አለበት፡፡ ይህ መሰረታዊ የሆነው የስነምግባር መለኪያው ነው፡፡ የዳኝነት ነጻነት ማረጋገጫውም ይህ ነው፡፡ ህገመንግስት አንቀጽ 79 (3) ዳኛ በህግ መሰረት ብቻ ይወስናል ይላል፡፡ አንድ ዳኛ የዳኝነት ሥራውን በፍጹም ነጻነት የቀረበለትን ክርክር ፍሬ ነገር በህጉ አንጻር ብቻ በመመዘን ያለ አንዳች ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ ውጪያዊ ተጽኖ፣ ማባበያ፣ ግፊት፣ ማስፈራሪያ ወይም ጣልቃ ገብነት ሳይበገር በህጉ አግባብ መወሰን ይኖርበታል፡፡ ከውጪ የሚመጡ ተጽኖዎች በምንም መልኩ የዳኛው ውሣኔ ላይ አሻራ ሊኖራቸው አይገባም፡፡ ይህ የሚሆን ከሆነ ግን ህብረተሰቡ በዳኝነት ተቋሙ ገለልተኝነት ዙሪያ ያለው እምነት ስለሚሸረሸር የፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ፍትሃዊነት ከጥርጣሬ ይገባል፡፡ ስለዚህም ዳኞች የፍ/ቤት ውሣኔዎች በውጪያዊ ተጽእኖ የሚቃኙ መስለው ለህብረተሰቡ እንዳይታዩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ በራሱ ህብረተሰቡ በፍትህ ሥርዓት ላይ እምነት እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ የዳኝነት አካሉን ነጻነትም ለማጠናከር የራሱ የሆነ በጎ ጎን አለው፡፡ ይህ ማለት ዳኞች ለተለያየ ተጽእኖ አይጋለጡም ማለት አይደለም፡፡ ቢሆንም የዳኞች

---

[18] J.A.G.Griffith, The Politics of the Judiciary,3rd ed.,1985,p.199 as quoted in the commentary on Banglore Principles on Judicial Conduct.

ግዴታ ግን ህግን በአግባቡ ከቀረበላቸው የክርክር ጭብጥ አንጻር አመዛዝኖ ያለ አንዳች አድሎና ፍርሃት ወይም ውሣኔው ሰፊ ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል ብለው ሳይሰጉ መወሰን መቻል ነው፡፡ ዳኞች ከህብረተሰቡ ውዳሴ ለማግኘት ወይም ትችት እንዳይደርስባቸው በመስጋት ውሣኔዎችን ሊወስኑ አይገባም፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሚዲያ አማካይነት ዳኞች በያዟቸው ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ የሆነ ክርክር ሊነሳ ይችላል፡፡ እነዚህ የሕዝብ ግፊቶችም አንዳንዴ ወደ አንድ ዓይነት ውሣኔ እንድንደርስ የሚገፋፉን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ዳኛው በፍርድ አሰጣጥ ሂደት ከነዚህ የሕዝብ ግፊቶችና አስተያየቶች ራሱን በማግለል በነጻነት መወሰን ይገባዋል፡፡ ከዚህ በላይ የተገለጸው ነገር እንደተጠበቀ ሆኖ አንድን የውጭ ድርጊት እንደተጽእኖ ወይም ግፊት ለመቁጠር ዳኛው በሚገባ የነገሩን ሁኔታ በማመዛዘን መለየት አለበት፡፡ ይህም ማለት በአንድ በኩል የዳኝነት ሥራን ከአላስፈላጊ ተጽኖዎች የመጠበቅ እና በሌላ በኩል ደግሞ በህብረተሰባዊ ጉዳዮች ላይ መንግሥትም ሆነ ፕሬሱ እንዲሁም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ትችት ሊያቀርቡ እንደሚችሉና ዴሞክራሲያዊ ባህልም ይህንን እንደሚፈቅድ ዳኛው ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህም ዳኞች በሕግ አግባብ በውሣኔያቸው ይዘት፣ በሰጡዋቸው ምክንያቶች ዙሪያ እንዲሁም በውሣኔ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ትችት ቢቀርብባቸው እንደተጽእኖ ሊቆጥሩት አይገባም፡፡

2. በዳኞች ላይ የሚመጡ አንዳንዶቹ የግፊት ዓይነቶች የዕዝ ሰንሰለታቸውን ጠብቀው ህጋዊ ሊመስል በሚችልና በሚያሳስት መልኩ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም ዳኞች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ተደጋጋሚ ተጽእኖ የመፍጠር ሙከራዎች ከተደረጉበት ዳኛው ለተገቢው አካል ሪፖርት ማድረግ ይገባዋል፡፡
3. ዳኛው ባጠቃላይ ከህብረተሰቡና በተለይ ደግሞ ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ገለልተኝነቱን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ግንኙነት መመስረት የለበትም፡፡ በርግጥ እንዲህ ሲባል ከህብረተሰቡ ሙሉ በሙሉ ተነጥሎ ገዳም ውስጥ መኖር አለበት ማለት አይደለም፡፡ ዳኛው ከጓደኞቹ፣ ከስራ ባልደረቦቹና ከሚዲያ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ለተለያዩ አመለካከቶች የሚጋለጥበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህ ደግሞ ዳኛው ከህብረተሰቡ ዘንድ ያለውን ነገር እንዲረዳ፣ እንዲያውቅና እንዲላመዳቸው እንዲሁም ከነርሱ ጋር አብሮ እንዲኖር ይጠይቃሉ፡፡ ዳኞች

የተለያዩ አጨቃጫቂ ማህበራዊና የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን እንዲወስኑ ይጠየቃሉ፡፡ ዳኛው ከማህበረሰቡ ተገልሎ በሚኖርበት ጊዜ የሕዝብ ጥቅምም ሆነ የዳኘው የግል ስብእና ዕድገት ይጠበቃል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ የተለያዩ የሕግ ድንጋጌዎችም ዳኛው የአንድ ምክንያታዊ ሰው አስተሳሰብን ከግምት በማስገባት ውሣኔዎችን እንዲሰጥ ይጠይቃሉ፡፡ በዛሬው አለም ከማህበረሰቡ የተገለለ ዳኛ በፍርድ ሥራ ላይ ውጤታማ እንዲሆን፣ የቀረበለትን ፍሬ ነገር መርምሮ ጭብጡን በማውጣት ወደ ውሳኔ ለሚደረግ ጉዞ ዳኛው ልምዱንና በልምድ የዳበረ ስሜቱን (common sense and experience) በመጠቀም ለቀረበለት ክርክር እልባት መስጠት ይገባዋል፡፡ ስለዚህም ዳኛው ተገቢ በሆነ ደረጃ ከህብረተሰቡ ሳይርቅ የዳኝነት ተግባሩን ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ይሁንና አንድ ክርክር በሚያጋጥምበት ጊዜ ዳኛው አግባብነት ከሌላቸው አድሎአዊ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች ነጻ መሆን ይኖርበታል፡፡ በተለይም ፍትሃዊና ገለልተኛ የሆነ ፍርድ እንዳይሰጥ እክል የሚፈጥሩበትን ግንኙነቶች፣ አድሎአዊ አስተሳሰቦችና አመለካከቶችን መጠንቀቅ አለበት፡፡ ከዚህ አንጻር ተከራካሪ ወገኖች በግል ለመገናኘት የሚያቀርቡለትን ጥያቄ፣

1. በተቻለ መጠን ከመቀበል መቆጠብ፣
2. መቀበል አስፈላጊ መስሎ ከታየው ዳኛው ከመገናኘቱ በፊት የግንኙነቱ አላማ ምን እንደሆነ መጠየቅና ማጣራት፣
3. ዳኛው በግንኙነቱ ጊዜ በክርክሩ ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች (አቃቤ ህግ፣ ጠበቃው) እንዲገኙ ማድረግ፣

ይኖርበታል፡፡

የዳኝነት አካሉ ነጻ መሆን ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ነጻ መሆኑ በሌሎች ዘንድም ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድን የዳኝነት ተቋም ነጻ ሊያሰኙ የሚችሉ መሠረታዊ ነጥቦችን ያሟላ መሆኑ በሌሎችም ሊታመን ይገባል፡፡ በእርግጥ የዳኝነት ነጻነት በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ወይም ዋስትናዎች ላይ የተመሰረተና የፍ/ቤትን ነጻነት አስመልክቶ ያለ አዕምሮአዊ ሁኔታን የሚመለከት ቢሆንም አንድ የዳኝነት ተቋም ነጻ ነው ወይስ አይደለም ብሎ ለማለት ዋናው ቁም ነገር ምክንያታዊ የሆኑ ሌሎች ተመልካቾች በዚህ ረገድ ያላቸው እይታ ወይም ምልከታ ነው ሊባል

ይችላል፡፡ የዳኝነት ነጻነት መኖሩ ብቻ ሳይሆን የዳኝነት ነጻነት እንዳለ ህብረተሰቡ ሊያምነ ይገባል፡፡ ስለሆነም ህብረተሰቡ በዳኝነት ነጻነት መኖር ላይ ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ እንዲያሳድር በር ከሚከፍቱ ባህርዮች ዳኛው እራሱን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ዳኛው ከህግ አውጪውና ከሥራ አስፈጻሚው አካል ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት መመስረት የለበትም፣ ከነዚህ አካላት ተጽእኖ የሚደረግበት መስሎ መታየትም አይኖርበትም፡፡ ሁሉም የመንግሥት አካላት በተለይም የሥራ አስፈጻሚው ክፍል ህገመንግሥታዊ ድንጋጌዎችንና በአለም አቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች የተረጋገጡትን መብቶች አክብሮ መንቀሳቀሱን ፍ/ቤቶች ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ ፍ/ቤቶች ነጻ መሆን ይገባቸዋል የሚለውም እነዚህን ወሳኝነት ያላቸውን ኃላፊነቶች በተገቢው ሁኔታ መወጣት ይችሉ ዘንድ ነው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ የዳኝነት ነጻነት የዳኝነት አካሉ ያለ አንዳች ተጽኖና አድሎአዊነት ተግባሩን እንዲያከናውን ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ዳኛው ምን እንዲያደርግ ይጠበቃል?

1. አንዳንድ ጊዜ የህግ አውጪው ወይም የህግ አስፈጻሚው ከፍተኛ ባለስልጣኖች በፍርድ ቤት ስለተያዘ አንድ ጉዳይ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ወይም ለመወያየት ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ አንድ የህግ አውጪው ወይም የህግ አስፈጻሚው ከፍተኛ የሆነ ባለስልጣን በፍርድ ቤት የተያዘውን ጉዳይ የሚከታተሉት መሆኑን፣ በጉዳዩ ላይ ፍትሀዊ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚፈልጉ መሆኑን፣ ጉዳዩ በቶሎ እንዲያልቅ የሚፈልጉ መሆኑን የሚገልጽ ጽሁፍ ቢልኩለት ዳኛው ምን ማድረግ አለበት? በአግባቡ ይህ በዳኝነት ነጻነት ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት መሆኑን መግለጽ ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመዝገቡ ውስጥ ስላሉ ዝርዝር ጉዳዮች ወይም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው መቼ እንደሚሆን ሊገልጽ አይገባውም፡፡ ይህንን ያደረገ ከሆነ ግን ፍርድ ቤቱ ነጻ አይደለም የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ ለመፍጠር በር ይከፍታል፡፡
2. የዳኛው የትዳር ጓደኛ (ባል/ሚስት) በፖለቲካ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ዳኛው በዚህ ምክንያት የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊ ተደርጎ ሊታይ ይችላል፡፡ ይሁንና ፖለቲከኛ የሆነ የትዳር ጓደኛ ሊኖር አይገባም አይባልም፡፡ ነገር ግን በምክንያታዊ ሰው እይታ የዳኛውን ነጻነት ጥርጣሬ ውስጥ ከሚያስገቡ ተግባራቶች መራቅ አለበት፡፡ ከዚህ አንጻር የባንግሎር የዳኝነት ስነምግባር መርሆዎች ዳኛው የሚከተሉትን እንዲያደርግ ይመክራል፡፡ 1) የትዳር ጓደኛው በሚያደርገው ስብሰባዎች ከመገኘት እራሱን ማግለል 2) በተቻለ መጠን

በመኖሪያ ቤቱ ስብሰባ እንዳይደረግ ማድረግ 3) በመኖሪያ ቤቱ ስብሰባ የሚደረግ ከሆነም እራሱ ከዚያ ውጭ መሆን 4) ለአንድ የፖለቲካ ፖርቲ/ አጀንዳ መዋጮ ከማዋጣት መቆጠብ ወይም ከመቀስቀስ መቆጠብ፡፡ ይሁንና የተወካዮች ምክር ቤት ሲከፈት በሚኖረው ስነስርአት ላይ ከትዳር ጓደኛ ጋር በስነስርአቱ ላይ መገኘትን አይከለክልም፡፡

3. የዳኝነት ሥራን በሚያከናውንበት ጊዜ ዳኛው ከሥራ ባልደረቦቹ ሊደርስበት ከሚችለው ተጽኖ ነጻ በመሆን የዳኝነት ውሣኔን በፍፁም ነጻነት መስጠት ይኖርበታል፡፡ የዳኝነት ተግባር ከሌሎች ተጽእኖ ነጻ መሆንና በራስ ህሊና መመራትን የሚጠይቅ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ለዚህም ነው የዳኝነት ነጻነት የፍ/ቤቶችን ተቋማዊ ነጻነት ብቻ ሳይሆን ዳኞችም ከባልደረቦቻቸው ሊደርስ ከሚችል ማንኛውም ተጽኖ ተጠብቀው በህጉና በህሊናቸው ብቻ በመመራት መወሰን እንደሚኖርባቸው የሚያስቀምጠው፡፡ በሌላ አነጋገር የዳኝነት ነጻነት ከውጪ ሊመጣ ከሚችል ተጽኖ ፍ/ቤትን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ከውስጥ ሊመጣ ከሚችል ማንኛውም ግፊትም ቢሆን ዳኞች ነጻ መሆን አለባቸው፡፡ በተለይም ዳኞች በአንድ ችሎት ላይ ተሰይመው የሚሰሩ እንኳን ቢሆን አንዱ በሌላኛው ተጽእኖ ሥር ፈጽሞውኑ መውደቅ የለበትም፡፡ አንድ ዳኛ የዳኝነት ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቀጣሪ አድርጎ ራሱን በመውሰድ ከተቋሙ ኃላፊዎች ትዕዛዝ መጠበቅ የለበትም፡፡ በፍ/ቤቶች ዘንድ ያለው አደረጃጀት ተጠሪነት ላይ ያልተመሰረተና ዳኛው በያዘውና በቀረበለት ጉዳይ ላይ ራሱ የመጨረሻ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን ያለው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ከዚህም የተነሳ የበላይ አካል አመራር ጠባቂነት ሊታይበት አይገባም፡፡ በባንግሎር የዳኝነት ሥነምግባር ሀተታ ዘምክንያት ላይ ከዚህ በታች የሰፈረው አስተያየት ሁኔታውን በሚገባ የሚያብራራው ስለሆነ እንደሚከተለው እናስቀምጠዋለን፡፡

It is axiomatic that, apart from any system of appeal, a judge deciding a case does not act on any order or instruction of a third party inside or outside the judiciary. Any hierarchical organization of the judiciary and any difference in grade or rank shall, In no way,

interfere with the right of a judge to pronounce the judgment freely, uninfluenced by extrinsic considerations or influences.[19]

4. ዳኞች ውሳኔያቸው ይግባኝ ቀርቦበት የሚሻር ካልሆነ በስተቀር በዳኝነት በያዙት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የማድረግ ስልጣን ያላቸው መሆኑና በፍ/ቤቶች አካባቢ ያለው አወቃቀር ከይግባኝ መስማት ባለፈ መልኩ የዳኝነት ውሳኔን በበላይ ትዕዛዝ መፈፀምን እንደማይጨምር ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ዳኞች በያዙት ጉዳይ ፍሬ ነገር ላይ ሪፖርት ከማቅረብና መልስ ከመስጠት የመቆጠብ መብት አላቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ነፃነታቸው አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ አንድ ዳኛ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በውሳኔው ላይ ምክንያት እንዲሰጥ ከሚጠይቅ በስተቀር ለሌሎች የፍ/ቤት አባላት እንኳን ቢሆን ስለ ያዘው ጉዳይ ዝርዝር ፍሬ ነገር/Merit pf the case/ሪፓርት የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡ ይሁን እንጂ ዳኛው ከወሰነው ውሳኔ ጋር በተያያዘ በዲሲኘሊን የሚያስጠይቅ ከሆነ በዚህን ጊዜ ዳኛው ስለሰጠው ውሳኔ ዝርዝር ፍሬ ነገር ጠቅሶ መልስ የሚሰጥበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህም ቢሆን ስለ ጉዳዩ ሪፖርት ማድረግ ሳይሆን ስለቀረበበት የዲሲፒሊን ክስ ወይም ምርመራ መልስ መስጠት ብቻ ነው፡፡
5. ዳኞች የፍ/ቤቶችን ተቋማዊ ነፃነት የሚጠብቁ አሰራሮችና ዋስትናዎች የመጠበቅና የመንከባከብ እንዲሁም የማጠናከር ግዴታ አለባቸው፡፡ ተቋማ የዳኝነት ነፃነትን የሚፈታተኑ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ እነዚህን ሁኔታዎች ለመቀነስ ወይም ለመከላከል ዳኞች ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በርግጥ እንዲህ ሲባል የፍ/ቤቶችን ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራር በመለወጥ ቀልጣፋ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚቀርቡ የማሻሻያ ሃሳቦችን ሁልጊዜ በመቃወም የዳኝነት ነፃነትን ለትንሹም ለትልቁም ማንሳት ይገባቸዋል ማለት አይደለም፡፡ ሆኖም ግን ዳኛው የፍ/ቤትን ነፃነት ለማስከበር ሁሌም ቢሆን ራሱን ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
6. ህብረተሰቡ ስለ ዳኝነት ነፃነት ምንነትና ይዘት እንዲሁም አስፈላጊነት እንዲገነዘብ ማድረግ ለዳኝነት ነጻነት መከበር ወሳኝነት አለው፡፡ በርግጥ የዳኝነት ነፃነት ሰፊ

[19] ዝኒ ከማሁ ገጽ 46

ተቀባይነትና ህገ መንግስታዊ መሰረት ያለው ፅንሰ ሀሳብ ቢሆንም የዳኝነት ነፃነትን እንዲሁም ይህ ነፃነት በዳኝነት ስራ ላይ የሚያስከትለውን እንድምታ ሁሉም ወገን ያውቀዋል ብሎ መደምደም ግን አይቻልም። በመሆኑም ስለ ፍ/ቤቶች ጠቅላላ አሰራርና የዳኝነት ነፃነት ህብረተሰብ እንዲገነዘብ ማድረግ የዳኝነት ተቋሙ ኃላፊነት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። ይህ ካልሆነ ህብረተሰቡ በዳኝነት ተቋሙ ላይ አመኔታ ሊያሳድር አይችልምና። ፍ/ቤቶች ስለ ዳኝነት ነፃነት በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ፈጥረው የህብረተሰቡን ግንዛቤ ካላዳበሩ በስተቀር ይህ ስራ ለሚዲያዎች ብቻ ከተተወ የዳኝነት ነፃነትን ህብረተሰቡ በአግባቡ እንዳይረዳ ሊያደርጉ ይችላሉ። ምክንያቱም ሚዲያዎች ብዙውን ጊዜ የሚያተኩሩት የዳኝነት ነፃነት ዳኞችን ለመከላከል የተወሰደ አቋም አድርገው ስለሚያስተጋቡ ነው። ለዚህም ነው ጉዳዩ ለሚዲያዎች ብቻ ከተተወ ህብረተሰቡ ከዳኝነት ነፃነት አኳያ ሚዛናዊ መረጃና እውቀት ሊያገኝ አይችልም የሚባለው። ስለዚህም ዳኞች የህዝብን ጥቅም ለማራመድ ሲባል ባገኙት መልካም አጋጣሚ ሁሉ የዳኝነት ነፃነት ምንነትንና አስፈላጊነትን ለህብረተሰቡ ለማስገንዘብ የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ማድረግ ይገባቸዋል።

7. ዳኞች ህብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን እምነት እንዲያጠናክር በማድረግ የዳኝነት አካላት ነፃነትን ለማጎልበት ከፍ ያለ ስነ ምግባር ሊኖራቸው ይገባል። ህብረተሰቡ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን የሚደግፈውና የሚቀበለው በዳኞች ስብዕናና ነፃነት(Integrity and independence) ላይ ሙሉ እምነት ሲኖረው ነው። ዳኛው የተሟላ ስብዕና ያለውና ያለ አንዳች አይነት ተፅዕኖ የሚሰራ ነው ብሎ ህብረተሰቡ የሚያምነው ዳኛው በፍ/ቤት መልካም ምግባር ሲያሳይ እንደሆነ አያጠያይቅም። ስለዚህ ዳኛው የፍ/ቤትን ነፃነት ለማጎልበት የመልካም ስነ ምግባር ባለቤት ለመሆን ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

   ዳኛው ከፍ ያለ ወይም መልካም ስነ ምግባር ሊኖረው ይገባል ሲባል ቢያንስ ፍትሃዊ ሊባል የሚችል የዳኝነት ስርዓት አካሄዶችን (Minimum requirements of fair trial) ሊያከብር ይገባል ለማለት ተፈልጎ ነው። በሌላ አነጋገር ዳኛው ጥሩ ምግባር አለው የሚባለው የሚከተሉት መብቶች ለተከራካሪ ወገኖች ሲያከብርና ሲያስፈፅም ነው።

- ስለ ክርክር ሂደቱ አይነትና አላማ በቂ ማስታወቂያ መስጠት፣(adequate notice of the nature and purpose of the proceeding)
- ተከራካሪ ወገኖች የራሳቸውን ክርክር በሚገባ ተዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በቂ እድል መስጠት(be afforded an adequate opportunity to prepare a case)
- ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ክርክርና ክርክራቸውን የሚደግፍ ማስረጃ እንዲያቀርቡ እንዲሁም የቀረበባቸውን ተቃራኒ ክርክርና ማስረጃ በፅሁፍም ሆነ በቃል እንዲያስተባብሉ እድል አለመንፈግ (present arguments and evidence, and meet opposing arguments and evidence , either in writing, orally or by both means)
- በማናቸውም የክርክሩ ሂደት በህግ አማካሪ ወይም በመረጠው ሌሎች ሙያተኞች የመወከልና በቂ የህግ ምክር አገልግሎት የማግኘት መብት ሲከበር፣(consult and be represented by counsel or other qualified persons of his or her choice during all stages of the proceeding)
- ፍ/ቤቱ የሚሰራበትን ቋንቋ የማይችል እንደሆነ በማንኛውም የክርክሩ ሂደት በአስተርጓሚ የመልገል መብት፣(consult an interpreter during all stages of the proceedings, if he or she cannot understand or speak the language used in the court)
- በመብቶች ወይም በግዴታዎቹ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳርፍ ማንኛውም ውሳኔ በግልፅ ችሎት በተከራከረበትና በሚያውቀው ማስረጃ ላይ ብቻ የተመሰረ መሆኑ፣ (have his or her rights or obligations affected only by a decision based solely on evidence known to the parties to proceedings)
- ያለአግባብ ሳይዘገይ የተፋጠነ ውሳኔ የማግኘት በተለይም ስለ አካሄዱ በቂ ማስታወቂያ ደርሶትና ውሳኔውም በበቂ ሁኔታ በምክንያት ተደግፎ የተሰጠ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ፣(have a decision rendered without undue delay and as to which the parties are provided adequate notice there of and the reasons therefore)

- በመጨረሻ የይግባኝ ሰሚ የዳኝነት አካል የታየ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ወደ ሚቀጥለው የዳኝነት እርከን ይግባኝ የመጠየቅ መብት ናቸው፡፡(except in the case of the final appellate court, appeal or seek leave to appeal, decisions to a higher judicial tribunal)

ዳኞች የተከራካሪ ወገኖችን ነፃነቶች ያለ ህግ ውሳኔያት መገደብ የለባቸውም፡፡ በመሆኑም አንድ ዳኛ የአንድ ግለሰብን ነፃነት በህግ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ወይም ስርዓቶች በስተቀር ሊገድብ አይገባም፡፡ ስለዚህም የግለሰቦችን ነፃነት የሚገድቡ የፍ/ቤት ትዕዛዛት ምክንያታዊነታቸው አስፈላጊነታቸው በሚገባ ሳይጤን ሊተላለፉ አይገባም፡፡ በተመሳሳይ መልኩም ቀና ባልሆነ ልቦና ወይም ህጉን ከቸልተኝነት በመነጨ አኳኋን በትክክል በስራ ላይ ባለማዋል ግለሰቦች በፍ/ቤት በተላለፈ የእስራት ትዕዛዝ ምክንያት ነፃነታቸውን እንዲያጡ ከተደረገ ይህ ከዘፈቀዳዊነት የተለየ አካሄድ ሊሆን አይችልም፡፡

ዳኞች የተከሳሾችን መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በሚገባ መከበራቸውንና በህጉ አግባብ መረጋገጣቸውን እርግጠኛ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን በአንቀፅ 14/1/ላይ ፍትሃዊ የዳኝነት ሂደትን/fair trial/ ይተነትናል፡፡ ሁሉም ሰዎች በፍርድ ቤቶችና በዳኝነት አካላት ፊት በእኩልነት ይታያሉ፡፡ የቀረበበት የወንጀልም ሆነ የፍትሃብሄር ክስ በሚወሰንበት ጊዜ ማንኛውም ሰው በህግ በተቋቋመ ፣ ስልጣን ባለው፣ ነፃና ገለልተኛ በሆነ የዳኝነት አካል ዘንድ የመቅረብና አድሎ የሌለበትና ግልፅ የሆነ ዳኝነት የማግኘት መብት አለው፡፡” ይላል፡፡ [20] የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ሰነድ በአንቀፅ 14 ከንዑስ ቁጥር/2-7/ ባለው ድንጋጌ “ አድሎ የሌለበትና ግልፅ የሆነ ዳኝነት” የማግኘት መብት ተግባራዊ የሚደረግበትን አሰራር በዝርዝር አስቀምጦል፡፡ እነዚህ በዝርዝር የተቀመጡ አሰራሮች የተከራካሪዎችን መብቶች በሁሉም የፍርድ ሂደት ከቀድመ ምርመራ አንስቶ እስከ ክስ መሰማትና ዋናው የፍርድ ሂደት ድርስ ባሉት ደረጃዎች በሙሉ ለማስፈፀም የታቀዱ ናቸው፡፡ እነዚህ አሰራሮች በፍርድ ሂደት ውስጥ ቢያንስ ሊያሟሉ የሚገባቸው ቅድመ

[20] የአለምአቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ሰነድ አንቀጽ 14(1) ይመልከቱ፡፡

ሁኔታዎች ወይም አድሎ የሌለበትን ዳኝነት ለመስጠት እንደ ዋስትና የሚያገለግሉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

- ጥፋተኛነት በፍርድ ውሳኔ እስኪረጋገጥ ድረስ ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት፣(the right to be presumed innocent until proved guilty according to law)
- ተከሶ በተቀጣበት ወይም ነፃ በወጣበት ጉዳይ ዳግም ያለመጠየቅ መብት፣(the right not to be tried again for an offence for which he has already been finally convicted or acquitted)
- የተከሰሰበትን ጉዳይ የክስ ምክንያት በሚገባው ቋንቋ ተተርጉሞ ወዲያውኑ እንዲነገረው ያለው መብት፣(the right to be informed promptly and in detail in a language which he understands of the nature and cause of the charge against him)
- በቀረበበት ክስ ላይ መከላከያ ለማቅረብ በቂ ጊዜና ግብዓት የማግኘት መብት፣(the right to have adequate time and facilities for the preparation of his defense)
- ከመረጠው የህግ አማካሪ ጋር ግንኙነት የማድረግ ወይም የመመካከር መብት፣ (the right to communicate with counsel of his own choosing)
- ሳይዘገይ በተፋጠነ ሂደት ፍትህ የማግኘት መብት፣ (the right to be tried without undue delay)
- በተገኘበት የፍርድ ሂደት የመዳኘት መብት፣(the right to be tried in his presence)
- በመረጠው የህግ አማካሪ እየተደገፈ ወይም በራሱ በመከራከር ራስን የመከላከል መብት ወይም የህግ ምክር አገልግሎት ያላገኘ እንደሆነ የህግ አማካሪ የማግኘት መብት እንዳለው የማወቅ መብት፣(the right top defend himself in person or though legal assistance of his own choosing and to be informed , if he does not have legal assistance, of this right)

- ፍትህ ማድረግ ይህንን የሚጠይቅ እንደሆነ በማንኛውም በተከሰሰበት ጉዳይ የመክፈል አቅም የሌለው እንደሆነ በነፃ የህግ አማካሪ የማግኘት መብት፣(the right to have legal assistance assigned to him, in any case where the interests of justice so require, and without payment by him in any such case if he does not have sufficient means to pay for it.)
- የቀረቡበትን ምስክሮች ራሱን ለመከላከል የመጠየቅ መብት(the right to examine, or have examined, the witnesses against him)
- በርሱ ላይ የቀረቡ ምስክሮች በተደመጡበት ሁኔታ በተመሳሳይ መልኩ የመከላከያ ምስክሮች የማቅረብና የማስደመጥ መብት፣(the right to obtain the attendance and examination of witness on his behalf under the same conditions as witnesses against him)
- ፍ/ቤቱ የሚሰራበትን ቋንቋ መረዳት የማይችል እንደሆነ አስተርጓሚ የማግኘት መብት፣ (the right to have assistance of an interpreter if he cannot understand of speak the language used in court)
- በራሱ ላይ እንዲመሰክር ወይም ጥፋተኛነቱን እንዲያምን ያለመገደድ መብት፣(the right not to be compelled to testify against himself or to confess guilt)
- ዕድሜያቸውንና ህዳሴያቸውን ከግምት ባስገባ ስነ ስርዓት ለመዳኘት የወጣት ጥፋተኞች ያላቸው መብት፣(the right of a juvenile person to procedure that takes account of his age and the disability of promoting his rehabilitation)
- ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ በብሄራዊ ህግም በአለም አቀፍ ህግ ወንጀል ተብሎ ባልተደነገገ ድርጊት ያለመከሰስና ጥፋተኛ ያለመሆን መብት፣(the right not to be held guilty of any criminal offence on account of any act of mission which did not constitute a criminal offence , under national or international law , at the time when it was committed)

- በግልፅ ችሎት የመዳኘት መብት፣(the right to a judgment rendered in public)
- የጥፋተኝነት ውሳኔ የተላለፈበት ሰው በጥፋተኛነቱና በተላለፈበት ቅጣት ላይ ወደ ከፍተኛው የዳኝነት እርከን ይግባኝ በማቅረብ ጉዳይ እንደገና እንዲታይለት የማድረግ መብት፣(the right of a person convicted of a crime to have his conviction and sentence reviewed by a higher tribunal according to law)

ከነዚህ መብቶች በተጨማሪ የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ላይ ቅጣትን በተመለከተ የሚከተሉት መብቶች ያላቸው መሆኑና እነዚህንም መብቶች ዳኞች በሚገባ የማስከበር ግዴታ እንዳለባቸው በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ሰነድ አንቀፅ 6/5፣7፣14/7/እና 15 ስር ተደንግጓል፡፡

- ወንጀሉ በተፈፀመበበት ጊዜ ከነበረው የቅጣት መጠን ከበድ ያለ ቅጣት ያለመቀጣት መብት፣(the right not to be imposed a heavier penalty than the one that was applicable at the time when the criminal offence was committed)
- ተከሶ ነፃ በወጣበት ወይም ጥፋተኛ በተባለበት ወንጀል ዳግም ያለመቀጣት መብት፣(the right not to be punished again for an offence for which he already been finally convicted or acquitted)
- ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊና አዋራጅ ቅጣት ያለመቀጣት መብት፣(the right not to be subjected to cruel , inhuman or degrading punishment)
- የሞት ቅጣት ቀሪ ባልተደረገባቸው ሀገራት ለከባድ ወንጀሎች ካልሆነና ድርጊቱ በተፈፀመበበት ወቅት የነበረው ህግ ይህንን ቅጣት የሚደነግግ ካልሆነ በቀር 18 አመት ያልሆናቸው አጥፊዎች በሞት ቅጣት አለመቅጣት፣In those countries which have not yet abolished the death penalty, the right not to be sentenced to death if below 18 years of age, and then only for the most serious

crimes, and if prescribed by the law in force at the time of the commission of the crime

<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>

1. አንዳንድ ጊዜ ለክርክር በቀረበ ጉዳይ ላይ የአካባቢው ህብረተሰብ በጣም ከመዋጡ የተነሳ በግልጽ ምን አይነት ውሳኔ እንዲወሰን እንደሚፈልግ የሚገልጽበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ ለምሳሌ በከተማው በሌብነቱና በጭለማ ሰዎችን በመደብደብ የሚታወቅ ሰው አለ እንበል፡፡ ይህ ሰው በየጊዜው እየተከሰሰ ፍርድ ቤት እየተፈረደበት እስሩን ጨርሶ ሲወጣ ተመልሶ ወደዚያው የዘረፋና የሌብነት ተግባሩ ይሰማራል፡፡ ህብረተሰቡ በዚህ ድርጊቱ ተማሮ በሚያለቅስበት ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ዘረፋ ተፈጽሞ በድርጊቱም ሰው ሞተ፡፡ ድርጊቱን የፈጸመው ይህ ሰው ነው ተብሎ በከተማው ይወራል፡፡ ፖሊስ ምርመራ በመጀመር የምርመራ መዝገብ በማጠናቀር ለአቃቤ ህግ ያቀርባል፡፡ አቃቤ ህጉም በሁኔታው በመደሰት ይህ ህዝብ ከዚህ ወንበዴ መገላገል አለበት ብሎ ክስ ይመሰርታል፡፡ እርስዎ ዳኛ ነዎት፡፡ በዚያው ከተማ ነዋሪ በመሆንዎት እንደማንኛውም ሰው በሰውየው ላይ የሚወራውን ያውቃሉ፡፡ ህብረተሰቡ ዳኝነት ከእርስዎ ይጠብቃል፡፡ በጉዳዩ ላይ ህብረተሰቡ ከሚፈልገው ውጭ ወይም ተቃራኒ ውሳኔ ቢሰጡ ህብረተሰቡ ምን ሊያደርግ እንደሚችል አያውቁም፡፡ ምን ያደርጋሉ? የህዝቡን ተጽእኖ መሰረት አድርገው ይወስናሉ? ህዝቡ ቢጠላኝም ይጥላኝ ብለው ይወስናሉ? እራስዎትን ከጉዳዩ ያገላሉ? እያንዳንዱ አማራጭ ከሚያስከትለው ጥቅምና ጉዳት አንጻር በመተንተን የተሸለው አማራጭ የትኛው እንደሆነ እና ለምን የተሸለ አማራጭ እንደሆነ አብራሩ፡፡
2. ዳኛው የያዘውን ጉዳይ(መንግስት የተከሰሰበት) በሚመለከት የክልሉ ፕሬዚዳንት አማካሪ ፕሬዚዳንቱ ጉዳዩን በሚመለከት አንዳንድ ጉዳዮችን አጣርቼ እንዳቀርብላቸው ስለፈለጉ እስቲ እዚህ መጥተህ እንነጋገር ስላለው ዳኛው መዝገቡን ይዞ ሄዶ አነጋገረው፡፡ በጉዳዩ ላይ አማካሪው ፕሬዚዳንቱ ከሳሹ እያጭበረበረ መሆኑን እናውቃለን፣ ፍርድ ቤቱም ምን እንደሚወስን አይተን እኛም አስፈላጊውን እርምጃ እንወስዳለን ማለታቸውን ይነግረዋል፡፡ ዳኛውም 1) አሁን በዚህ ጉዳይ ላይ በመንግስት ላይ ብፈርድ ምን ሊደርስብኝ እንደሚችል

አላውቅም፡፡ 2) እራሴን ላግል ብዬ መልቀቂያ ብጠይቅ ሰው የመንግስት ተጽእኖ ስለአለበት ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ነጻ አይደለም በማለት በፍርድ ቤቱ ነጻነት ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠር አደርጋለሁ፡፡ 3) የክልሉ የበላይ ሀላፊዎች ለፍርድ ቤት ማስረጃውን ብናቀርብ ሚስጥር እንዳይባክን ተጠንቅቀው ነው እንጂ እውነትም አጭበርባሪ መሆኑን ቢያውቁ ነው በማለት የመንግስት ሀላፊዎች በፈለጉት መልክ ወሰነ፡፡ በዳኛው የቀረበውን ክርክር ላይ ያላችሁ አስተያየት ምንድነው?

3. እርስዎ በዳኝነት በሚሰሩበት ወረዳ አስተዳዳሪ የሆኑት በወረዳው በፍርድ ቤት የአስገድዶ መድፈር ወንጀልን በተመለከተ በፍርድ ቤት ተገቢው ትኩረት ባለመሰጠቱ ምክንያት ወንጀሉ እየተበራከተ ነው፡፡ ስለሆነም በፍርድ ቤት በኩል ምን መደረግ እንዳለበት፣ ራሱን የቻለ ችሎት ማቋቋም ይሁን፣ ከፍተኛ ቅጣት መቅጣት ወይም ሌላ መፍትሄ ለማፈላለግ ምን ማድረግ እንደሚገባን እስቲ እንነጋገርበት በማለት ይገለጽሎታል፡፡ ምን ያደርጋሉ?

4. አንድ ዳኛ በውሳኔ አሰጣጡ እና በቅልጥፍናው ይወደሳል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ማዘጋጃ ቤት እንዲህ አይነት ዳኛን ማበረታታት አለብን በማለት 300 ካሬ ሜትር ቦታ በሽልማት መልክ እንዲሰጠው ይወስናሉ፡፡ ዳኛው ይህንን ሽልማት መቀበል አለበት ወይ?

5. አንድ ዳኛ በከተማው ጉቦኛ እንደሆነ ይወራበታል፡፡ ስለሆነም ዳኛው ላይ ክስ ይመሰረትበታል፡፡ ይሁንና ጉቦ ስለመውሰዱ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ነገር ግን የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማስረጃ ባይኖርም ህብረተሰቡ ጉቦኛ ነው እያለ ማውራቱ የዳኝነት ነጻነትን አደጋ ላይ የጣለው ስለሆነ፣ ሊባረር ይገባል ብሎ ወሰነ፡፡ ይህንን እንዴት ትገመግሙታላችሁ?

6. በአገራችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት አንድ ዳኛ ባል ወይም ሚስት የፖለቲካ ንቁ ተሳታፊ ወይም የፖለቲካ ድርጅት አመራር ቢሆን ፣ ዳኛው የፍርድ ቤቱን ነጻነት ለመጠበቅ፣ እንዲሁም በህብረተሰቡ የዳኝነት ነጻነት ጥርጣሬ ውስጥ እንዳይገባ ምን አይነት ባህርይ ሊያሳይ ይገባል? ምን አይነት ድርጊቶችን ከማድረግ ሊቆጠብ ይገባል?

7. አቶ መርጊያና አቶ በድሩ በአንድ ፍርድ ቤት የሚሰሩ ዳኞች ናቸው፡፡ የሚቀራረቡ ጓደኛሞች ስለሆኑ ምሳ በሚበሉበት ጊዜ አቶ መርጊያ ለአቶ በድሩ

በችሎት ስለያዘው ጉዳይ በዝርዝር ያጫውተዋል፡፡ በመቀጠልም የቀረበውን ማስረጃና ህጉን መሰረት በማድረግ የከሳሽ ክስ ትክክል እንደሆነና ለእሱ እንደሚወስን ይነግረዋል፡፡ አቶ በድሩ በጉዳዩ ላይ አቶ መርጊያ የደረሰበት ድምዳሜ ትክክል እንዳልሆነ እና ተከሳሽ ተጠያቂ ሊሆን እንደማይገባ ይነግረዋል፡፡ በመጨረሻም አቶ መርጊያ የአቶ በድሩን ክርክር በመቀበል በዚሁ መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የአቶ መርጊያ እና የአቶ በድሩን ድርጊት ከሙያ ስነምግባር አንጻር እንዴት ትገመግሙታላችሁ?

በአድሎአዊነት ያለመስራት(Impartiality)

ያለ አድሎ መስራት የዳኝነት ስራን በአግባቡ ለማከናወን ወሳኝ ነው፡፡ ያለአድሎ መስራት ማለት ውሳኔው ከአድሎ የጸዳ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁንም ውሳኔው የሚሰጥበት ሂደትም ከአድሎ የፀዳ መሆን ይገባዋል ማለት ነው፡፡ የዳኝነት አካሉ ከአድሎ በፀዳ ሁኔታ እንዲሰራ ለማድረግ በቀዳሚነት ነፃ የሆነ የዳኝነት ተቋም መኖር አለበት፡፡ የዳኝነነት ነጻነት መኖር ያለ አድሎ ለመስራት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ነፃ ያልሆነ ዳኛ በምንም አይነት ከአድሎአዊነት በፀዳ መልኩ ይሰራል ብሎ መናገር አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁንና አንድ ዳኛ ነፃ ስለሆነ ብቻ ሁሌም ያለ አድሎ ነው የሚሰራው ለማለት አይቻልም፡፡ በነጻነት መስራት ማለትና ያለአድሎ መስራት የተለያዩ እሴቶች ናቸው፡፡ አድሎአዊነት ማለት እውነትን ማፈላለግ ትቶ ወደ አንድ ወገን ያጋደለ አቋም በማራመድ ሌላኛውን ወገን በተዛባ አመለካከት መጉዳት ነው፡፡ የባንግሎር የዳኝነት ስነ ምግባር ህተታ ዘ ምክንያት ሰነድ አድሎአዊነት በሚገባ እንደሚከተለው ገልጾታል፡፡

> Bias or prejudice has been defined as a leaning, inclination, bent or predisposition towards on side or another or a particular result. In its application to judicial proceedings, it represents a predisposition to decide an issue or cause in a certain way which does not leave the judicial mind perfectly open to conviction. Bias is a condition or state of mind, an attitude or point of view, which sways or colors

judgment and renders a judge unable to exercise his or her functions impartially in a particular case.[21]

ይህም በተዛቡ አመለካከቶች በመመራት ፍትሃዊ የሆነ ፍርድ ዳኞች መስጠት እንዳይችሉ የሚያደርግ የአዕምሮ ሁኔታ ማለት ነው ማለት ይቻላል፡፡ አድሎአዊነት ዳኞች ኃላፊነታቸውን በትክክል እንዳይወጡ ከማድረጉም በላይ የህግ የበላይነት እንዳይሰፍን ያደርጋል፡፡

ያለ አድሎ መስራት ከአንድ የዳኝነት አካል የሚጠበቅ መሰረታዊ እሴት ከመሆኑም በላይ የዳኝነት አካሉ ዋነኛ መገለጫ ባህሪይ ነው፡፡ ያለ አድሎ መስራት በተጨባጭ ብቻ አይደለም መታየት የሚገባው፡፡ ይልቁንም የዳኝነት ተቋሙ ያለ አድሎ እንደሚሰራ ሌሎችም መገንዘብ በሚችሉበት ሂሳብ ነው ተግባራዊ መደረግ ያለበት ፡፡ የዳኝነት ተቋሙ ያለ አድሎ የሚሰራ ተቋም አይደለም የሚል አመለካከት ሰዎች ዘንድ ከተስፋፋ ይህ በራሱ በፍ/ቤቶች ላይ ቅሬታ እንዲኖር የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ፍትሃዊነት ህብረተሰቡ እንዲጠራጠርና ብሎም በፍ/ቤቶች ላይ ያለው እምነት እንዲሸረሸር ያደርጋል፡፡ የዚህ አይነቱንም አመለካከት/perception/ የምንለካው በምክንያታዊ ሰው እይታ መሆኑ ልብ ልንል ይገባል፡፡ ማለትም አንድ ምክንያታዊ ነው ተብሎ የሚታሰብ ሰው የዳኝነት ተቋሙ ያለ አድሎ የሚሰራ አይደለም ብሎ እንዲያምን የሚያስገድዱት ሁኔታዎች ካሉ የዳኝነት ተቋሙ ያለ አድሎ ነው የሚሰራው ብሎ በእርግጠኝነት መናገር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች በጭፍን በአድሎ ተሰራ ብለው ፍርድ ቤትን ሊኮንኑ ይችላሉ፡፡ ይህንን መከላከል ወይም ማቆም አይቻልም፡፡ ዋናው ነገር ምክንያታዊ በሆነ ሰው እይታ ፍርድ ቤትን ያለ አድሎ አይሰራም የሚል ጥርጣሬ የሚፈጥር ሁኔታ እንዳይኖር መከላከል ነው፡፡

ያለ አድሎ መስራት የራሱ የሆኑ 2 መለያ ባህሪያት ያሉት እንደሆነ የአውሮፓ ህብረት ፍ/ቤት ያትታል፡፡[22] የመጀመሪያውና ዋንኛው ቁምነገር"subjective impartiality" ሲሆን ይህም ማለት ችሎቱ ላይ የተሰየሙ ዳኞች በግላቸው ከተዛቡና አድሎአዊ ከሆኑ

---

[21] ዝኒ ከማሁ ገጽ 55
[22] ዝኒ ከማሁ ገጽ 53

አመለካከቶች ነፃ መሆን ይገባቸዋል የሚለው ነው፡፡[23] ሁለተኛው ቁምነገር “ objective impartiality of the tribunal” ሲሆን ይህም ማለት አንድ ችሎት ለሌሎችም ሊታይና ግንዛቤ ሊወሰድበት በሚያስችል አኳኋን ከአድሎ የፀዳ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡ ይህም ማለት ያለ አድሎ የሚሰራ መሆኑን ከጥርጣሬ የሚያስገቡ ሁኔታዎችን በማስወገድ እነዚህ ጥርጣሬዎች እንዳይኖሩ ዋስትና የሚሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡ በሌላ አነጋገር ዳኛው በግሉ ከአድሎ የፀዳ አመለካከት ያለው መሆኑ ብቻውን በቂ አይደለም፣ ይልቁንም ዳኛው ከአድሎ የፀዳ መሆኑን ከጥራጣሬ ላይ የሚጥሉ ኩነቶች ካሉ ችሎቱ”objective impartiality” አለው ማለት አይቻልም፡፡ እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ነጥብ የዳኝነት ተቋሙ ከአድሎ ነፃ በሆነ መልኩ መስራት መቻል ህብረተሰቡ በአንድ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ በሚገኝ የዳኝነት አካል ላይ ፅኑ እምነት እንዲኖረው የሚያደርገው ሲሆን የዳኝነት ተቋሙ ከአድሎ ነፃ ሆኖ መስራትን በሚመለከት ምክንያታዊ ጥርጣሬ ላይ ያለ እንደሆነ ግን ይህ ብቻውን በተቋሙ ላይ ህብረተሰቡ ያለውን እምነት ይሸረሽራል፡፡

ዳኞች በፍ/ቤት ውስጥም ሆነ ከፍ/ቤት ውጪ በሚያሳዩዋቸው ባህሪያት የራሳቸውንና የፍ/ቤቶችን ገለልተኝነትና ከአድሎአዊነት የፀዱ መሆንን በሚገባ በሚያረጋግጥ መልኩ ነው መንቀሳቀስ የሚገባቸው፡፡ በተለይም የህብረተሰቡን፣ የሌሎች ህግ ሙያተኞች እንዲሁም የተከራካሪ ወገኖችን እምነት ሊያገኙ በሚያስችላቸው መንገድ ነው የዳኝነት ተግባራቸው ማከናወን ያለባቸው፡፡

ዳኞች በግላቸው የሚመርጡት የህግ አይዲዮሎጂ ወይም ፍልስፍና ሊከተሉ ይችላሉ፡፡ ይህ ምርጫቸው በራሱ አድሎአዊ ናቸው አያሰኝም፡፡ ዳኛው ከቀረበለት ጉዳይ ጭብጥ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የህግና ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ አንዳች አይነት አቋም ወይም አመለካከት የሚያራምድ እንደሆነ ይህ ብቻውን አድሎአዊ ነው አሰኝቶት ያንን ጉዳይ እንዳያይ የሚያደርገው አይሆንም፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ ዳኛው የአስተሳሰብ ነፃነት እስካለው ድረስ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የራሱ የሆነ አስተያየት ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ አስተያየት ግን ከተዛባ አድሎአዊ አመለካከት የተለየ ነው፡፡

[23] ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ማንኛውም ዳኛ አድሎአዊ ከሆኑ ግላዊ አመለካከቶች የፀዳ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡

ዳኞች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ የሚያቀርቧቸው ምክንያቶችና ሀተታዎች የተለየ አቋም በማንፀባረቅ የተፃፉ እንኳን ቢሆን እንደ ተዛባ አመለካከት ሊወሰዱ አይገባም፡፡

አድሎአዊነት በምን ይገለፃል?

1. አድሎአዊነት ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሊገለጽ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ዳኛ በጾታ፣በባህል፣ በዘር ፣በሃይማኖት፣ላይ በመመስረት ተከራካሪ ወገኖች ላይ መድሎን የሚያመለክቱ ቃላት የተጠቀመ እንደሆነ ዳኛው አድሎአዊ ነው ለማለት እንችላለን፡፡
2. ዳኞች በችሎት ላይ የሚያሳዩት ድርጊትና ባህሪይም አድሎአዊነት መኖሩን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ስለዚህም ዳኞች በተቻላቸው መጠን ሁሉ አድሎአዊ መስለው እንዲታዩ ከሚያደርጉዋቸው ባህሪያት መጠንቀቅ ይገባቸዋል፡፡ የሚያሳዩት የአካል እንቅስቃሴም ሆነ ከፊታቸው ላይ የሚነበበው ስሜት አድሎ የሚያደርጉ እንዳይስመስላቸው ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በከሳሽ ወይም በተከሳሽ ወይም ምስክር ክርክር ወይም ምስክርነት ላይ መሳቅ፣ የመሰልቸት ምልክት ማሳየት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ አንዱን ተከራካሪ የሚደግፍ ወይም የማይደግፍ መስሎ መታየት ተከራካሪዎች ከአድሎ የጸዳ ውሳኔ የሚያገኙ ለመሆኑ እንዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል፡፡
3. ዳኛው ግልጽ ያልሆኑለትን ጥያቄዎች መጠየቅ ተገቢና ትክክልም ነው፡፡ ይሁንና ዳኛው የአቃቤ ህጉን ሚና ወይም የጠበቃውን ሚና በሚጫወት በሚመስል መልኩ በክርክሩ ላይ ጥያቄ በመጠየቅ በማፋጠጥ የሚያስቸግር ከሆነና በራሱ ጥያቄ የተገኘውን ውጤት መሰረት አድርጎ የሚወስን ከሆነ ያለአድልዎ ነው የሰራው ለማለት ያስቸግራል፡፡
4. ዳኞች የችሎትን ክብር የማስጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሁሉ ችሎት ተደፍሯል በሚል ሰበብ ለጥቃቅን ስህተቶች ተከራካሪዎችን ወይም ጠበቆቻቸውን መቅጣት የለባቸውም፡፡ በተለይም የእስራት ቅጣትን እንደ መጨረሻ አማራጭ አድርገው ነው መጠቀም የሚገባቸው፡፡ አለበለዚያ የዳኝነት አካሉ ገለልተኝነትና ያለ አድሎ መስራት ከጥርጣሬ ሊገባ ይችላል፡፡ ይህንን ስልጣን ዳኞች ያለአግባብ የሚጠቀሙ እንደሆነ አድሎአዊነታቸውን ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡ ስለዚህም ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የህጉን

መስፈርቶችና ስነስርዓቶች በመከተል ብቻ ነው ይህንን ስልጣን ዳኞች ሊጠቀሙበት የሚገባው፡፡

5. ዳኞች የችሎት ሂደት ማስከበርና የተከራካሪዎችን የመናገር ነፃነት በማክበር የክርክራቸውን ጭብጥ በተገቢ ሁኔታ ለፍ/ቤቱ እንዲያስረዱ በቂ እድል መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም ጠበቆችን ወይም ተከራካሪ ወገኖችን ያለአግባብ ከመዝለፍ፣ ከመገሰፅ ፣አድሎአዊነታቸውን ከሚያመለክቱ አስተያየቶች፣ ከቁጣና ስሜታዊነት ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን ነፃ በማድረግ ፍፁም አድሎአዊነት እንደሌለባቸውና በገለልተኝነት የቀረበላቸውን ጉዳይ ተመልክተው በህጉ ብቻ እንደሚወሰኑ በተጨባጭ በሚያሳዩት ባህሪም ጭምር ማስመስከር ይኖርባቸዋል፡፡ እንደዚሁም የግለሰቦች የግል ባህሪይ በችሎት ላይ በማንሳት ከተያዘው ጉዳይ ጭብጥ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ሳይኖረው ከተከራካሪዎች አንዳቸውን መዝለፍ ወይም መናገር በዳኛው በኩል አድሎአዊ አመለካከት መኖሩን ያሳያል፡፡

6. ከፍ/ቤት ውጪም ቢሆን ዳኞች ከፍተኛ ጥንቃቄ ነው ማድረግ ያለባቸው፡፡ በተለይም ያልሆኑ ቃላትን ከመጠቀም፣ ተገቢ ያልሆኑ ባህሪያት ከማሳየት መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዳኞች በግል ከተከራካሪ ወገኖች፣ ከጠበቆቻቸው፣ ከምስክሮቻቸው፣ ወዘተ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ማድረግ የለባቸውም፡፡ ከነዚህ ወገኖች ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ሁሉ በግልፅ ችሎት ተመዝግቦ የተደረገ መሆን ይገባዋል፡፡ ከማንኛውም ሰው ጋር በሚያደርጉት ማህበራዊ ሆነ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት አድሎ የሚያደርጉ አስመስሎ ከሚያሳያቸው ማናቸውም አይነት እንቅስቃሴ መቆጠብ ይገባቸዋል፡፡

7. ዳኞች ሊቀርብላቸው በሚችል ጉዳይ ላይ ቀድሞ አስተያየት በመስጠት ፍትሃዊ ዳኝነት መኖሩ ከጥርጣሬ ላይ እንዲወድቅ ከሚያደርግ ባህሪይ ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው፡፡ የሚቀርብላቸው ጉዳይ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንዳይታይ የሚያደርጉ አቋሞችን ቀድመው ማራመድ የለባቸውም፡፡ እንደዚሁም አንድን ጉዳይ ወይም ግለሰብን በተመለከተ ቀድሞ አቋም በመያዝ ያ ጉዳይ ከአድሎ ነፃ በሆነ መልኩ መታየት እንዳይችል ከሚያደርጉ ምክንያቶች ራሳቸውን በሚገባ መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ማለት ክርክሩ እነርሱ ጋር ከቀረበ ጊዜ አንስቶ ውሳኔ እስኪያገኝ ድርስ ገለልተኛ ሆነው

መቆየት ይኖርባቸዋል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ በዜና ማሰራጫ ቅድሚያ ተሰጥቶት እየቀረበና ለፍርድ ሊቀርብ በሚችል ጉዳይ ላይ አንድ አቋም በመያዝ አስተያየት መስጠት ወይም አንድ ወንጀል እየተበራከተ በመምጣቱ ይህንን ችግር ለመግታት ዳኞች የዚህ ዓይነት ወንጀል ተፈፅሞ ቢገኝ ከዚህ አመት በታች ላለመቅጣት ተስማምተናል ብለው በአደባባይ ቢናገሩ ይህንን ወንጀል ፈፅመው በሚገኙ ግለሰቦች ላይ አቋም የያዙ መሆናቸውን ስለሚያመለክት አድሎአዊነታቸው ሊያሳይ ይችላል፡፡ ስለዚህም ከዚህ አይነት እንቅስቃሴ ራሳቸውን መገደብ ይገባቸዋል፡፡

8. አንድ ዳኛ በሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ ከተከራካሪ ወገኖች አንደኛው ውሳኔውን በመተቸት ለዳኛው ተቃውሞ ቢፅፍ እንኳን ለዚህ ትችት መልስ መስጠት አይገባም፡፡ የዳኞች ውሳኔ በሚዲያ በሚተችበት ጊዜም ለዚህ በጋዜጣም ሆነ በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች መልስ ለመስጠት መሞከር ተገቢ አይሆንም፡፡ ይልቁኑ ዳኞች አስተያየታቸውን ሁሉ ማስፈር ያለባቸው በውሳኔዎቻቸው ውስጥ ነው፡፡ በውሳኔዎቻቸው ውስጥ ፍርዱን የሰጡበት ምክንያት በግልፅ ማስፈር ስለሚችሉ ከዚህ ውጪ በመጓዝ በውሳኔዎቻቸው ላይ ለሚቀርቡ ትችቶች መልስ ለመስጠት ደፋ ቀና ማለት አይጠበቅባቸውም፡፡ ሆኖም ግን የሚዲያ ሪፖርት የፍርድ ሂደቱንም ሆነ አንድን ውሳኔ ፍሬ ነገሮቹን በማዛባት የተሳሳተ ሪፖርት ያቀረበ እንደሆነ ይህንን ስህተት ለማረም ብቻ ለመገናኛ ብዙሃን ወይም ለጋዜጦች መግለጫ በሬጅስትራር በኩል ወይም እንደ ነገሩ ሁኔታ በፍ/ቤቶች የህዝብ ግንኙነት በኩል ሊላክ ይችላል፡፡ በመሆኑም ለሚዲያ መግለጫዎችን ከመስጠት ዳኞች መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡

9. በጥቅም ግጭት ምክንያት ከጉዳዩ እራስን የማግለል ሁኔታን ለመቀነስ ዳኞች ከኃላፊነታቸው ጋር የማይጣጣሙ የጥቅም ግጭቶች እንዳይፈጠሩ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡ Frequent disqualification may bring public disfavor to the bench and to the judge personally, and impose unreasonable burdens upon the judge’s colleagues. It may be open to the appearance that a litigant can pick and choose the judge who will decide its case and this would be undesirable. It is necessary, therefore, that a judge should organize his or her personal and business affairs to minimize the potential for conflict with judicial

duties.[24] የዳኛው፣ የቤተሰቦቹ ወይም የወዳጆቹን የግል ጥቅም ከያዘው የዳኝነት ኃላፊነት ጋር እንዳይጋጭ የጥቅም ግጭት ሊያስከትሉ የሚችሉ ምክንያቶችን ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት ጥረት ማሳየት ይገባል፡፡ ከዚህም ባሻገር የቤተሰብ አባላቶቹ በርሱ ዳኝነት በመጠቀም ተገቢ ባልሆነ መልኩ ጥቅም እንዳያገኙ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

10. በህግ በተደነገገ ጊዜ አንድ ዳኛ ስለ ራሱ ገቢዎችና የንግድ እንቅስቃሴዎች ለተገቢው አካል የማሳወቅ ግዴታ ሲኖርበት የቤተሰቦቹንም የንግድ እንቅስቃሴ በቅርበት በመከታተል የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡[33] ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ የዳኛው ቤተሰባዊ ፣ ማህበራዊ ወይም ሌሎች ግንኙነቶች የዳኝነት ስራው ላይ ተፅዕኖ እንዳያሳርፉ መጠንቀቅ አለበት፡፡ የዳኛው ፣ቤተሰቦች፣የቅርብ ጓደኞችና የሙያ ባልደረቦች ከዳኛው ጋር ዘወትር የሚያደርጉት ግንኙነት ፣በዳኛውና በነርሱ መካከል ያለውን መተማመን በመጠቀም ተገቢ ያልሆነ ተፅዕኖ በዳኛው ላይ በማድረስ የዳኛነት ስራውን ያለ አድሎ መስራት እንዳይችል ሊያደርጉት ስለሚችሉ ከዚህ አንፃር ዳኛው የዚህ አይነቱን ግንኙነት ሚዛናዊነት መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

11. ዳኛው ተገቢውን ጥንቃቄ ቢያደርግም የጥቅም ግጭት በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ እንደዚህ አይነት ጉዳዮችን ከመመልከት ራሱን ማግለል አለበት፡፡ ዳኛው ራሱ ተከራካሪ በሆነበት ጉዳይ ወይም ከክርክሩ ውጤት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በሚያገኝባቸው ጉዳዮች ላይ ተሰይሞ ዳኛ መሆን አይችልም፡፡ ይህም አንድ ሰው በራሱ ጉዳይ ራሱ ዳኛ መሆን አይገባውም ከሚለው መርህ የመነጨ ነው፡፡

12. አንድ ዳኛ የቤተሰቡ አባል በህግ አማካሪነት አንድን ባለጉዳይ ወክሎ እርሱ በሚያስችልበት ፍርድ ቤት የቀረበ እንደሆነ ወይም በቤተሰቡ አባል ከቀረበው ጉዳይ ጋር አንዳች አይነት የሚያስተሳስረው የጥቅም ግንኙነት ያለው እንደሆነ ጉዳዮን ከማየት ራሱን ማግለል ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም የዳኛው ገለልተኛው ጥርጣሬ ውስጥ ይወድቃልና፡፡ ዳኛው ከጠበቃው ጋር የፍቅር ግንኙነት የመሰረተ እንደሆነ ይህ ጠበቃ የሚያቀርበው ጉዳይ ከሚመለከት ራሱን ማንሳት አለበት፡፡ አንድ ዳኛና አንድ አቃቤ ህግ ወይም ጠበቃ ባለበት አካባቢ

[24] ዝኒ ከማሁ ገጽ 58

ደግሞ ያ ጠበቃ ወይም አቃቤ ህግ የዳኛው የቅርብ ዘመድ እንደሆነ የዳኛው ገለልተኝነት አደጋ ላይ ሊወድቅ ስለሚችል እንደዚህ አይነት ጉዳዮችን ከማየት መቆጠብ ይኖርበታል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ዳኛው የራሱን መኖሪያ ቤት ጠበቃ የሆነ ሰው ባለጉዳዮችን ተቀብሎ እንዲያነጋግርበት መፍቀድ የለበትም፡፡

13. እውነተኛ የጥቅም ግጭት ሲኖር ብቻ ሳይሆን፣ ዳኛው ያለ አድሎ መወሰን አይችልም ተብሎ ምክንያታዊ በሆነ አኳኋን በሚገመትበት ጊዜ እንዲህ አይነት ጉዳዮችን ከማየት ራሱን ማግለል አለበት፡፡ ዳኛው ምንም አይነት ጥቅም ከጉዳዩ አወሳሰን የማያገኝ ከሆነና ከጉዳዮም ጋር የሚያያይዘው አንዳች ነገር ባይኖርም ዳኛው ካሳየው ድርጊት ወይም ከተናገረው ነገር ወይም ካሳየው ጠባይ በመነሳት ያንን ጉዳይ በፍፁም ገለልተኝነት ያለ አድሎ ሊያይ አይችልም ተብሎ በሚታመንበት ጊዜ ዳኛው እንደዚህ አይነቱን ጉዳይ ከማየት ራሱን ማግለል አለበት፡፡ እንደዚህ አይነት ጥርጣሬ በዳኛው ላይ እንዲኖር ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል ለአብነት ያህል ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አንደኛው የዳኛው የልብ ጓደኛ መሆን፣ ወይም ለክርክር የቀረበው ጉዳይ ሳይቀርብ በፊት ዳኛው በአደባባይ አቋሙን መግለጽ፣ ወይም ከተከራካሪ ወገኖች መካከል በአንደኛው ላይ የተዛባ አመለካከት እንዳለው በሚያሳይ መልኩ ዳኛው አስተያየት በችሎትም ሆነ ከፍ/ቤት ዉጪ መስጠት ሊቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ዳኛው ገለልተኝነቱን ከጥያቄ የሚያስገቡ ነጥቦች መኖራቸውን በተረዳ ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዮን ማየት እንዲቀጥልበት ቢፈቅዱለትም እንኳ ጉዳዩን ከመመልከት ራሱን ማግለል ይገባዋል፡፡

14. ዳኛው እንዴት መቼ ነው ራሱን በገለልተኝነት ለማየት ከማይችላቸው ጉዳዮች ራሱን የሚያገለው የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ያለበት ነው፡፡ ዳኛው በገለልተኝነት አንድን ጉዳይ ማየት አልችልም ብሎ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የሚያሳምኑት ነጥቦች ካገኘ/criterion of reasonable apprehension of bias/ ራሱን ማግለል ይኖርበታል፡፡ በርግጥም አንድ ዳኛ በተጨባጭ አድሎአዊነት ይታይበታል ብሎ የርሱን" actual bias" ማሳየት ይከብዳል፡፡ ለዚህም ነው ህጉ አንድ ምራቁን የዋጠ ምክንያታዊ ሰው ዳኛው በገለልተኝነት አንድን ጉዳይ ማየት እንደሚሳነው የሚገምት ከሆነ ዳኛው ራሱን ማግለል ይገባዋል፡፡ ፍትህ ያለ አድሎ በተጨባጭ መስጠት መቻል ብቻ አይደለም

ቁምነገሩ፣ ይልቁንም ፍትህ ያለ አድሎ ይደረጋል ተብሎ መታመንም አለበት። ይህ ካልሆነ ግን የፍትህ አስተዳደሩ ሀቀኝነትና ገለልተኝነት ላይ ዜጎች እምነት መጣል አይችሉም። ለህግ ልዕልናም ያላቸው ከበሬታ ይቀንሳል።

መወያያ ጥያቄዎች

1. ዳኞች እንደማንኛውም ሰው ሰብአዊ መብት አላቸው። የራሳቸውን እምነት የመከተል፣ የራሳቸውን ሀሳብ የመግለጽ መብት አላቸው። አንድ ዳኛ ሴቶች ከወንዶች እኩል አይደሉም፣ ሴቶች ከወንዶች እኩል ማሰብ አይችሉም፣ ሴቶች አይታመኑም የሚል አመለካከት ሊኖረው ይችላል። ይህ የኔ አመለካከት ነው አመለካከቴን የመግለጽ ህገመንግስታዊ መብቴ ነው በማለት ሀሳቡን ከጓደኞቹ ጋር ሲገናኝም፣ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥም ይገልጻል። ዳኛው ይህ መብቱ ነው ወይ? ለምን? ይህ መብቱ አይደለም ከዚህ አይነት ባህርይ መቆጠብ አለበት የሚባል ከሆነ ለምን?
2. አንተ ዳኛ ነህ። በምትኖርበት አካባቢ ጎረቤትህ የሆነው ሰው ተከሶ ቀረበ። ከጎረቤትህ ጋር ብዙም ቅርርብ የለህም። ይሁንና ተከራካሪው አንተ ከዳኝነት ወንበር እንድትነሳ ጥያቄ አቀረበ። ይህ ጥያቄ ምን ያህል ተቀባይነት አለው?

የፍርድ ስራን በሀቀኝነት ስለማከናወን (Integrity)

ዳኞች የዳኝነት ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ በሀቀኝነት ላይ መመስረት ይኖርባቸዋል።[25] የፍርድ ስራን በሀቀኝነት ለመምራት ዳኛው የተሟላ ስብዕና ያለው መሆን አለበት።

ዳኛው በፍርድ ቤት ብቻ ሳይሆን ከፍርድ ቤት ውጭም በግል ህይወቱ ከማጭበርበር፣ ውሸታም ከመሆንና ከመሳሰሉት ማንነቱን ዝቅ ከሚያደርጉ ተግባራት እራሱን ማራቅ አለበት። ዳኛው በአደባባይ የሚያወግዘውን ነገር እርሱ በግል ሕይወቱ በድብቅ የሚያደርገው ከሆነ ግብዝ ይባላል። ስለሆነም ህብረተሰቡ በፍርድ ቤት ላይ ያለውን

[25] ዝኒ ከማሁ ገጽ 72-77 ይመልከቱ

እምነት ይሸረሽረዋል፡፡ ስለሆነም የዳኛው የግል ህይወት በዳኝነት ስራው ከሚበይነው ፍትህ ጋር የሚጋጭ መሆን የለበትም፡፡

በርግጥ ከዳኛ የሚፈለገው ስብዕና እንዲህ ነው ወይም እንዲያ ነው ብሎ በዝርዝር ማስቀመጥ ይከብዳል፡፡ የእያንዳንዱ ዳኛ ድርጊትና ባህሪይ በህብረተሰቡ እየተመዘነ ተቀባይነት ሊያገኝ ወይም ሊያጣ ይችላል፡፡ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው የዳኛው ባህሪይ ወይም ድርጊት እንደ ትክክለኛ ስብዕና ተቀባይነት ያጣው ባህርይ ወይም ድርጊት ግን ይህንን ስብዕና የሚያጎድፍ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በመሰረቱ የተሟላ ሰብእና ጉዳይ ከአንድ ሀይማኖት ወይም የሞራል አስተሳሰብ ጋር የሚጣጣም ወይም የሚጋጭ መሆኑ አይደለም፡፡ ወይም በአብዛኛው ህብረተሰብ ተቀባይነት ያገኘ ነገርን መተግበር ወይም አለመተግበር አይደለም፡፡ ይሁንና የፈጸመው ድርጊት ዳኛው በዳኝነት ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ፍትሀዊ፣ነጻና ህጉን ያከበረ ዳኝነት ሊሰጥ አይችልም የሚያስብለው ነው ወይ? ከሚል አንጻር መታየት ያለበት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ዳኛው በግል ህይወቱ ከሚፈጽመው ተግባር አንጻር ህብረተሰቡ ዳኝነት ለመስጠት ይችላል ወይም አይችልም የሚል ግምት ማሳደሩ ነው፡፡ የሚከተሉት የዳኛው ሰብእና የተሟላ ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመለካት እንደመመዘኛ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡[26]

- የዳኛው ድርጊት (ግላዊም ሆነ ከኃላፊነቱ ጋር የተያያዘ) በስራ ላይ ያሉትን ህጎች የሚፃረር መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣/the public or private nature of the act and specifically whether it is contrary to law that is actually enforced/
- ዳኛው ያሳየው ድርጊት ወይም ባህሪይ እንደ ግለሰብ መብት በህግ ጥበቃ የተሰጠው መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣/The extent to which the conduct is protected as an individual right/
- ዳኛው ድርጊቱን በሚፈፅምበት ጊዜ የወሰደው ጥንቃቄ /the degree of discretion and prudence exercised by the judge/

[26] ዝኒ ከማሁ ገጽ 75 ይመልከቱ

- የዳኛው ድርጊት ተፅዕኖ ያሳረፈባቸው ወገኖች በድርጊቱ የተጎዱ እንደሆነ ወይም ሌሎች ምክንያታዊ ሰዎች በነርሱ ቦታ ሆነው ሲመለከቱት ጎጂ ድርጊት ነው ብለው የሚያዩ እንደሆነ/Whether the conduct was specifically harm full to those most closely involved or reasonably offensive to others/
- ዳኛው ያሳየው ባህሪይ ወይም የፈፀመው ድርጊት ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ ለህብረተሰቡ አባል ምን ያህል ክብር እንደሚሰጥ ወይም እንደማይሰጥ የሚያመለክት እንደሆነ/the degree of respect or lack of respect for the public or individual members of the public that the conduct demonstrates/
- ዳኛው ያሳየው ባህሪይ ምን ያህል ተገቢ ባልሆነ ተፅዕኖ፣ በተዛባ አመለካከትና በአድሎ እንደሰራ የሚያመለክት ከሆነ/the degree to which the conduct is indicative of bias, prejudice, or improper influence/

እነዚህን መስፈርቶች በመጠቀም የዳኛው ባህሪይ ህብረተሰቡ በሚፈለግበትና በሚቀበለው አቅጣጫ የተገራ መሆኑን መለካት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የዳኛው ግለሰባዊ መብቶችም ከተሸከመው የዳኝነት ኃላፊነት አንፃር ተግባራዊ የሚደረግበት ሚዛን በነዚህ መስፈርቶች ሂሳብ ማስላት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣

1. ዳኛው በችሎት ላይ ጭምት፣ አድማጭ፣ ትዕግስተኛ፣ ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች እኩል እድል የሚሰጥ፣ በሚሰጣቸው ብይኖችና ትዕዛዞች ላይ ህጋዊ ምክንያቶችን የሚያሰፍር፣ የግራ ቀኙን ክርክርና የምስክሮች ቃል በተሟላ መልኩ ተከታትሎ በትጋት የሚመዘግብ፣ በፍርድ ሂደት የመዘገባቸውንና በችሎት ላይ የተናገራቸውን ነገሮች የሚፃረር ነገር በፍርድ ውስጥ የማይፅፍ፣ በጥቅሉ የፍርድ ሂደቱን በሀቀኝነትና በፍትሃዊነት የሚመራ መሆን ይኖርበታል፡፡ በወሰናቸው ጉዳዮች ላይ ይግባኝ የተጠየቀም ቢሆን ወደ ይግባኝ ሰሚ ዳኞች ወይም ፍርድ ቤት በመደወል ያልሆነ ተፅእኖ ለመፍጠርና የራሱን አቋም ለማራመድ መሞከር የለበትም፡፡
2. ዳኞች በፍርድ ሂደትም ሆነ ከዚያ ውጪ ለህግ ፍፁም ተገዢና ህግ አክባሪ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ዳኞች በግል ህይወታቸው ከሀሰትና ከማጭበርበር ራሳቸውን በሚገባ ጠብቀው ጥሩ ስነ ምግባር ሊያሳዩ ይገባል፡፡ ዳኞች ህግን

ራሳቸው የሚፃረሩ ከሆነ የዳኝነት ተቋሙን ለህግ መከበር መቆም ግምት ውስጥ ያስጥላሉ፡፡ ዜጎች ለህግ ተገዢ እንዳይሆኑ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም ባጠቃላይ ህብረተሰቡ በፍ/ቤቶች ላይ ፅኑ እምነት እንዳይኖረው ያደርጋሉ፡፡

3. አንዳንድ ጊዜ ዳኛው መሰረታዊ የሰብአዊ መብትንና ሰብአዊ ክብርን የሚጥሱ ህጎችን መሰረት አድርጎ የመወሰን አጣብቂኝ ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ እንዲህ ባለጊዜ እራሱን ከዳኝነት ሀላፊነት በማግለል ለፍትህና ለሰብአዊነት ያለውን ታማኝነት ማሳየት አለበት፡፡ ምክንያቱም ዳኞች ወደዚህ ኃላፊነት በሚመጡበት ጊዜ " ለፍትህና እውነት" መከበር እንቆማለን ብለውና ምለው ነው፡፡ ፍትህና እውነት ደግሞ የህግ የበላይነትና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተመሰረተባቸው ፅንሰ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ለነዚህም እሴቶችም ዳኞች በፅኑ መቆም የሚችሉት ለህግ መከበር ፍፁም ታማኝ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡

4. አንድ ዳኛ አብሮት የሚሰራ ሌላ ዳኛ ከሙያው ስነምግባር ውጪ የዳኝነት ሥራን በትጋት የማከናወን ኃላፊነት ወደ ጐን በመተው ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊት መፈፀሙን ያወቀ እንደሆነ ተገቢውን ርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ ተገቢ ርምጃ የሚባለው ለዳኛው ምክር መለገስን ወይም እንደ ነገሩ ክብደትና ሁኔታ ለሚመለከተው አካል ማስታወቅን ያጠቃልላል፡፡

<u>*መወያያ ጥያቄዎች*</u>

1. ፍርድ ቤት መከበር አለበት ሲባል ምን ማለት ነው? ፍርድ ቤትን እንዲፈራ የሚያደርገው ምን አይነት የዳኛ ባህርይ ነው? ፍርድ ቤት እንዳይፈራ ነገርግን እንዲከበር ዳኛ ምን ማድረግ አለበት?
2. የዳኝነት ስራ ከሌሎች ስራዎች ሁሉ ከፍ ያለ ሰብእናንና ሀቀኝነትን ስለሚጠይቅ ሰብእናቸውን ዝቅ ከሚያደርግ ተግባር መቆጠብ አለባቸው ይባላል፡፡ በዚህ አስተያየት ትስማማላችሁ ወይ? ለምን?
3. አንድ ዳኛ በሀቀኝነት ሊያከናውናቸው የሚገባ የግል ባህርያትና ድርጊቶችን አንስታችሁ ተወያዩበት፡፡ የዳኛውን ሰብእናና ሀቀኝነት ላይ ጥርጣሬ ሊፈጥሩ የሚችሉ ባህርያቶችን አንስታችሁ ተወያዩበት፡፡ እንዴትስ ሊወገዱ ይችላሉ? የሚለውንም አንስታችሁ ተወያዩበት፡፡

2.2.4. ቅንነት (PROPRIETY)

ዳኞች የዳኝነት ስራን በሚያከናውኑበት ጊዜ ለገቡት ቃል ታማኝ በመሆን በፍፁም ቅንነት ማገልገል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በዋነኛነት ዳኞች ቅንነታቸውን ከጥርጣሬ ከሚጥሉ ተገቢነት የሌላቸው ድርጊቶች መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡ የቅነነት መለኪያም አንድ ምክንያታዊ ሰው የዳኛውን ባህሪይ በማጤን ዳኛው ኃላፊነቱን በነፃነት፣ በትጋት፣ ያለ አድሎና በፍፁም ሀቀኝነት ሊያከናውን ይችላል ወይም አይችልም ብሎ በሚያስቀምጠው አስተያየት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ዳኛ ከባለጉዳዮች መካከል አንድን ባለስልጣን በተለየ ሁኔታ ያስተናገደ እንደሆነ ቅንነት የጎደለው ባህሪይ አሳይቷል ማለት ነው፡፡[27] ከዚህ አንጻር የሚከተሉት ነጥቦች እንደመለኪያ ሊታዩ ይችላሉ፡፡

1. ዳኞች ስራቸውን በሚያከናውኑበት፣ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ በኃላፊነታቸው ምክንያት የሚጣልባቸውን የስነ ምግባር ግዴታዎች በሙሉ ፈቃደኝነት በመቀበል ሊያጎለብቷቸውና ተግባራዊ ሊያደርጓቸው ይገባል፡፡ እነዚህ ገደቦች ከከፍተኛ ኃላፊነታቸው የመነጨ መሆኑንም መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ዳኞች የህብረተሰቡ ዋልታዎች ተደርገው የሚቆጠሩ በመሆናቸው ከፍተኛ ስነ ምግባር የማሳየትና ባጠቃላይ ለህብረተሰቡ በመልካም ምግባራቸው ምሳሌዎች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ የዳኝነት ክብርን ዝቅ ከሚያደርጉ ስፍራዎችና ድርጊቶች መቆጠብ አለባቸው፡፡ በተለይም አዘወትረው በመጠጥ ቤቶች፣ የቁማር ስፍራ መገኘትን በሚገባ ማጤንና ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡[28]
2. ዳኛው በሚያስችልበት ፍ/ቤት አዘውትረው የሚቀርቡና ጉዳይ ካላቸው ጠበቆች ወይም የህግ ባለሙያዎች ጋር ዳኛው ተገቢ ያልሆነና ለአድሎአዊነት በር የሚከፍት ግንኙነት ከማድረግ መቆጠብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት ዳኞች ባጠቃላይ ከሌሎች የህግ ሙያተኞች ጋር ግንኙነት እንዳያደርጉ የሚከለክል ሳይሆን ግንኙነቱ በጥንቃቄ እየተፈሸ የዳኞችን ገለልተኝነት ከጥራጣሬ በማይከት መልኩ ሊሆን ይገባል ለማለት ተፈልጎ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ

[27] ዝኒ ከማሁ ገጽ 80
[28] ዝኒ ከማሁ ገጽ 81-82

ዳኛ በጠበቆች ወይም በህግ ሙያተኞች በተዘጋጀ የግብዣ ኘሮግራም ላይ ሊሳተፍ ይችላል፡፡ ነገር ግን በያዘው ጉዳይ ላይ ውይይት እንዳይካሄድ ተገቢውን ጥንቃቄ ዳኛው ሊወስድ ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዳኛው እርሱ ዘንድ ጉዳይ ይዘው ከሚቀርቡ ጠበቆች ላይ ምንም አይነት ስጦታ መቀበል የለበትም፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን አዘወትረው ከሚቀርቡ ተከራካሪዎች ጋርም ከልክ ያለፈ ማህበራዊ ግንኙነት መመስረት አይኖርበትም፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር ዳኞች ከባለጉዳዮች፣ ከጠበቆችና ከሌሎች የመንግስት ባለስልጣናት ጋር በሚፈጥሩት ግንኙነት የዳኝነት ኃላፊነታቸውን በገለልተኝነት በሀቀኝነት ከማከናወን እንዳያደናቅፋቸው ከፍ ያለ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ዳኞች በተቻላቸው መጠን ሁሉ ተገቢ ያልሆኑ ግንኙነቶች ከሌሎች ጋር ከማድረግ መቆጠብ ይገባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ከሌሎች ጋር ከመጠን ያለፈ ግንኙነት በማድረግ ለአላስፈላጊ ተፅዕኖ ሊጋለጡ ይችላሉና፡፡ ለምሳሌ አንድ ዳኛ አዘወትሮ በጠበቆች የግል መኪና የሚጠቀም፣ ወይም ከፖሊሶች ጋር ግንኙነት የሚያዘወትር ከሆነ፣ ወይም ከባለጉዳዮች ጋር በነርሱ መኪና በተደጋጋሚ ሁኔታ የሚጓጓዝ እንደሆነ፣ እነዚህ ድርጊቶች ተገቢ ያልሆኑና የዳኛውን ገለልተኝነት የሚፈታተኑ ናቸው፡፡ ስለዚህ ዳኞች በስነምግባራቸው ከፍ ያለ ጠባይን በማሳየት በቅንነት በመስራት ለህብረተሰቡ አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

3. ዳኞች እንደ ሌሎች ዜጎች ሁሉ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ፣የመደራጀትና የመሰብሰብ መሰረታዊ መብቶች አሏቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን መብቶች በሚጠቀሙበት ጊዜ የዳኝነት ስራቸው ዝቅ እንዳያረግ፣ ገለልተኝነታቸውንና ነፃነታቸውን እንዳያደናቅፍ ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዳኞች በህዝባዊ ውይይቶች በሚሳተፉበት ወቅት አንደኛ ተሳትፏቸው በገለልታኝነታቸው ላይ አሉታዊ ገፅታ እንዳይፈጥር በሌላ በኩል ደግሞ የዳኛውን ፖለቲካዊ ወገንተኝነት እንዳያመለክት ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር ዳኞች በህዝባዊ መድረኮች አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መከራከርም ሆነ አስተያየታቸውን መስጠት አይገባቸውም፡፡ በዚህ ረገድ ዳኞች ቁጥብነትን ማሳየት የሚገባቸው ሲሆን ህግን ለማሻሻል ወይም የፍትህ አስተዳደርን በተመለከተ በሚጠሩ ህዝባዊ ውይይቶች ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡

4. ዳኞች የዳኝነት ስልጣናቸውን በተገቢ መልኩ ለህዝብ ጥቅም ብቻ ነው ሊገለገሉበት የሚገባው፡፡ የዳኝነት ስልጣናቸውን የግል ጥቅሞቻቸውን ለማራመድ ወይም ሌሎችን ለመጉዳት ሊጠቀሙበት አይገባም፡፡ ምንም ጊዜ ቢሆን ዳኞች ስልጣናቸውን በዘፈቀደ የግል ጥቅሞቻቸውን ለማራመድ ወይም በአድሎአዊነት ነው የሚጠቀሙበት ተብሎ እንዳይወሰድ ጥርጣሬ የሚፈጥሩ ነገሮችን ሁሉ ለማስወገድ ብርቱ ጥረት ማሳየት አለባቸው፡፡ ዳኞች ስልጣናቸውን ያለ አግባብ ይጠቀሙበታል የሚል አመለካከት በህብረተሰቡ ዘንድ ከተንሰራፋ የፍ/ቤቶች ተዓማኒነት አደጋ ላይ መውደቁ አይቀርም፡፡ አንድ ዳኛ የራሱን የግል ጥቅም ወይም የቤተሰቦቹን ጥቅም ለማስጠበቅ የዳኝነት ስልጣኑንና ክብሩን ያለአግባብ ሊጠቀምበት አይችልም፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን የዳኛውን ስልጣን መከታ በማድረግ ጥቅም ማግኘት የሚፈልጉ የቤተሰቦቹን አባላት በሚገባ በመከታተልና መከላከል ይኖርበታል፡፡ ማንም ሰው ከዳኛው ጋር ባለው ቅርበት ምክንያት ዳኛው ላይ ተገቢ ያልሆነ ተፅእኖ መፍጠር እንደሚችል አድርጎ ሌሎችን እንዳይቀርብና እንዳይሳሳት ዳኛው ሁሌም ቢሆን ነቅቶ መጠበቅ አለበት፡፡ የዳኝነት ስልጣኑን ተገቢ ያልሆነ የግል ጥቅሙን ለማራመድ መጠቀም የለበትም ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ምሳሌ ወስደን እንመልከት፡፡ ለምሳሌ ዳኛው የግል ቢዝነሱን በሚያካሄድበት ወቅት የዳኝነት መንበሩን በመጠቀም በፍርድ ቤቱ ደብዳቤ በመጠቀም መልዕክቶችን መለዋወጥ የለበትም፣ አገልግሎት ፍለጋ የሆነ ቦታ ሄዶ ከቢሮክራሲያዊ አሰራሮች በማምለጥ በፍጥነት ለመስተናገድ ሲል ዳኛ መሆኑን በመግለፅ በተለየ ሁኔታ እንዲስተናገድ መጠየቅ የለበትም፡፡ በርግጥ ዳኛው ዳኝነቱን ይደብቅ ለማለት ተፈልጎ ሳይሆን የዳኝነት መንበሩን ያለአግባብ የግል ጥቅሙን ለማስጠበቅ መጠቀም የለበትም ነው፡፡ ለምሳሌ የዳኛው፣ልጁ ወይም ባለቤቱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ቢታሰር ዳኝነቱን በመጠቀም እነዚህ ሰዎች ከሌላው የተለየ መስተንግዶ ተደርጎላቸው እንዲፈቱ ወይም ጉዳያቸው በትኩረት እንዲታይ ግፊት መፍጠር የለበትም፡፡

5. አንድ ዳኛ ለሌሎች ሰዎች የድጋፍ ደብዳቤ ሊፅፍላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ረገድ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የዳኝነት ኃላፊነቱ የተጎናፀፈውን ክብር በመጠቀም ሌሎች ሰዎች በርሱ የድጋፍ ደብዳቤ

ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንዳያገኙ ነው ፡፡ በተለይም በቅርበት ለማያውቃቸው ሰዎች የድጋፍ ደብዳቤ መፃፍ የለበትም፡፡ በርሱ ኃላፊነት ስር ለሚሰሩ የፍ/ቤት ሰራተኞች ወይም በቅርበት ለሚያውቃቸው ሰዎች ግን መፃፍ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ዳኛ በንግድ ሬዲዮ ወይም ቴሌቭዥን ላይ ማስታወቂያ ለመስራት ወይም የአንድን ድርጅት ለማስተዋወቅ መቅረብ የለበትም፡፡ ምክንያቱም በርሱ የዳኝነት ክብር ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ሊገኝ ይችላልና፡፡

6. የፍ/ቤት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የቀጠሮ ፋይል ለማውጣት መጥሪያ ለመስጠት፣ የማስረጃ ወይም የፍርድ ግልባጭ ለመስጠት ፣እንዲሁም ትዕዛዞችን በፍጥነት ወጪ ለማድረግ ከባለጉዳዮች የማይገባቸውን ክፍያ እንዳይጠይቁ ዳኞች ተገቢውን ጥንቃቄና ክትትል ማድረግ የሚገባቸው እንደሆነ መዘንጋት የለባቸውም፡፡ እነዚህን አግባብነት የሌላቸውን ጥቅሞች የፍ/ቤት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ከባለጉዳዮች ሲጠየቁ ህገ ወጥ መሆኑን ተረድተው ክፍያውን እንዳይፈፅሙና እንዲህ አይነቱን በደል በሚያደርሱባቸው ሰራተኞች ላይ አቤቱት የሚያቀርቡበትን ስርዓት ማስቀመጥና ሚስጠራዊነቱም እንደሚጠበቅ በመግለፅ ባለጉዳዮችን ማበረታታት አለባቸው፡፡ የኢንስፔክሽን ስርዓት በመዘርጋት እንዲሁም የፍርድ ቤት ተጠቃሚዎች በፍ/ቤት አገልግሎት ላይ ያላቸውን ቅሬታ የሚገልፁበት የአቤቱታና ቅሬታ በግልፅ በመደንገግ ጉቦኝነትን መዋጋት የዳኝነት ስራ የሚጠይቀው የስነ ምግባር ግዴታ ነው፡፡

7. ዳኞች በስራ አጋጣሚ ያወቁትን ሚስጥር ለዳኝነት ስራቸው አስፈላጊ ካልሆነ በቀር በማናቸውም ሌሎች ሁኔታዎች ሊጠቀሙበት አይችሉም፡፡ እነዚህ ሚስጥሮችም አሳልፈው መስጠትና መግለፅ አይችሉም፡፡[29] ዳኞች በስራቸው ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የንግድ ሚስጥሮች ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ እነዚህን የንግድ ሚስጥሮች ለግል ጥቅማቸው ማዋልም ሆነ ለሌላ ሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት አይገባቸውም፡፡

8. የዳኝነት ኃላፊነቱን በሚገባ ከተወጣ በኋላ አንድ ዳኛ ከዳኝነት ስራው በተጨማሪ ህግን በማስተማር፣ ህግ በመፃፍ፣ የፍትህ አስተዳደርን ለማሻሻል

[29] ዝኒ ከማሁ ገጽ 97

የታቀዱ ተግባራት ላይ ሊሳተፍ ይችላል።[30] ዳኛው በተለይም ህብረተሰቡ ስለ ህግ እንዲገነዘብ የሚረዱ ትምህርቶች በመስጠት፣ ፅሁፎችን በማዘጋጀት ላይ መሳተፉ ለፍትህ ስርዓቱን ለፍትህ አስተዳደሩ መጎልበት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ስላለው የሚበረታታ ጉዳይ ነው። በህግ ትምህርት ቤቶች ዳኞች፣ በማስተማር በሴሚናሮች ላይ በመሳተፍ፣ የህትመት ውጤቶችን በማዘጋጀት ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። በማስተማር ፣በሴሚናሮች ላይ በመሳተፍ፣ የህትመት ውጤቶች በማዘጋጀት ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። ሆኖም ግን በፅሁፎቹ ላይም ሆነው በሚያስተምረው ትምህርት ላይ ዳኛው የሚያንፀባርቀው አቋም በዳኝነት ስራውም ላይ የሚከተለው አቋም እንደሆነ መግለፅ ይገባዋል።

9. በመጨረሻ አንድ ዳኛ ከዳኝነት ኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ከርሱ አንዳች አይነት ተግባር እንዲፈፅም ወይም ሳይፈፅም እንዲቀር ለማድረግ የርሱ የቤተሰብ አባላት ምንም አይነት ስጦታ ወይም ብድር እንዳይወስዱ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል። በተመሳሳይ መልኩ በርሱ ስር የሚገኙ የፍ/ቤት ሰራተኞችም እንደዚህ አይነቱን ጥቅም በዳኛው ስም እንዳይጠይቁ ወይም እንዳይወስዱ ዳኛው ሁሌም ቢሆን ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

<u>*መወያያ ጥያቄዎች*</u>

1. ዳኛ ብዙ ግንኙነትና ጓደኛ የሚያፈራ ከሆነ በተለያየ መልኩ ለተለያዩ ተጽእኖዎች ሊጋለጥ ስለሚችል ማህበራዊ ግንኙነቱ የተወሰነ መሆን አለበት ይባላል። በዚህ ሀሳብ ላይ ምን አስተያየት አላችሁ?
2. በአንድ ክልል ያለ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ በአካባቢው ከአሉ ነጋዴዎች ጋር እቁብ አለው። በየወሩ ይገናኛሉ። ቢራ ወይም ድራፍት ጠጥተው እቁባቸውን ጥለው ይለያያሉ። ይህ የዳኛው ድርጊት ተገቢ ነው ወይ?
3. ዳኛው ለመዝናናት ከረንቦላ ወይም ፑል ቤት ያዘወትራል። ይህ ተገቢ ድርጊተት ነው ወይ?
4. ከበደና ዳኛቸው በትምህርት ቤት በጣም የቅርብ ጓደኛሞች ናቸው። ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላም የቅርብ ጓደኝነታቸው ቀጥሏል። ይሁንና ከበደ ዳኛ ሆኖ

---

[30] ዝኒ ከማሁ ገጽ 98

ሲሾም፣ ጓደኛው የፍትህ ቢሮ ሀላፊ ይሆናል። ዳኛው ከቅርብ ጓደኛው ጋር ያለውን ግንኙነት ይቀንስ? እርስዎ ቢሆኑ ምን ያደርጋሉ?

5. ዳኛው ምግብ ሊበላ በገባበት ቤት ውስጥ ምግብ አዞ ከበላ በኋላ ተከፍሏል የሚል ምላሽ ተሰጠው። ዳኛው ምን ማድረግ አለበት?
6. ዳኛው ወቅታዊ በሆኑ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ ያለውን አስተያየት ይገልጻል። የሚደግፈው የፖለቲካ ድርጅት በጠራው ስብሰባ ላይ ተገኝቷል። በአንዳንድ ወገኖች አስተያየት ዳኛው ይህንን በማድረጉ ገለልተኛ እንዳልሆነ ይቆጠራል። ስለሆነም ከእንደዚህ አይነት ድርጊት ራሱን ማራቅ አለበት ይላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ድርጅት ፓርቲ አባል እስካልሆነ ድረስ ይህ መብቱ ነው ገለልተኛ እንዳልሆነ አያስቆጥረውም በሚል መልኩ ክርክር ይቀርባል። እናንተ ክርክሮቹን እንዴት ትገመግማላችሁ?
7. አቶ ከበደ የተባለው ዳኛ የፖለቲካ ድርጅት አመራር ከሆነው ጓደኛው ጋር ሁልጊዜ በፖለቲካ ጉዳይ ላይ ይወያያሉ። ጓደኛሞች ይሁኑ እንጂ አቶ ከበደ ከጓደኛው ጋር በፖለቲካ አቋማቸው አይስማሙም። ዳኛው በፖለቲካ ጉዳይ ከፖለቲካ ድርጅት አመራር ጋር ክርክር ማድረጉ ተገቢ ነው ወይ?
8. አንድ የተወካዮች ምክር ቤት አባል ምስክርነት ተጠርተው ፍርድ ቤት ሲገቡ ዳኛው ከሌሎች ምስክሮች ለየት ባለ መልኩ አቀባበል አደረጉላቸው። በዚህ ምክንያት ዳኛው ከሌላው ምስክር በተለየ አቀባበል ማድረግህ ትክክል አይደለም ተብሎ ክስ ተመሰረተባቸው። እሳቸው ግን የተወካዮች ምክር ቤት አባል ናቸው። ከበስተጀርባቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ይወክላሉ። ስለሆነም አክብሮቴ ለህዝቡ እንጂ ለእሳቸው አይደለም በማለት ይመልሳሉ። ምን አስተያየት አለዎት?
9. ዳኛው ስራ ከለቀቀ በኋላ ወዲያውኑ ስራ ከመልቀቁ በፊት እሱ በሚያስችለው ችሎት ውስጥ ክርክር ሲያደርግ ከነበረ ድርጅት ውስጥ ተቀጠረ። ይህ ተገቢ ነው ወይ? ተገቢ አይደለም ከተባለ ስራውን ከለቀቀ በኋላ እስከስራ ድረስ በዳኝነት ተቋሙ ላይ ምን ጉዳት ያመጣል?
10. ዳኛው የራሱን መኖሪያ ቤት እሱ በሚያስችልበት ፍርድ ቤት ለሚከራከር ጠበቃ ያከራያል። ጠበቃው ይዞት በሚከራከረው ጉዳይ ላይም ችሎት ተቀምጦ

ይወስናል፡፡ ዳኛው ቤቱን ለጠበቃ ማከራየቱ ተገቢ ነው አይደለም? ጠበቃው ችሎት በሚከራከርበት ጊዜ እራሱን ማግለል ይገባው ነበር ወይስ አይገባውም?

11. አንድ ዳኛ አንድን ጉዳይ በቅንነት እንዳያይ የሚያደርጉ ከዚህም የተነሳ ከዳኝነት እንዲነሳ የሚያደርጉ ባህርያትን ይግለጹ፡፡

2.2.5. የባለጉዳዮችን መብት በእኩልነት ስለመጠበቅ (Equality)

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 25 ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፡፡ በመካከላቸውም ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሄር፣ ብሄረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት ፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው ይላል፡፡ ዳኞች ይህ በህገመንግስት የተቀመጠውን የእኩልነት መርህ ተግባራዊ የማድረግ ህገመንግስታዊ ሀላፊነት አለባቸው፡፡

ዳኛ በፍርድ ቤት የሚቀርቡትን ተከራካሪዎች ሁሉ በእኩልነት ማየትና መብታቸውን በእኩልነት መጠበቅ የዳኝነት ሥራ በትክክል እንዲከናወን ወሳኝ ነው፡፡[31] በዚህ ረገድ ዳኞች መድሎን አጥብቀው የሚያወግዙና የሚከለክሉ ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችን በሚገባ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም በዘር ላይ የተመሰረተ አድሎአዊ ልዩነትን ለማስቀረት እ.አ.አ. በ1965 ዓ.ም የተደረገውን ስምምነት፣ በሴቶች ላይ የሚፈፀም አድሎአዊ ልዩነትን ለማስወገድ እ.አ.አ. በ1979 ዓ.ም የተደረገውን ስምምነት፣ በሃይማኖት ወይም በእምነት ላይ የተመሰረተ አለመቻቻልና አድሎአዊ ልዩነትን ለማስቀረት እ.አ.አ. በ1981 ዓ.ም የወጣ መግለጫን፣ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሄር አባላትን፣ ሃይማኖት ተከታዮችን ወይም ቋንቋ ተናጋሪዎችን መብቶች ለመደንገግ እ.አ.አ. በ1992 ዓ.ም የወጣውን መግለጫ በጥልቀት ማወቅና መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዓለምአቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን አንቀጽ 14/1/ ሰዎች ሁሉ በፍርድ ቤቶች ፊት በሕግ እኩል መሆናቸውንና እኩል የመዳኘት መብት እንዳላቸው ማጤን ይኖርባቸዋል፡፡

[31] ዝኒ ከማሁ ገጽ 111

የዓለምአቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን ሰነድ በአንቀፅ 2/1/ እና በአንቀጽ 14/1/ የደነገገውን በጣምራ ስናነብ የሚሰጠን ትርጉም በዘር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ ወይም ሌሎች አመለካከቶች፣ በማህበራዊ አመጣጥ ፣ ወይም በማናቸውም ሌሎች ምክንያቶች በሰዎች መካከል አድሎአዊ ልዩነት በማድረግ በሕግ ፊት እኩል የመዳኘት መብታቸውን ማጥበብ እንደማይቻል ተደንግጓል፡፡ " በሌሎች ምክንያቶች " የሚለው ሀረግ በኤች አይ ቪ፣ በአካል ጉዳት፣ በሀብት ደረጃ፣ ከጋብቻ ውጪ በመውለድ ወዘተ ልዩነት አለማድረግን እንደሚያጠቃልል ተደርጐ ነው በአብዛኛው እየተተረጐመ ያለው፡፡[32] ስለዚህም ዳኞች በተቻላቸው መጠን ሁሉ በተከራካሪዎች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት ሳያደርጉ ሁሉም ወገኖች የበኩላቸውን ክርክር እንዲያሰሙ እኩል እድል በመስጠትና በማዳመጥ ሚዛናዊና ፍትሃዊ የሆነ ውሣኔ ላይ መድረስ ይገባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

1. ዳኞች በችሎት የሚጠቀሙባቸው ቃላት አድሎአዊነትን የሚያንፀባርቁ (stereotyping) እንዳይሆኑ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ክርክር ይዘው ፍትሃዊ ውሣኔ ፍለጋ ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ዓይን በመመልከት ማስተናገድ የሚገባ ሲሆን ሁሉም በሕግ ፊት እኩልና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የመዳኘቱ ጉዳይ ፍትህና ርትዕ የሚጠይቁት ቁምነገር ናቸው፡፡ በርግጥ የባለጉዳዮችን እኩልነት ማክበር የፍትህ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የዳኝነት አካሉ ያለ አድሎ እንዲሰራ አስፈላጊም ጭምር ነው፡፡ ስለዚህም ዳኞች በተቻላቸው መጠን አድሎአዊነትን ከሚያንፀባርቁ አመለካከቶች ራሳቸውን በማራቅ ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች በእኩል ማየትና ማስተናገድ ይገባቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በፆታ ላይ የተመሰረተ ልዩነት ላለማድረግም ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባ ሲሆን የዳኝነት ሂደቱ ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች በእኩል ደረጃ ተደራሽ እንዲሆንና ፍትሃዊነት እንዲኖረው ማስቻል ተገቢነት ያለው ጉዳይ ነው፡፡ ዳኞች ከጠበቆች ፣ ከተከራካሪ ወገኖች እንዲሁም ከፍርድ ቤት ሠራተኞች ጋር በሚያደርጉት ማናቸውም ግንኙነት ይህንኑ በሚገባ ማሳየት ይገባቸዋል፡፡ ለምሳሌ

[32] ዝኒ ከማሁ

በችሎት ላይ የቀረቡ ሴት ጠበቆችን “ የኔ ቆንጆ ” “ እናትዬ ” የመሳሰሉት ብሎ መጥራት ወሲባዊ ትንኮሳን የሚያመለክት ከሚችል ተግባር መቆጠብ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም ለሴቶች ያለን የተዛባ አመለካከት የሚገልፁ ቃላትን ከመጠቀም መቆጠብ ተገቢ ነው፡፡ ለምሣሌ አንድ ዳኛ “ ይህ የክስ ማመልከቻ በሴት የተዘጋጀ መሆን አለበት ” በማለት የማመልከቻውን ይዘት የተቸ እንደሆነ ዳኛው በፆታ ረገድ የተዛባ አመለካከት እንዳለው ሊያመለክት ይችላል፡፡ ስለዚህ ዳኞች በፍርድ ሂደት ላይ በችሎት በሚያሳዩት ጠባይና አነጋገር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

2. ዳኞች በሕብረተሰቡ ውስጥ በዘር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በአካል ጉዳት፣ በእድሜ፣ በጋብቻ፣ በሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ላይ በመመስረት ልዩነቶች መኖራቸውን ማወቅና መረዳት አለባቸው፡፡ እነዚህ ልዩነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ መኖራቸውን ዳኞች ከመረዳት አልፈው በነዚህ ምክንያቶች የተዛባ አመለካከት ይዘው አድሎአዊ ልዩነቶችን መፈፀም የለባቸውም፡፡ በየጊዜው በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን የባህልና የማህበራዊ እሴቶች ለውጥን በመከታተል ማወቅ ተገቢ ሲሆን የተዛባ አመለካከት እንዳይኖርም ጥንቃቄ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ ከላይ በገለፅናቸው ምክንያቶች ዳኞች ልዩነት እንዳያደርጉና ልዩነት የሚያደርጉ መስለው እንዳይታዩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባቸው እንደሆነ ነው፡፡

3. ዳኞች በዳኝነት ሥራቸው ላይ ከተከራካሪዎች በአንዳቸው ላይ ወይም በአንድ በተለየ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ አድሎአዊ ልዩነትን ከሚያደርግ አነጋገር ወይም ተግባር መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ማለት ለአንድ ወገን ተገቢውን ክብር አለመስጠትን የሚያንፀባርቁና የተዛባ አድሎአዊ አመለካከትን የሚያመለክቱ አስተያየቶችን፣ አገላለፆችን፣ ምልክቶችንና ድርጊቶችን መጠቀም ተገቢነት የለውም፡፡ ስለዚህም ዳኞች በዘር፣ በባህል ወይም በሌሎች ምክነያቶች ልዩነት ማድረጋቸውን ከሚያመለክቱ ድርጊቶች መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚሁ ጉን ለጉን ዳኞች የሚጠቀሙባቸው ቃላት ለተከራካራ ወገኖች ፍርድ ቤቱ ክብር የሚሰጥ መሆኑን የሚያመለክቱና የዳኛውን ትህትና የሚያስረዱ መሆን አለባቸው፡፡ ጠበቆችን ፣ ምስክሮችን ፣ ተከራካሪዎችን፣ ወዘተ የሚዘልፉና

የሚያዋርዱ ቃላትን መጠቀም በፍፁም የተከለከለ ነው። ከዚህ አንፃር ጠበቆችም ሆኑ ተከራካሪዎች እንዲህ ዓይነቱን አገላለፅ እንዳይጠቀሙ ዳኞች ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል፣ ተጠቅመው እንኳን ቢገኙ ተገቢነት የሌላቸው አስተያየቶች መሆናቸውንና ፍርድ ቤቱ እንደዚህ ዓይነት የተዛቡ አመለካከቶችን እንደማይቀበልና በዝምታም እንደማያልፈው መግለፅ ተገቢ ነው። ዳኞች በወንጀል ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ሰዎችን በሚቀጡበት ጊዜ እንኳን ለተከሳሹ ተገቢውን ክብር መስጠታቸውን በሚያሳይ መልኩ እንጂ ተከሳሹን በሚያወግዝና በሚያወርድ አገላለፅ መጠቀም አይኖርባቸውም። በርግጥ ተከሳሹ ወንጀል በመፈፀሙ ምክንያት ላደረሰው በደል የሕብረተሰቡን ቁጣ በሚያሳይ መጠን ብቻ መጠነኛ ተግሳፅ ማድረግ የዳኛው ኃላፊነት ቢሆንም ከመጠን ያለፈና አዋራጅ የሆኑ የስድብ ቃላትን መጠቀም ተገቢነት የለውም።

4. ከዚህ በተጨማሪ ዳኞች ለእያንዳንዱ ሰው ማለትም ለሁሉም ተከራካሪዎች፣ምስክሮችና የሕግ አማካሪዎቻቸው ተገቢውን ክብርና እኩል እንክብካቤ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በተለይም የፍርድ ሂደቱ ፍፁም ፍትሃዊና ሁሉንም ወገኖች በእኩልነት አይቶ የሚዳኝ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ነው ዳኞች መስራት የሚጠበቅባቸው። በተከራካሪ ወገኖች መካከል ልዩነት የሚያደርጉ መስለው መታየትም የለባቸውም። ለምሣሌ በችሎት ላይ ለአንደኛው ተከራካሪ ወገን ሃዘኔታን በገጽታም ሆነ በቃላት ማሳየት፣ ለአንደኛው ወገን ረዘም ያለ የመናገር እድል መስጠትና ሌላውን መንፈግ ፣ ለአንደኛው ወገን ንግግር ወይም ሃሳብ ብቻ ትኩረት መደረጉን የሚያሳይ ገጽታ ወይም ድርጊት ማሳየት ወዘተ የዳኛውን አድሎአዊነት ሊያንፀባርቅ ስለሚችል በተቻለ መጠን መወገድ ያለበት ባህርይ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ የሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች አስተያየትና ክርክር በጥሞና ማድመጥና በትኩረት መከታተል የሚያስፈልግ ሲሆን ለሁሉም ወገኖች እኩል ክብር መስጠትም በጣም አስፈላጊ ነው።

5. ዳኞች መድልዎን ከሚያራምዱ ድርጅቶች አባልነት መራቅ አለባቸው። ዳኞች በተለያዩ የግብረ ሰናይ ስራዎች ሊሳተፉ ይችላሉ። ይሁንና፣

1. ገለልተኛ መሆናቸውን ጥያቀ ውስጥ ሊያስገባ በሚችል መልኩ ወይም ከዳኝነት ስራቸው ጋር በሚጋጭ መልኩ መሳተፍ የለባቸውም፡፡
2. ለእንደዚህ አይነት ድርጅቶች ገንዘብ ለማሰባሰብ ከሚደረግ እንቅስቃሴ እራሳቸውን መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. በፍርድቤት ክስ ሊኖረው ይችላል ብለው በሚገምቱት ድርጅት ተሳታፊ ከመሆን መታቀብ ይኖርባቸዋል፡፡

<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ከእኩልነት መርህ ጋር የሚቃረን ዳኛው ከማድረግ ሊቆጠብባቸው የሚገቡ ባህርያትን አንስታችሁ ተወያዩበት፡፡
2. ዳኛው በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች እርዳታ ለማሰባሰብ በጎ አድራጎት ድርጅት መስራች ብቻ ሳይሆን፣ እርዳታ ለማሰባሰብ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር እንዴት ይታያል;

2.2.6. <u>በዳኝነት ስራ ትጋትና ጥረት ማሳየት (due deligence)</u>

1. ዳኛው በዳኝነት ስራው ላይ ተገቢውን ትጋትና ጥረት ማሳየት፣ እንዲሁም ስለህግ ያለውን ዕውቀት ለማዳበር ዘወትር ጥረት ማድረግ አለበት፡፡[33] ዳኛው ማሳየት የሚገባው ጥረትና ትጋት በዕውቀት፣ ክህሎት፣ ጥልቀት ባለው አስተሳሰብና በቂ ዝግጅት የተደገፈ መሆን ይኖርበታል፡፡ የዳኝነት ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ዳኛው በበቂ የህግ ዕውቀት ላይ ተመስርቶ መሆን አለበት፡፡ ዳኛው ለአልኮልና ለተለያዩ ሱሶች የተጋለጠ እንደሆነ የዳኝነት ስራ የሚጠይቀውን ትጋትና ጥረት ማሳየት ሊሳነው ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዳኛው የግል ባህሪይ የተረጋጋ ካልሆነና በቂ ልምድ የሚያንሰው ከሆነ የዳኝነት ስራ የሚጠይቀውን ብቃትና ችሎታ ሊጎድለው ይችላል፡፡
2. ዳኛ የቀረበለት ጉዳይ በፍፁም ጥንቃቄ ማየት፣መመርመርና ያለ አድሎ መወሰን ሲኖርበት ይህም የዳኝነት ብቃት መገለጫ ነው፡፡ እንዲሁም ዳኛው ህጎች በትክክል ተግባራዊ ማድረግ ያለበት ሲሆን በፍርድ ሂደትም ቢሆን የተከራካሪ ወገኖች መብት ሙሉ በሙሉ እንዲከበር የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

---
[33] ዝኒ ከማሁ ገጽ 119

በተለይም የፍርድ ሂደቱ ፍትሃዊና ግልፅ እንዲሁም አግባብነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ በርግጥ የዳኛው ጥረትና ትጋት በተለያዩ ነገሮች ሊወሰን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ዳኛው ከፍተኛ የስራ ጫና ያለበት እንደሆነና ብቃት ባላቸው የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የማይደግፍ እንደሆነ እንዲሁም የዳኝነት ስራውን በተገቢ ሁኔታ ለመምራትና ለማሻሻል በቂ ሀብት ያልተመደበለት እንደሆነ ዞሮ ዞሮ የዳኝነት ስራውን በብቃትና በትጋት ለማከናወን የሚቸገር መሆኑ የሚያጠራጥር ነገር አይደለም፡፡

3. ዳኞች ሁልጊዜም ቢሆን የስራ ሰአትን አክብረው በመገኘት አርአያነት ማሳየት ይገባቸዋል፡፡

4. ዳኞች ስራቸውን በትጋት ማከናወን ይችሉ ዘንድ በቂ ዕረፍት ማግኘት ይገባቸዋል፡፡ የዳኛው ማህበራዊ ህይወትና የቤተሰብ ኃላፊነት ከግምት ገብቶ በአመት ውስጥ በቂ ጊዜ በእረፍት ላይ መቆየት አለበት፡፡ ይህ ዕረፍት ዳኛው በተሻለ ሁኔታ ጤንነቱ እንዲጠበቅና የአዕምሮ ዕረፍት እንዲያገኝ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ዳኛው የራሱን ክህሎትና ዕውቀት የሚያሻሻልበት ጊዜም ያስፈልገዋል፡፡ የዳኝነት ስራ ከፍተኛ ጫናን የሚፈጥር በመሆኑ በዳኞች ላይ ጭንቀት ሊፈጥር እንደሚችል በሌሎች ሀገሮች የተደረጉ ምርምሮች ያሳያሉ፡፡[34] ስለዚህም ዳኞች የምክር አገልግሎት ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡

5. የዳኞች ቀዳሚ ስራ የዳኝነት አገልግሎት በመሆኑ ዳኞች ከየትኛውም ተግባር የዳኝነት ስራቸውን በማስቀደም በከፍተኛ ትጋትና ጥረት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም የሚቀርቡላቸው ክርክሮች በአግባቡ ማስተናገድና ተገቢውን ፍርድ መስጠት የዳኞች ኃላፊነት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ አንድ ዳኛ ሌሎች ኃላፊነቶች በመንግስት ተሰጥቶት ሌላ ስራ እንዲያከናውን ቢመድብም እንኳን በቅድሚያ ከፍ/ቤቱ ኃላፊዎች ጋርና አብሯቸው ከሚሰራቸው ዳኞች ጋር በመመካከር የዳኝነት ስራው ወይም ተግባሩ እንዳይስተጓጎል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ኃላፊነት በመውሰዱ ምክንያት የዳኝነት ስራው የሚስተጓጉል እንደሆነ ዳኛው ሌላ ስራ ከመስራት መቆጠብ አለበት፡፡ ዳኞች በትርፍ ጊዜያቸው ሌሎች ስራዎችን በማከናወን ገቢ የሚያገኙ እንደሆነ ይህ ሁኔታ ተፈታትኗቸው ለመደበኛ ስራቸው ትኩረት እንዲነፍጉ ሊያደርግ

---

[34] ዝኒ ከማሁ

ይችላል፡፡ ከዚህም አልፎ ዳኞች የያዙትን ከፍተኛ ኃላፊነት የህዝብ አገልጋይነት ወደ ጎን ትተው ገቢያቸውን ማዳበር ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ የዳኝነት ስራ የህዝብ አገልጋይነት/community service/ መሆኑን በመገንዘብ ዳኞች በመደበኛ ስራቸው ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫናዎችን ከሚፈጥሩባቸው ሌሎች ስራዎች ራሳቸውን ማግለል ወይም መቆጠብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

6. አንድ ዳኛ ሙያዊ ዕውቀቱን ክህሎቱን ከዳኝነት ስራ በተለይም ውሳኔዎችን ከመስጠት ባሻገር የፍ/ቤቱን የስራ አፈፃፀም ለማሻሻል የሚበጁ ሌሎች ተግባራት ላይም ማዋል ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ማለት ዳኞች ውሳኔ የመስጠት ወይም የፍርድ ስራን በአግባቡ የማከናወን ክህሎትና ችሎታ ብቻ አይደለም የሚያስፈልጋቸው ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፍ/ቤትን ስራ በአግባቡ ለመምራት ብቃትም ሊኀናፀፉ ይገባል፡፡ ይህም ማለት ዳኛው በሚሰራበት ፍ/ቤት ውስጥ የፍትህ አስተዳደር ስራ ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እንዲመራ የማድረግ ተጨማሪ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህ ኃላፊነት የጉዳዮች አመራርን፣ የፋይል አያያዝን ፣የፍ/ቤቱን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ክትትል ማድረግን፣ እንዲሁም የፍ/ቤቱን ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መምራትን ያጠቃልላል፡፡ ዳኛው የያዛቸውን ጉዳዮችን በፍጥነት እንዲያልቁ በትጋት የማይሰራ ከሆነ ጉዳዮች በተንተቱ ቁጥር በፍ/ቤቱ ላይ ተጨማሪ ወጪን ማስከተላቸውና የፍትህ አስተዳደሩን ውጤታማነት ማስተጓጎላቸው አይቀርም፡፡ ስለዚህም ዳኞች የፍትህ አስተዳደር ስራ በአግባቡ እንዲያከናውን እንዲሁም የፍ/ቤት ኃላፊዎች የዳኝነት ስራን በአግባቡ ለመምራት ለሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ የዳኝነት ትጋት የሚጥልባቸው የስነ ምግባር ግዴታ ነው፡፡

7. የፍ/ቤት ፋይሎች በስርዓት እንዲጠብቁና እንዳይጠፉ ዳኞች ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም የፋይል አያያዝ ስርዓቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግ አለባቸው፡፡ ፋይሎች በሚጠፉበት ጊዜም እነዚህ የጠፉ ፋይሎች የሚገኙበትን ስርዓትና ሆነ ተብሎ እንዲጠፉ መደረጉ ከተጠረጠረ ደግሞ ምርመራ የሚካሄድበትን ስርዓት መበጀት አለበት፡፡

8. የፋይል አያያዝ ስርዓትን ኮምፒዩተራይዝ ማድረግ፣ በፍ/ቤት የሚሰጡ አገልግሎቶች እስታንደርድ እንዲኖራቸው በማድረግ የሚፈፀሙበትን ጊዜ ማስቀመጥ የሚያስፈልግ ከመሆኑም በላይ ተጠቃሚው ህብረተሰብ በፍ/ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚያነሳቸውን ቅሬታዎች አስተያየቶች በየወቅቱ በመመርመር ወቅታዊ ምላሽ መስጠት ያሻል፡፡

9. ዳኞች የዳኝነት ስራን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችላቸው ዕውቀት፣ ክህሎትና ጥሩ የግለ ስብዕና ለማዳበርና ለማጎልበት ብርቱ ጥረት ማድረግ የሚገባቸው ሲሆን በተለይም ለዚሁ አላማ በፍ/ቤት የሚዘጋጁ ስልጠናዎች በንቃት መከታተልና ፍ/ቤት የሚያቀርብላቸውን ግብዓቶች እየተጠቀሙ ሙያዊ ብቃታቸውን ለማሻሻል የማያቋርጥ ጥረትና ትጋት ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡[35] በርግጥ ዳኞች ነፃነት ቢኖራቸውም በዚያው ልክ ደግሞ የዳኝነት ስራን በከፍተኛ ስነ ምግባር የማከናወን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ዳኞች ከተጣለባቸው የስነ ምግባር ግዴታዎች መካከል የዳኝነት ስራን በከፍተኛ ሙያዊ ብቃትና ትጋት የማከናወን ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ አይነቱን ከፍተኛ የሙያ ብቃት ለማግኘት ዳኛው በስልጠናዎች ላይ የመሳተፍ ግዴታ እንዳለው ሁሉ ሙያዊ ክህሎቱንና ችሎታውን ለማሻሻልና በየጊዜው እያዳበረ ለመሄድ የሚያጎናፅፋቸው የተለያዩና ጠለቅ ያሉ ስልጠናዎች ጀማሪ የሆኑ ዳኞች የዳኝነት ሙያንና ክህሎትን የሚያጎናፅፋቸው የተለያዩና ጠለቅ ያሉ ስልጠናዎች የማግኘት መብት አላቸው፡፡ እነዚህ ስልጠናዎችም በመሰረታዊ የስነ ስርዓት ህጎች ላይ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ ህግን ተግባራዊ ማድረግ በህብረተሰቡ ህይወት ላይ የሚኖረው ተፅእኖ ጭምር ዳኞች በሚገባ አውቀው የህብረተሰቡን ችግሮች ከግምት ያስገቡ ውሳኔዎችን መስጠት የሚያስችላቸው መሆን ይገባዋል፡፡ በዚህ ረገድ የባንግሎር የዳኝነት ስነምግባር ሃተታ በምክንያት ሰነድ ላይ የሰፈረውን እንመልከት፡፡ እንዲህ ይነበባል፡-

   The trust that citizens place in the judicial system will be strengthened if a judge has a depth and diversity of knowledge which extends beyond the technical field of law to areas of important social concern, as well as courtroom and personal

---
[35] ዝኒ ከማሁ ገጽ 123

skills and understanding enabling the judge to manage cases and deal with all persons involved appropriately and with sensitivity.

ከዚህ አስተያየት እንደምንረዳው የዳኞች ዕውቀት ቴክኒካዊ የሕግ ዕውቀት ያለፈ መሆን ይኖርበታል። በተለይም ዳኞች ወሳኝ የሆኑ ማህበራዊ ጉዳዩች ላይ ሰፋ ያለ ዕውቀትና መረጃ ሊኖራቸው እንደሚገባ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ከዚህም አልፎ የችሎት አመራር፣ የተለያዩ ባለጉዳዮችን እንደየጠባያቸው የመረዳትና የማዳመጥ፣ እንዲሁም የጉዳዮች አመራር ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል። እነዚህን ክህሎቶች እንዲጨብጡም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ስልጠናዎችን ማግኘት አለባቸው። ከዚህ አኳያ ስለ አንዳንድ ወቅታዊና አከራካሪ ጭብጦች በተለይም ስለ ስነፆታ ፣ ዘር ፣ የሕብረተሰቡ ጥንታዊ ባህላዊ እሴቶች ፣ [indigenous cultures] የተለያዩ ሃይማኖቶች፣ የኤች አይ ቪ ሰለባዎች፣ አካል ጉዳተኞች ወዘተ ላይ ዳኞች ስልጠና እንደሚያስፈልጋቸው በምርምር ተረጋግጧል።[36] በእርግጥ ከነዚህ ወቅታዊ ጉዳዮች ባሻገር የዳኝነት ሥራ አዲስ ለሚሾሙ ዳኞችም ሆነ ሰፊ ልምድ ላላቸው የሕግ ሙያተኞች ጭምር አዲስ ነው የሚሆንባቸው ፣ ምክንያቱም ከዚህ በፊት እነዚህ ሰዎች የማያውቁትን አዳዲስ እውቀትና ክህሎት በተለይም የዳኝነት ሥነ ምግባር፣ የችሎት አመራር ፣ እንዲሁም ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ሊኖር የሚገባ ግንኙነት፣ ወዘተ ላይ የሚያገኙበት ነውና። ስለዚህም ዳኞች በዳኝነት ሥራ ላይ ተገቢውን ትጋትና ጥረት እንዲያሳዩ እንዲሁም በየወቅቱ ከሚለዋወጡ ሁኔታዎችና አዳዲስ ሕጎች ጋር በሚገባ እንዲተዋወቁ በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ የሥራ ላይ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል።መንግሥትም ቢሆን ይህንን በቅጡ በመገንዘብ ለዳኞች ስልጠና የሚያስፈልገውን በጀት መመደብ ያለበት ሲሆን የዳኞችም ስልጠና በፍ/ቤቶች እንጂ በሌላ ማንኛውም አካል ሊመራ ወይም ሊሰጥ አይገባም። በዚህ በኩል አንድ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ነጥብ ዳኞች በዕለት ተዕለት የዳኝነት ተግባራቸው ምክንያት ባገኙት ዕውቀት ብቻ በየቀኑ የሚያጋጥማቸውን ውስብስብ የሆኑ የማህበረሰቡን ችግሮች ለመፍታት ብቃት አላቸው ብሎ መገመት ከባድ ነው። ምክንያቱም አሁን ባለንበት ጊዜ የሕብረተሰቡ አኗኗር

[36] ዝኒ ከማሁ

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰበ ከመምጣቱም በላይ በየጊዜው እየተለዋወጠ የሚገኘው የቴክኖሎጂ ዕድገትና የመረጃ ፍሰትም ተከታታይ ስልጠናዎችን የግድ ይላል፡፡

11. ዳኞች ሁልጊዜም ቢሆን በየወቅቱ ከሚፈጠሩ አዳዲስ የዓለምአቀፍ ሕግ መርሆዎች ጋር በተለይም የዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች ጋር በሚገባ መተዋወቅና ዕውቀታቸውን ማዳበር አለባቸው፡፡[37] አሁን ያለንበት ወቅት የግሎባላይዜሽን ጊዜ በመሆኑ ምክንያት የዓለምአቀፍ ሕግ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ አስፈላጊነቱ እየጨመረ በመምጣቱ ዳኞች በዋነኛነት ሰብዓዊ መብቶችን የሚመለከቱ የአለምአቀፍ ህግጋትን እንዲያውቁ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር በባንግሎር የዳኝነት ሥነምግባር ሃተታ ዘምክንያት ሰነድ ላይ የሰፈረውን አስተያየት እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

increasing relevance Of international law in relations between the individual and the State, it is necessary that the powers entrusted to a judge must be exercised, not only in accordance With domestic law, but also, to the full extent that domestic law permits, in a way consistent with the principles of international law recognized in modern democratic societies. Subject to any requirements of local law, whatever the nature of his or her duties, a judge cannot properly ignore, or claim ignorance of, international law, including the international law of human rights, be it derived from customary international law, the applicable international treaties or the regional human rights conventions, where applicable.[38]

12. አንድ ዳኛ የዳኝነት ሥራውን በጠቅላላና ለርዕሱ የተመደቡትን ጉዳዮች በተቻለው መጠን ሁሉ በፍጥነት ፣ ፍትሃዊ በሆነ መንገድና በአጭር ጉዜ

---

[37] ዝኒ ከማሁ ገጽ 126

[38] ዝኒ ከማሁ

ውስጥ ለማከናወን ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡[39] ዳኞች የያዟቸውን ጉዳዮች በቅልጥፍና እና ውጤታማ በሆነ መንገድ በሚያዩበት ወቅት በፍርድ ሂደቱ ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በቂ የሆነ የመደመጥ ዕድል እንዲያገኙና ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቧቸው ሁሉም የክርክር ጭብጦች ያለ አንዳች መዘግየትና ከፍተኛ ወጪ ሳያስከትል በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ማግኘት አለበት፡፡ ዳኞች ሁልጊዜም ቢሆን ጉዳዩች በአላስፈላጊ ምክንያቶች እንዳይጓተቱና ባለጉዳዮችም በዚህ ሳቢያ ለአላስፈላጊ ወጪና እንግልት እንዳይጋለጡ ለማድረግ ብርቱ ጥረት ማድረግ የዳኝነት ትጋት የሚጠይቀው ዋነኛው የዳኞች የሥነ ምግባር ግዴታ ነው፡፡ በርግጥ ጉዳዮችን በፍጥነት ለመወሰን ዳኞች የተለያዩ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ አንዳንዴም ባለጉዳዮች ክርክራቸውን በስምምነት [settlement] እንዲቋጩ ግራ ቀኙን ማበረታታት ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ዳኞች ጉዳዮችን በቅልጥፍና አይተው እልባት እንዲያገኙ ማድረግ አለባቸው ሲባል በርግጥ ስለ ፍርድ ጥራት፣ ህጋዊነትና ፍትሃዊነት መጨነቅ አይገባቸውም ማለት ሳይሆን ለነዚህ እሴቶችም እየሰሩ በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳዮች በፍጥነት ለመወሰንም ዘወትር የሥራ ሰዓትን አክብረው በችሎት ላይ መገኘት የሚገባቸው ሲሆን ከእነርሱ ጋር የሚሰሩ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ፣ እንዲሁም ጠበቆችና ተከራካሪ ወገኖችም ቢሆን ከዳኞች ጋር በመተባበር የቀጠሯቸውን ሰዓት አክብረው እንዲገኙ ዳኞች ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ዳኛ በእጁ የሚገኘውን ጉዳይ በተቻለው አቅም ሁሉ በፍጥነት መወሰን ያለበት ሲሆን ለሚሰጣቸው ውሣኔዎችም ተገቢውን ምክንያት አግባብ ባለው ሕግ አስደግፎ በፍርዱ ውስጥ በሚገባ ማተት አለበት፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለጉዳዮች ወይም ጠበቆች በቀጠሮ ላይ ያሉ ጉዳዮች ስላሉበት ደረጃ እንዲያውቁ ግልፅ የሆነ የአሰራር ስርዓት በማስፈን ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ከዚሁ ጐን ለጐን ደግሞ ያለአግባብ የዘገዩ ጉዳዮች ለምን እንደዘገዩ ቅሬታ ያላቸው ወገኖች አቤቱታ አቅርበው ምክንያቱን የሚያብራራ መረጃ የሚያገኙበትን አሰራር መቀየስ አለባቸው፡፡

[39] ዝኒ ከማሁ ገጽ 127

13. ዳኛ በማንኛውም ጊዜ በአሰራሩና በችሎት አመራሩ የፍርድ ቤቱን ክብርና ግርማ መጠበቅ ያለበት ሲሆን በችሎት በርሱ ፊት የቀረቡትን ጠበቆች ፣ ተከራካሪዎች ፣ ምስክሮችና እማኞችን በትዕግሥት ፣ በማክበርና በትህትና በማዳመጥ ከክርክሩ ጭብጥ ጋር አግባብነት ያለውን ሃሳባቸውን ማስጨረስ ይኖርበታል፡፡[40] በዳኛው ኃላፊነት ሥር የሚሰሩ ሌሎች የፍርድ ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችም ይህንኑ አክብረው እንዲገኙ ተገቢውን ክትትል ማድረግ አለበት፡፡ የፍርድ ቤቱን ክብር ማስጠበቅ ሲባል በችሎት ላይ የታደሙ ወገኖች በሙሉ የክርክር ሂደቱ በተለመደው ሥነሥርዓት እንዲካሄድ ስርዓት እንዲጠብቁና የክርክር አካሄድ ስነስርዓቶችን እንዲያከብሩ ማድረግ ነው፡፡ የፍርድ ቤቱን ግርማና ሞገስ ማስጠበቅ ደግሞ በችሎት ላይ የታደሙ ወገኖች በሙሉ በሰለጠነ አካሄድና በጥሞና የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተሉ ማድረግ ሲሆን ዳኛው በገፅታው ላይ በሚነበበው ስሜትና በአነጋገሩ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ክርክር በጽኑ ሁኔታና በአግባቡ [seriously and with fair consideration] እንደሚመለከተው ማሳየት ነው፡፡ በርግጥ አንድ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ቢኖር የፍርድ ቤቱን ግርማና ሞገስ ወይም ክብር ለማስጠበቅ በሚደረግ ጥረት ውስጥ ይህ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችል የታወቀ እስታንዳርድ የለም፡፡ በመሆኑም ብዙውን ጊዜ እንደዚህ ዓይነቱ ጉዳዩ ለዳኞች ውሣኔ [discretion] የተተወ በመሆኑ በዳኞች መካከል የአሰራር ልዩነት ይስተዋላል፡፡ አንደኛው ዳኛ የችሎቱን ክብርና ግርማ የሚነካ ባህርይ ነው ብሎ የሚፈርጀው ድርጊት በሌላኛው ዳኛ እንደ ተገቢ ድርጊት ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይም በኛም ሀገር በዳኞች መካከል የአሰራር ልዩነት የሚስተዋል ሲሆን ብዙውን ጊዜ ያለአግባብ ለትንሹም ለትልቁም የችሎት ሥነሥርዓት አላከበርክም በሚል የባለጉዳይን ቀልብ መግፈፍ አልፎ አልፎ ይታያል፡፡ ከዚህም የተነሳ ዳኞች ልብ ሊሉት የሚገባው ነጥብ ቢኖር የዚህ ዓይነቱ ድርጊታቸው ይልቁንም የፍርድ ቤቱን ግርማና ሞገሥ የሚነካ ተግባር መሆኑን ተረድተው ከዚህ ዓይነቱ ተግባር በመራቅ ባለጉዳዩችንና ጠበቆችን በትዕግሥት፣ በማክበርና በትህትና ማስተናገድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በርግጥ እንዲህ ሲባል የችሎት ሂደትን የሚያውኩ ተግባራት በተከራካሪዎች ወይም በጠበቆቻቸው በሚፈፀምበት ጊዜ ዳኞች እጃቸውን አጣጥፈው መቀመጥ አለባቸው ለማለት ሳይሆን የችሎት

[40] ዝኒ ከማሁ ገጽ 128

ሂደቱን የሚያውክ ነገር ባልተፈፀመበት ሁኔታ ለጥቃቅን ነገሮች ባለጉዳዮችን ማስደንገጥ ተገቢነት የለውም ለማለት ነው፡፡ ከላይ የገለፅነውን ሀሳብ በባንግሎር የዳኝነት ሥነምግባር ሃተታ ዘምክንያት ሰነድ ላይ የሰፈረ አንድ አስተያየት ጉዳዩን በሚገባ ስለሚያብራራው እንደሚከተለው አቅርበንዋል፡፡

> In court and in chambers, a judge should always act courteously and respect the dignity of all who have business there, A judge should also require similar courtesy from those who appear before him of her, and from court staff and others subject to the judge's direction or control. A judge should be above personal animosities, and must not have favourites amongst advocates appearing before the court. Unjustified reprimands of counsel, offensive remarks about litigants or witnesses, cruel jokes, sarcasm, and intemperate behaviour by a judge undermines both order and decorum in the court. When a judge intervenes, he or she should ensure that impartiality, and the perception of impartiality, are not adversely affected by the manner of the intervention.[41]

15. በመጨረሻም ዳኞች የዳኝነት ሥራን በትጋትና ጥረት እንዳያከናውኑ ከሚያደርጋቸውና አግባብነት ከጉደላቸው ድርጊቶች ሊታቀቡ ይገባል፡፡ በተለይም መዝገቦችን ለዳኞች የማከፋፈል ኃላፊነት ያለበት ዳኛ የባለጉዳዮችን ወይም የጠበቆችን ወይም የሥራ አስፈጻሚውን የመንግሥት አካል ፍላጐት ብቻ ከግምት በማስገባት መዝገቦችን ለአንድ ችሎት ወይም ለሌላ ችሎት ማከፋፍል እያለበት አንድ ጠበቃ ወይም ባለጉዳይ ጉዳያቸውን እንዲያይ ለሚፈልጉት ዳኛ እንዲሰጥ ማድረግ ተገቢነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዮች በተወሰኑ ዳኞች ወይም ችሎቶች እጅ ተከማችተው በፍጥነት እልባት እንዲያገኙና እንዳይቋጩ ሊያደርግ ከመቻሉም በላይ በጥቂት ዳኞች ላይ ተገቢ ያልሆነ የሥራ ጫና ሊፈጥር ይችላልና፡፡ ስለዚህም የመዝገብ ክፍፍል በሚደረግበት ወቅት ከሁሉም ዳኞች ጋር ውይይት በማካሄድ ፍትሃዊ

---
[41] ዝኒ ከማሁ ገጽ 129

እንዲሆን መጣር የሚያስፈልግ ሲሆን ክፍፍሉ በቁጥርም ሆነ በጉዳዩ ውስብስብነት ለሁሉም ዳኞች እኩል መከፋፈል ይኖርበታል፡፡

16. አንድ ጉዳይ ለአንድ ዳኛ ከተሰጠ በኋላ በምንም ዓይነት ዳኛው በሕመም ምክንያት ወይም ከጥቅም ግጭት የተነሳ ጉዳዩን ለማየት የማይችል ካልሆነ በቀር ጉዳዩን እንዳያይ ለማድረግ መዝገቡ ከርሱ ሊወሰድ ወይም ሊነጠቅ አይገባም፡፡ አንድን ጉዳይ እንዳይመለከት መደረግ የሚችለው አግባብ ያለውን የሕግ ሥነሥርዓት ተከትሎ ዳኛው ጉዳዩን ከማየት ራሱን ማንሳት ወይም ማግለል ካለበት ብቻ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱም ውሣኔ ቢሆን በሌሎች የመንግሥት አካላት ጣልቃ ገብነት ወይም ተጽኖ ሊወሰን አይገባም፡፡ ይልቁንም አግባብነት ያላቸውን ህጎችና ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ተከትሎ ሊሆን ይገባል፡፡

17. ከዚህ በተጨማሪ ዳኞች የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ያለአግባብ ከመደበኛው ሥራ ጋር ግንኙነት በሌላቸው ሁኔታዎች የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማስገደድና የሥራ ጫና እንዲበዛባቸው ማድረግ አይገባቸውም፡፡ በተለይም የራሳቸውን የግል ሥራ እንዲሰሩ አላስፈላጊ ጫና እና ግፊት ማሳደር ተገቢነት የለውም፡፡

<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በአንድ ችሎት በተያዘ ጉዳይ ዳኛው ውሳኔ ሲጽፍ ተከሳሽ ያቀረባቸውን የህግ ክርክሮች ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም ብሎ ስላመነ በቀረቡት የህግ ክርክሮች ላይ ሳይተችበት በተከሳሽ ላይ ውሳኔ ሰጠ፡፡ ዳኛው ይህንን ማድረጉ ለከሳሽ ያደላ መሆኑን ያመለክታል በሚል በዳኛው ላይ ክስ ቀረበበት፡፡ በእርግጥ ዳኛው አድልዎ ፈጽሟል ሊባል ይችላል?
2. የዳኛውን ትጋትና ጥረት በሚመለከት ከጫት ጋር በተያያዘ ምን አይነት ባህርይ ሊኖረው እንደሚገባ ተወያዩበት፡፡

የአቃቤ ህግ የስነምግባር መርሆዎች

የተለያየ የህግ ስርአት በሚከተሉ አገሮች ተመሳሳይ የሆነ የአቃቤ ህግ ሚና ለማስቀመጥ ያስቸግራል። ይሁንና በብዙዎቹ አገሮች በአቃቤ ህግ የሚሰሩት ስራዎች የሚከተሉት ናቸው ማለት ይቻላል።

1. የወንጀል ምርመራ ስራን መምራትና መቆጣጠር፣
2. የወንጀል ምርመራ መዝገብን መርምሮ ክስ ለመመስረት ወይም መዝገቡን ለመዝጋት መወሰን፣
3. በፍርድ ቤት የወንጀል ክስ መስርቶ መከራከርና ክሱን ለማቆም መወሰን፣
4. በማስረጃ ከተረጋገጠው የወንጀል ድርጊት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅጣት ውሳኔ ማቅረብ፣
5. በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብና መከራከር
6. በህግ የተፈቀደ በሆነ ጊዜ ለአነስተኛ የወንጀል ድርጊቶች ከወንጀል ክስ ውጭ በሌላ መልኩ ክርክሩን መጨረስ፣
7. የወንጀል ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲሆን መቆጣጠር
8. የወንጀል ፍትህ ስርአቱን ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ ማሳወቅና ማስተማር

አቃቤ ህግ በህግ ከሚያከናውነው ስራ አንጻር ሊከተላቸውና ሊተገብራቸው የሚገቡ ሙያው የሚጠይቃቸው የስነምግባር ደረጃዎች አሉ።

2.3.1. መልካም ሙያዊ ተግባር

በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ መሰረታዊ አንቀሳቃሾች እንደመሆናቸው መጠን ዐቃብያነ ሕግ ዘወትር ለሙያቸው ክብር መታመንና በጽኑ መቆም አለባቸው።[42] እንደሚታወቀው ሁሉ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ በሕግ ፊት እኩል ሆኖ የመታየትን ፣ ንፁህ ሆኖ የመገመትን፣ እንዲሁም ነፃና ገለልተኛ በሆነ የፍርድ አካል

[42] በአቃቤ ህግ ሚና ላይ የተባበሩት መንግስታት መመሪያዎች አንቀጽ 3ትን ይመልከቱ። በተጨማሪም standards of professional responisibilty and statement of the essential duties and rights of prosecutors adopted by the international Association of Prosecutos on the twenty third day of April 1999 article 1 ይመልከቱ።

ፍትሃዊና ግልፅ በሆነ መንገድ የመዳኘት መብትን፣ እንደቁልፍ መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች መደንገጉ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ዐቃብያነ ሕግ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ በእነኚህ መርሆዎች ለመመራትና እነዚህን መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ሙያዊ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዐቃብያነ ሕግ በፍትህ አስተዳደር ውስጥ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑና አስፈላጊ የሆኑ ሃላፊነቶቻቸውን ስለመወጣት ያሉት ሕጐች እነዚህን መርሆዎች ዐቃብያነ ሕግ እንዲያከብሯቸውና እንዲገዙባቸው ሊያበረታቱ ይገባል፡፡ በዚህም ፍትህና ርትዕ የተሞላው የወንጀል ፍትህ ስርዓትና ለዜጐች ከወንጀል መጠበቅ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ ስርዓትን መፍጠር ይቻላል፡፡

ዐቃብያነ ሕግ በወንጀል ፍርድ ሂደት ውጤታማ፣ ገለልተኛና ፍትሃዊ እንዲሆኑ የሚያስፈልግ ሲሆን እነዚህን የሥነምግባር መርሆዎች ለመላበስም ለሙያቸውና ለሕግ መታመን ይኖርባቸዋል፡፡ ሥራቸውንና ኃላፊነታቸውንም በነዚሁ የሙያ የስነምግባር መርሆዎች መሰረት ማከናወን የግድ ይላል፡፡ ከዐቃብያነ ሕግ የላቀ ስብዕናና ከፍ ያለ ሥነምግባር ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን በየጊዜው የሚደረገውን የሕጐች ለውጥና አዳዲስ ሕጐችን በመከታተል ራሳቸውን በበቂ መረጃና ዕውቀት ማነፅ ይገባቸዋል፡፡ ይህም ማለት የሙያቸውን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት የራሳቸውን እውቀትና ክህሎት ለማሳደግ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዐቃብያነ ሕግ በወንጀል ፍርድ ሂደት ውስጥ ወጥነት ባለው መልኩ፣ ገለልተኝነታቸውን በሚያረጋግጥ አኳኋን፣ እንዲሁም ያለ አድሎ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም ሲባል የቀረበላቸውን የወንጀል ምርመራ መዝገብ በሚመረምሩበት ወቅት ክስ ለመመስረት ወይም ላለመመስረት የሚያደርጉት ውሣኔ ሁሌም ቢሆን ተገማችነት ሊኖረው የሚገባና ከማስረጃዎች ምዘና አንፃር የሚያራምዷቸው አቋሞች እርስ በርሳቸው የማይቃረኑ መሆን አለበት፡፡ ክስ ለመመስረት በሚያደርጉት ውሳኔም በማናቸውም አካል ጣልቃ ገብነት ወይም ተፅዕኖ ሊመሩ አይገባም፡፡ ይልቁኑ በሕጉ ላይ ብቻ በመመስረት የቀረበላቸውን ፍሬ ነገር ገለልተኛ ሆኖ መመዘን ነው የሚኖርባቸው፡፡ አሰራራቸው ለአድሎአዊነት በተጨባጭ የተጋለጠ ወይም አድሎ የሚያደርጉ መስሎ ለሌሎች ሰዎች መታየት እንደሌለበት በመገንዘብ ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ዐቃብያነ ህግ ሁሌም ቢሆን ተከሳሾች ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የመዳኘት መብታቸው እንዲከበር ተገቢውን ጥረት ማድረግ የሚኖርባቸው ሲሆን ለተከሳሾች ጠቀሜታ ያለው ማስረጃ በእጃቸው በሚኖርበት ወቅትም እነዚህኑ ማስረጃዎች በተገቢው የሕግ ሥነሥርዓት መሰረት ለተከሳሾች መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም ተከሳሾ ወደ ዋናው የፍርድ ሂደት ከመግባታቸው በፊት በክስ መስማት ደረጃ ዐቃብያነ ሕግ የሚያቀርቡባቸውን ማስረጃዎች ለተከሳሾች ግልጽ ማድረግ (pre trial disclosure of relevant evidences to accused persons) ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ዐቃብያነ ሕግ ለፍትህና እውነት ነው መቆም ያለባቸው እንጂ ተከሳሹን መርታትን እንደ ሙያቸው ግብ አድርገው መመልከት አይኖርባቸውምና፡፡

በሌላ በኩል ዐቃብያነ ሕግ ሁልጊዜም ቢሆን የሕዝቡን ጥቅም ማስጠበቅ ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ክስ ለመመስረትም ሆነ ላለመመስረትም ወይም ለፍርድ ቤት የቀረቡ ክሶችን ለማንሳት በሚወሰኑበት ጊዜ የሕብረተሰቡን ጥቅም ከግምት ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩና እንዲጠበቁ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያለባቸው ሲሆን የሙያ ግዴታቸውን በሚወጡበት ጊዜ የሰዎች ስብዕና፣ክብርና መሰረታዊ ነፃነቶች እንዲጐለብቱ ብርቱ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡[43]

የሙያ ነጻነት

ዐቃብያነ ሕግ ውጤታማና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲሁም ያለ አንዳች አድሎ ገለልተኛ ሆነው ሥራቸውን ማከናወን የሚችሉት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሊመጡ ከሚችሉ ተጽኖዎች ነፃ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡[44] በዚህ ረገድ የዐቃብያነ ሕግን ሚና ለመወሰን በተባበሩት መንግሥታት የወጣው መመሪያና በዐቃብያነ ሕግ ዓለምአቀፍ ማህበር የወጣው የተግባር መመሪያ ሁሉም ሀገራት የዐቃብያነ ሕግን ሙያዊ ነፃነት ለማስጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸውና ተጨባጭ ርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባቸው ነው፡፡ መንግሥታት ዐቃብያነ ሕግ ሙያዊ ግዴታቸውን ያለ ማስፈራራት፣ እክል፣ ትንኮሳ፣ አግባብ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት፣ ወይም ለምክንያት አልባ የፍትሃብሄር፣

---

[43] ዝኒ ከማሁ

[44] THE ROLE AND INDEPENDENCE OF PROSECUTORS Paul Mageean, Belfast,Northern Ireland 17 th May 2005, Cairo ገጽ 7 ይመልከቱ

የወንጀል ወይም ሌላ ሃላፊነት ሳይጋለጡ መወጣት መቻላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።[45] የዐቃብያነ ሕግ የአገልግሎት ሁኔታዎች፣ ደመወዝና የአገልግሎት ዘመን ገለልተኝነታቸውንና ነፃነታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ነው መደራጀት የሚገባው።[46] ተገቢነት ያላቸው የዐቃብያነ ሕግ የአገልግሎት ሁኔታዎች፣ በቂ ደመወዝ፣ እንዲሁም አግባብነት ባለው ጊዜ የአገልግሎት ዘመን፣ ጡረታና የጡረታ እድሜ በሕግ ሊደነገጉ ወይም በታተሙ ሕጎች ወይም ደንቦች ሊወጡ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪም ስርዓቱ በሚፈቅድበት ሁሉ የዐቃቤ ሕግ የሥራ ዕድገት በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ በተመሰረተ ህግ በተለይም ሙያዊ ብቃትን፣ ችሎታን፣ ጠንካራ ስብዕናን፣ እና ልምድን መሰረት ያደረገ ፍትሃዊና ገለልተኛ የሆነ ስነ ስርዓት ተከትሎ የሚወሰን መሆን አለበት።[47] ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዐቃብያነ ህግ የመክሰስ ውሳኔን ለመስጠት ወይም ክስን ላለመመስረት ለመወሰን ዲስክሬሽን ባላቸው ጊዜ ውሳኔያቸውን በህግና በቀረቡላቸው ፍሬ ነገሮች ላይ በመመስረት እንጂ ከየትኛውም አቅጣጫ በሚመጣ ተፅኖ ወይም ግፊት መወሰን የለባቸውም። በተለይም ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ዐቃብያነ ህግ ነፃ መሆን እንደሚገባቸው የአለም አቀፍ ዐቃብያነ ህግ ማህበር የተግባር መመሪያ አንቀፅ 2/1/ ያትታል። ሌሎች የመንግስት ባለስልጣናት ለዐቃብያነ ህግ ክስ እንዲመሰርቱ ወይም እንዳይመሰርቱ ትዕዛዝ ለመስጠት በህግ ስልጣን ያላቸው እንደሆነ እነዚህ የመንግስት አካላት ወይም ባለስልጣናት ይህንን ስልጣን ላይ ማዋል የሚገባቸው በግልፅነት፣ ህጋዊ የስልጣን ገደባቸውን ሳይተላለፉና የዐቃብያነ ህግን የመወሰን ሙያዊ ነፃነት ሳይገፉ መሆን ይገባዋል።[48]

2.3.3. <u>የዐቃቤ ህግነት ስራን ያለ አድሎአዊነት ማከናወን</u>

ዐቃብያነ ህግ ስራቸውን ያለ አድሎ፣ ፍትሃዊ ግልፅ በሆነ መንገድ እንዲያከናውኑ የዐቃቢያነ ህግን ሚና ለመወሰን በተባበሩት መንግስታት የወጣ መመሪያና የአለም አቀፍ የዐቃቢያነ ህግ ማህበር የተግባር መመሪያ ያስገነዝባሉ። የተባበሩት መንግስታት የዐቃቢያነ ህግን ሚና ለመወሰን የወጣው መመሪያ ዐቃቢያነ ህግ በወንጀል ፍርድ ሂደት

---

45 በዐቃብያነ ህግ ሚና ላይ የተባበሩት መንግሥታት መመሪያዎች አንቀፅ 4ን ይመልከቱ።

46 ዝኒ ካማሁ አንቀጽ 6ን ይመልከቱ።

47 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 7

48 Standards of professional responsibility and statement of the essential dities and rights of prosecutors adopted by the international association of prosecutors on the twenty third day of April 1999 አንቀፅ 2/2/ እና /3/ ይመልከቱ።

ውስጥ ስራቸውን ፍትሃዊ፣ ወጥና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እንዲወጡ፣ ለሰብአዊ መብቶች መከበር እንዲቆሙና ስራቸውን በገለልተኝነት ያለ አንዳች አድሎ እንዲያከናውኑ፣ እንዲሁም በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አቋም፣ በሃይማኖት፣በዘር፣በባህል ወይም በሌሎች ምክንያቶች አድሎአዊ ልዩነት ማድረግ አይገባቸውም፡፡[49] ዐቃብያነ ህግ በሕጉ መሰረት ግዴታቸውን ፍትሃዊ በሆነ፣ በአንድ ወጥና በቀልጣፋ ሁኔታ መወጣት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን መጠበቅ፣ ሰብአዊ መብቶችን ማክበር፣ በዚህም አግባብ ያለው የህግ አካሄድ እና እንከን የሌለው የወንጀል ፍትህ ስርዓት አሰራር እንዲኖር ለማስቻል የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር ስራቸውን ገለልተኛ በሆነ መልኩ ማከናወን እና ከማናቸውም የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ሃይማኖታዊ፣የዘር፣ባህላዊ ፣የጾታ፣ ወይም ሌላ ማናቸውም አይነት አድሎ ነፃ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

የህዝብን ጥቅም መጠበቅ፣በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ መመስረት፣ የተጠርጣሪውንና የተጠቂውን ሁኔታ በአግባቡ ከግምት ማስገባት፣ ለተጠርጣሪው ጠቀሙም አልጠቀሙም ማናቸውንም አግባብ ያላቸውን ሁኔታዎች ማስተዋል አስፈላጊ ነው፡፡ ገለልተኛ የሆነ ምርመራ ክሱ መሰረተ ቢስ መሆኑን ሲያሳይ ዐቃብያነ ህግ ክስ አይጀምሩም፡፡ አይቀጥሉም፣ ወይም ሂደቱ እንዲቆም የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡[50] ዐቃብያነ ህግ ክስ የሚመሰርቱት የቀረበላቸው ማስረጃ አጥጋቢና አሳማኝ እንዲሁም ተዓማኒነት ያለው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያያዞ የክሱ ማስረጃ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የተሰበሰበ እንደሆነ ወይም የተከሳሹን መሰረታዊ መብቶች በመጣስ የተሰበሰበ ማስረጃ እንደሆነ የዚህ አይነቱ ማስረጃ ለሚቀርበው ክስ በማስረጃነት እንዲያገለግል ማድረግ የማይገባ ሲሆን የተከሳሹን መብቶች በመጣስ ማስረጃውን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ እንዲሰበስብ ባደረጉ አካላት ላይ ተገቢውን ማጣራት ተካሂዶ ለህግ እንዲቀርቡ ማድረግ የዐቃብያነ ህግ ግዴታ ነው፡፡ ይህም ማለት ዐቃቢያነ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የተጠርጣሪውን መብቶች በብርቱ በሚጥስ በተለይም ማሰቃየት፣ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብአዊ፣ ወይም አዋራጅ አያያዝን ወይም ቅጣትን ወይም ሌላ የሰብአዊ መብት

---

[49] የዐቃቢያነ ህግ ሚና ለመወሰን በተባበሩት መንግስታት የወጣ መመሪያ አንቀፅ 12 እና 13 /ሀ/ ይመልከቱ፡፡
[50] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 14

መጣስን በመጠቀም እንደተገኘ የሚያውቁትን፣ ወይም በበቂ ምክንያት ይህ ስለመሆኑ የሚያምኑበትን በተጠርጣሪ ላይ የቀረበ ማስረጃ በድርጊቱ ፈፃሚዎች ላይ ካልሆነ በቀር በማንም ሰው ላይ ላለመጠቀም መወሰን፣ ወይም ፍርድ ቤቱን ስለሁኔታው ማስረዳት እንዲሁም እንደዚህ ያለውን መንገድ የተጠቀሙ ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ አለባቸው፡፡[51]

ዐቃቢያነ ህግ ስራቸውን ያለ አድሎ ለማከናወን ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

- በግለሰቦች ወይም በተወሰኑ ቡድኖች ወይም በሚዲያና በህብረተሰብ ግፊት ስር ባለመውደቅ የህዝብን ጥቅም መጠበቅ፣
- ለተጠርጣሪው ጠቀሜታ ያላቸውም ሆነ አልሆኑ አግባብ ያላቸውን ሁኔታዎች(All relevant circumstances)
- በአካባቢው ህግ የተፈቀደ እንደሆነ ወይም ፍትሃዊ የፍርድ ሂደት እንዲኖር የሚያስፈልግ ከሆነ ደግሞ የተጠርጣሪውን ንፅህና ወይም ጥፋተኝነት በሚመለከት ተገቢው ምርመራ እንዲካሄድና የምርመራውም ውጤት ይፋ እንዲደረግ የማድረግ
- በህግና ርትዕ መሰረት በተከሳሹ፣ በተጎጂውና በህብረተሰቡ መካከል ፍርድ ቤቶች ትክክለኛውን ፍትህ እንዲያደርጉና እውነትን እንዲያፈላልጉ ተገቢውን ጥረት ማድረግና ፍርድ ቤቶችን መርዳት ነው፡፡

2.3.4. <u>ዐቃቢያነ ህጎች በወንጀል የፍርድ ሂደት ሊኖራቸው የሚገባ ሚና</u>

የዓቃቤ ህግ ስራ ግልፅ በሆነ መንገድ ከዳኝነት ስራ መለየት ያለበት ሲሆን ክስ መመስረትን ፣በህግ በተፈቀደ ወይም በአካባቢው አሰራር የተለመደ በሆነ ጊዜ ደግሞ የወንጀል ምርመራን፣ የነዚህ ምርመራዎችን ህጋዊነት መቆጣጠርን፣ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ አፈፃፀምን መቆጣጠርን እንዲሁም የህዝብ ጥቅም በመወከል የሚፈፀሙ ሌሎች ስራዎችን ጨምሮ ዐቃብያነ ህግ በወንጀል የፍርድ ሂደት ውስጥ ንቁ ሚና መጫወት አለባቸው፡፡[52] የወንጀል ምርመራን በሚቆጣጠሩበትና በሚመሩበት ወቅት መርማሪ አካላት ህጉን አክብረው እንዲሁም የተጠርጣሪውን ሰብአዊ መብቶች ባረጋገጠ አኳኋን

---

[51] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 16
[52] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 10 እና 11

ምርመራውን እንዲያከናውኑ ክትትል ማድረግ የሚገባቸው ሲሆን ለመርማሪ አካላት ምክር በሚለግሱበት ወቅትም ገለልተኝነትና ፍትሃዊነትን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ክስ መመስረት ያለባቸው ደግሞ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ሲኖራቸው ብቻ መሆን አለበት፡፡ ዐቃብያነ ህግ የወንጀል ፍርድ ሂደትም በተቻለው መጠን ሁሉ ፍትሃዊና ግልፅነት ያለው እንዲሆን የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸው፡፡ በህግ በተፈቀደላቸው ጊዜ ወይም የአካባቢው አሰራር ልምድ በሚፈቅድላቸው ወቅት የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን አፈፃፀም በሚቆጣጠሩበት ጊዜ ወይም ሌሎች ተግባራትን በሚያከናውኑበት ጊዜ የህዝብ ጥቅም መጠበቅ ቀዳሚ አላማቸው ሊያደርጉ ይገባል፡፡

ከዚሁ በተጨማሪ ዐቃብያን ህግ በህዝብ ባለስልጣናት ለሚፈፀሙ በተለይም ሙስና፣ በስልጣን አላአግባብ መገልገል፣ ከባድ የሰብአዊ መብቶች ረገጣ፣ እና ሌሎችም በአለም አቀፍ ህግ ለተደነገጉ ወንጀሎች የክስ ሂደት ተገቢውን ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡[53] የግል ጥቅማቸው በሚነካበት ጊዜ የተጠቂዎችን አመለካከቶች ከግምት ማስገባት፣ በወንጀልና በስልጣን አላአግባብ መገልግል ተጠቂዎች መሰረታዊ የፍትህ መርሆዎች ድንጋጌ መሰረት ተጠቂዎች ስለመብቶቻቸው እንዲያውቁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተጠቂዎች መብት እንዲከበርም ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው መስራት የሙያ ግዴታቸው ነው ፡፡ በሌላ አነጋገር ዐቃብያነ ህግ ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ በስራ አጋጣሚ እጃቸው የገባውን ሚስጥር የመጠበቅ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን የወንጀል ተጠቂዎች ሆነ የምስክሮች መብት መከበሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋቸዋል፡፡

በተለይም ዐቃብያነ ህግ የሚከተሉት ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

- በነርሱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ካለ ቀጥሎ ወደ ሚገኙት ባለስልጣናት ወይም የሚቻል ከሆነ ወደ ፍርድ ቤት ቅሬታውን የማቅረብ መብት እንዳለው የማሳወቅ ግዴታ፣(seek to ensure that any aggrieved party is informed of the right of recourse to some higher authority) court, where that is possible)
- የተከሳሹን መብቶች ከፍርድ ቤቶችና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲከበር ብርቱ ጥረት ማድረግ፣(safeguard the right of the accused in cooperation with the court and other relevant agencies)

[53] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 15

- በህግ ወይም ፍትሃዊ ዳኝነት ማስፈን በሚጠይቀው አግባብ ለተከሳሹ የሚጠቅምም ሆነ የማይጠቅም ማስረጃ በተቻለ ፍጥነት ይፋ ማድረግ፣(disclose to the accused relevant prejudicial and beneficial information as soon as reasonably possible, in accordance with the law or the requirements of a fair trial)

- ክስ በሚመሰርትበት ጊዜ ዐቃብያነ ህግ ሊጠቀሙበት ያቀዱትን ማስረጃ ህጋዊነት በሚገባ መፈተሽ፣Examine proposed evidence to ascertain if it has been lawfully or constitutionally obtained)
- በህገ ወጥ መንገድም በተለይም የተጠርጣሪውን ሰብአዊ መብቶች በመጣስና በተጠርጣሪው ላይ ጭካኔ የተሞላበትና አዋራጅ የሆነ አያያዝን በመፈፀም የተሰበሰበ ማስረጃ ለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ካለ ዐቃብያነ ህግ እንዲህ አይነቱን ማስረጃ ለክስ አመሰራረት መጠቀም አይኖርባቸውም።(refuse to use evidence reasonably believed to have been obtained through recourse to un lawful methods which constitute a grave violation of the suspect's human rights and particularly methods which constitute torture or cruel treatment)
- እንደዚህ ያለውን መንገድ በመጠቀም ማስረጃን በህገ ወጥ መልኩ ያሰባሰቡ መርማሪ አካላት ካሉ በነዚሁ ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ነው።

ከላይ ከተገለፁት ተግባራት ባሻገር ዐቃብያነ ህግ ብሄራዊ ህግን መሰረት በማድረግ ክስን ለመተው ያለምንም ቅድመ ሁኔታም ሆነ በቅድመ ሁኔታ ለማቋረጥ፣ ወይም ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጉዳዮችን በአማራጭ እልባት ወደሚያገኙበት መድረክ ለመምራት ተገቢውን ትኩረት መስጠት አለባቸው። ይህንን ሲያደርጉ ግን የተጠርጣሪዎቹንና የተጠቂዎቹን መብቶች ሙሉ በሙሉ ማክበር ይገባቸዋል። ለዚህም ሲባል የፍርድ ቤቶች የስራ ጫና ለማቃለል ብቻ ሳይሆን ቅድመ ክስ፣ እስር ፣መከሰስ፣ጥፋተኛ በመባሉ የሚያስከትለው የመገለል ስሜትና እስር ሊያስከትል

የሚችለውን ፅኑ ውጤት ለማስቀረት መንግስታት በተቻላቸው አቅም አማራጮች እንዲያፈላልጉ ግፊት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡[54]

2.3.5. ከሌሎች የፍትህ አካላት ጋር በቀና የትብብር መንፈስ ተቀናጅቶ ስለመስራት

የክስ ሂደትን ፍትሃዊነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ዐቃብያነ ህግ በተቻላቸው አቅም ከፖሊስ፣ ፍርድ ቤቶች፣የህግ ባለሙያዎች፣ተከላካይ ጠበቆችና ሌሎች የመንግስት አካላት ወይም ተቋማት ጋር ለመተባበር መሞከር አለባቸው፡፡[55] ዐቃብያነ ህግ በሌሎች ሀገሮች ለሚገኙ የዐቃብያነ ህግ ተቋማትና የሙያ አጋሮቻቸው ጋርም ተባብረው መስራት እንደሚጠበቅባቸው ተመልክቷል፡፡

ከሌሎች አካላት ጋር ዐቃብያነ ህግ በሚኖራቸው የስራ ግንኙነት የሙያ ነፃነታቸው በሚገባ እንዲጠበቅ የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ ይጠቅባቸዋል፡፡
በተለይም የዐቃቤ ህግነት ስራቸውን ከስራ አስፈፃሚ የመንግስት ተቋማትና ከህግ አውጪው ክፍል ተፅእኖ ሳይደረግባቸው በህግና በህጉ መሰረት ብቻ ነው ማከናወን ያለባቸው፡፡[56] በርግጥ በብዙ ሀገሮች የዐቃቢያነ ህግ ተቋማት በስራ አስፈፃሚነት የመንግስት አካል ስር የተደራጁና ተጠሪነታቸውም ለነዚሁ አካል ሲሆን የተባበሩት መንግስታት የዐቃብያነ ህግ ሚናን በተመለከተ የወጣው መመሪያም ሆነ የአለም አቀፍ ዐቃብያነ ህግ ማህበር የተግባር መመሪያ ይህንን አደረጃጀት መቀየር ላይ ሳይሆን ትኩረቱ ዐቃብያነ ህግ ከስራ አስፈፃሚ የመንግስት አካል አንድ ጉዳይ ላይ ክስ እንዳይቀርብ የሚያስተላልፈው ትዕዛዝ ገደብ ሊበጅለት እንደሚገባ ነው የአውሮፓ ህብረት አስተያየቶች የሚጠቁሙት፡፡

---

[54] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 18

55 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 20 ን ይመልከቱ በተጨማሪም የዓለም አቀፍ የዐቃብያነ ሐግ ማህበርን የተግባር መመሪያ አንቀጽ 5ን መመልከት ይቻላል

[56] THE ROLE AND INDEPENDENCE OF PROSECUTORS Paul Mageean, Belfaxt, Northern Ireland 17th may 2005. Cairo ገፅ 8 ይመለከቱ

የስራ አስፈፃሚው የመንግስት አካላት እንዲህ አይነቱን ስልጣን አልፎ አልፎ ብቻ መጠቀም እንደሚገባቸውና እንዲህ በሚደረግበት ጊዜ በግልፅነት በታወቁ መስፈርቶች ላይ መመስረት ወሳኝ እንደሆነ ነው፡፡[57]

2.3.6. ስልጣንና ተሰሚነት

ዐቃብያነ ህግ ስራቸውን በፍፁም ነፃነትና ስለዐቃቤ ህግነት በወጡ አለም አቀፍ መርሆዎች መሰረት እንዲያከናውኑ ከሌሎች የመንግስት አካላት ጣልቃ ገብነት መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ የዐቃቤ ህግነት ስልጣናቸውንም በህግ አግባብ ለህብረተሰቡ ጥቅምን በሚያስገኝ መልኩ ነው በትክክል ስራ ላይ ማዋል የሚያስፈልጋቸው ፡፡ በተለይም የዐቃቤ ህግነት ስልጣናቸውን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት የሚከተሉት ጥበቃዎች ከመንግስት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡[58]

- የሙያ ግዴታቸውን ያለ ማስፈራራት፣ እንቅፋት፣ወከባ ፣አግባብ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት ለምክንያት አልባ የፍትሃብሔር ፣ወንጀል ወይም ሌላ ኃላፊነት ሳይጋለጡ እንዲወጡ ዋስትና መስጠት፣
- ዐቃብያነ ህግ የስራ ግዴታቸውን በሚወጡበት ወቅት የግል ደህንነታቸው አደጋ ላይ በወደቀ ጊዜ ከመንግስት ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው የአካላዊ ደህንነት ጥበቃን የማግኘት
- ከሚያከናውኑት ቁልፍ ተግባርና ኃላፊነት ጋር የሚመጣጠን የአገልግሎት ሁኔታ፣ተመጣጣኝ ክፍያና በቂ ደመወዝ እንዲሁም የአገልግሎት ዘመን
- በተቻለ መጠን ሁሉ የዐቃብያነ ህግ ምልመላና የስራ እድገት በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ሙያዊ ብቃትን ፣ችሎታን፣ ጠንካራ ስብዕናንና ልምድን መሰረት ያደረገ ሆኖ ፍትሃዊና ገለልተኛ የሆነ ስርዓት(Fair and impartial Procedure0 ተከትሎ እንዲወሰን
- ዐቃብያነ ህግ ግልፅ በሆነ መንገድ ከሙያዊ ደረጃቸው ወሰን ዉጪ የሆነ ኢስነምግባራዊ ድርጊት ፈፅመዋል የሚል ቅሬታ በቀረበባቸው ጊዜ የዲስፒሊን

---

[57] ዝኒ ከማሁ

[58] standards of professional responsiblity and statement of the essential duties and rights of prosecutors adopted by the international Association of Prosecutors on the twenty third day of April 1999 article 6 ይመልከቱ፡፡

ክስ ሂደቱን በፍጥነትና ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ አግባብ ባላቸው ስነ ስርዓቶች መሰረት እንዲታይ፣

- በዲስፒሊን ክስ ሂደት ዐቃብያነ ህግ ገለልተኛ በሆነ መንገድ የመሰማትና ፍትሃዊ ውሳኔ የማገኘት መብታቸውን ሊረጋገጥላቸው እንደሚገባ፣ በዐቃቢያነ ህግ ላይ የሚደረግ የዲስፒሊን የክስ ሂደት ተጨባጭ ግምገማና ውሳኔ እንዲኖረው ማድረግ ተገቢነት ያለው ሲሆን ሂደቱም በህግ፣ በሙያዊ ስነምግባርና በሌሎች ተቀባይነት ባገኙ የኖሩ ደንቦች ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል፡፡
- እንደ ሌሎች ዜጎች ሁሉ ዐቃብያነ ህግ ሃሳብን የመግለፅ፣የእምነት፣የመደራጀትና የመሰብሰብ ነፃነት አላቸው፡፡ በተለይም ህግን፣ የፍትህ አስተዳደርን፣ የሰብአዊ መብቶችን መስፋፋትና መጠበቅን በሚመለከቱ ህዝባዊ ሰብሰባዎች የመካፈል መብት አላቸው፡፡ እነዚህን መብቶች በስራ ላይ በሚያውሉበት ጊዜ ሁሉ ዐቃብያነ ህግ ራሳቸውን ለህጉና በሙያቸው ለታወቁ መመዘኛዎችና ስርዓቶች ተገዢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዐቃብያነ ህግ የሙያ ማህበራቸውን ወይም ሌሎች ጥቅማቸውን የሚያስጠብቁላቸው ድርጅቶችን በማቋቋምና አባል በመሆን ሙያዊ ስልጠናቸውን ለማስፋፋትና አቋማቸውን ለመጠበቅ የምንቀሳቀስ መብት አላቸው፡፡

2.3.7. አቃቤ ህጎች አጠቃላይ በግል ኑሮአቸው ሊያከብሩት የሚገባ ስነምግባር

1. አቃቤህግ ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶችን የጣሱ ሰዎችን ለፍርድ የሚያቀርብ ከመሆኑ አንጻር እሱም እራሱ በድርጊቱ ሰብአዊ መብቶችንና ነጻነቶችን የሚያከበርና አርአያ መሆን አለበት፡፡
2. አቃቤ ህግ በግል አኗኗሩ ተቋሙን ጥያቄ ውስጥ ከሚከት አኗኗር መጠበቅ አለበት፡፡ ተቋሙ ተገቢውን ክብርና ድጋፍ የሚያገኘው አቃቤ ህጉ በግል አኗኗሩ በሚያሳየው ባህርይ ነው፡፡
3. አቃቤ ህግ የጥቅም ግጭት በሚፈጥር ስራ ውስጥ መግባት የለበትም፡፡ ከሙያው ጋር የሚቃረን ተግባር ተሰማርቶ ገቢን ለማግኘት መሞከር የለበትም፡፡

4. አቃቤ ህግ የፍርድ ቤቱን ነጻነት መቀበልና መጠበቅ አለበት፡፡ የፍርድ ቤትን ውሳኔ ሊቃወመው የሚችለው ይግባኝ በማቅረብ ብቻ እንጂ በአደባባይ በመተቸት አይደለም፡፡

<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>

1. አንድ የምርመራ መዝገብ ተጠናቆ የመጣለት አቃቤ ህግ የተሰባሰቡትን ማስረጃዎች ሲመረምር አንዳንዱ ተከሳሽን የሚጠቅም ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽን የሚጠቅመውን ማስረጃ በማስቀረት በተከሳሽ ላይ ክሱን ለማስረዳት የሚጠቅመውን ማስረጃ ብቻ አያይዞ ክስ ይመሰርታል፡፡ አቃቤ ህግ ተከሳሽን የሚጠቅም ማስረጃ ለተከሳሹ ማሳወቅና መስጠት ይገባው ነበር፡፡ ይህንን ባለማድረጉ የሙያ ስነምግባሩን አላከበረም ይባላል?
2. አቃቤ ህግ በህገወጥ መንገድ የተገኘ ማስረጃ መኖሩን እያወቀ ማስረጃውን ይዞ ፍርድ ቤት ቀረበ፡፡ ይህ የአቃቤ ህግ ድርጊት ሊያስጠይቀው ይገባል ወይ?
3. አቃቤ ህግ በሚመረምረው የምርመራ መዝገብ በቂ ማስረጃ እንደሌለው በሚያውቀው መዝገብ ላይ ክስ መስርተህ ተከራከር የሚል የበላይ ትእዛዝ ቢመጣ ምን ማድረግ አለበት? እንዲህ አይነት ግንኙነት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለማስወገድ ምን አይነት ሲስተም መዘርጋት ይኖርበታል?
4. አቃቤ ህግ በአንድ የወንጀል ድርጊት ክስ በመመስረቱ፣ የወንጀል ድርጊቱ ሰለባ የሆኑ ሰዎች በድርጊቱ በመደሰት ከፍ ያለ ስጦታ ያቀርቡለታል፡፡ እርስዎ አቃቤ ህግ ቢሆኑ ስጦታውን ይቀበላሉ? ለምን?የማይቀበሉ ከሆነስ; ለምን?
5. አቃቤ ህግ ከመርማሪ የመጣለትን መዝገብ ሲመለከት ወንጀሉ የተፈጸመ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይሁንና አቃቤ ህግ በግሉ እንደሚያውቀው ተከሳሽ ሆኖ የቀረበው ወንጀሉን እንዳልፈጸመ ያውቃል፡፡ ምን ማድረግ አለበት? ጉዳዩን ስለማውቀው ብሎ መዝገቡን መዝጋት ነው? ወይስ በጉዳዩ ላይ እኔ ክስ አልመሰርትም ብሎ መተው ነው? ለምን?

ክፍል ሶስት

ስለጠበቆችና የህግ አስከባሪዎች የስነምግባር ደንቦች አንዳንድ ነጥቦች

አላማዎች

ይህንን ክፍል ሲያጠናቅቁ ሰልጣኞች፣

1. ከጠበቆች ስለሚጠበቁ የስነምግባር ደረጃዎች ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
2. ከህግ አስከባሪዎች ስለሚጠበቁ የስነምግባር ደረጃዎች ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

3.1. የጠበቆች የሙያ ስነ ምግባር መርሆዎች

የሰው ልጆች ሁሉ በሰብዓዊ ፍጡርነታቸው የተቸሩትን መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች እንዲጎናፀፉ ለማድረግ ብቃት ያለው የህግ ምክር አገልግሎት የሚያገኙበት መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ እንደሆነ የተባበሩት መንግስታት የህግ ሙያተኞችን ሚና ለመወሰን በደነገገው መሰረታዊ መርሆዎች ላይ በሚገባ ተመልክቷል፡፡[59] የዜጎች መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በተለይም ግልጽና ፍትሃዊ የሆነ ዳኝነትን የማግኘት መብት በተለያዩ የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና መግለጫዎች ላይ የሰፈረ ከመሆኑም ባሻገር በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙና፣ የተከሰሱ እንዲሁም በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎች በተቻለ መጠን ተገቢ የህግ ምክር አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸው መሆኑንና ከጠበቆቻቸውም ጋር የመገናኘትና የመወያየት፣ የውይይቱ ሚስጥራዊነትም እንዲጠበቅላቸው ሙሉ ነፃነት ያላቸው መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በአንድ የፍትህ ስርዓት ውስጥ የዜጎች እኩልነት ተከብሮ፣ ፍትህና ርቱዕ የተሞላበት ዳኝነት እንዲያገኙ ከተፈለገ ሁሉም ዜጎች በተቻለው አቅም ሁሉ የህግ አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻል ለፍትሃዊ የህግ ስርዓት መጎልበትና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በፍትህ ስርዓቱና በህግ የበላይነት ላይም ሰፊው ህብረተሰብ ፅኑ እምነት እንዲያሳድርና የሁሉም ሰው መብት ህግ ባስቀመጠው ወሰንና አግባብ እንዲከበር ጠንካራ የህግ ባለሙያዎች ማህበር ሊኖር የሚገባው ሲሆን

[59] እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ 1990 ዓ.ም የወጣው የተባበሩት መንግስታት የህግ ሙያተኞች ሚና መሰረታዊ መርሆዎች መግቢያ ፓራግራፍ 9ን ይመልከቱ

ከፍተኛ ስነ ምግባር የተላበሱ የህግ ሙያተኞችና ጠበቆችም እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1990 ዓ.ም የወጣው የተባበሩት መንግስታት የህግ ሙያተኞች ሚና መሰረታዊ መርሆዎች ከሚደነግጉት ሁኔታዎች መካከል አንዱና ዋንኛው ሁሉም ሰዎች በወንጀል የፍርድ ሂደት መሰረታዊ መብቶቻቸውን በሚገባ ለማስጠበቅና ራሳቸውን ለመላከል ተደራሽነት ያለው የህግ ምክር አገልግሎትና የህግ አማካሪዎችን ወይም ጠበቆችን በቀላሉ ማግኘት እንደሚገባቸውና መንግስታትም በዚህ ረገድ ያለ አንዳች አይነት አድሎአዊ ልዩነት ሁሉም ዜጎች ይህንን አገልግሎት የሚያገኙበት ውጤታማ ስልቶችና ስነስርዓቶች መቀየስ ይጠበቅባቸዋል፡፡[60]

ከዚህ አኳያ መንግስታት የተለየ ኃላፊነት እንዳለባቸውና ይህ ኃላፊነትም በቂ ገንዘብ በመመደብ ድሆችና ሌሎችም የተገፉ የህብረተሰብ ክፍሎች ነፃ የህግ ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግን ይጨምራል፡፡[61] የህግ ባለሙያዎች ማህበራትና ጠበቆችም በዚህ ረገድ ከመንግሰታት ጋር በመተባበር ነፃ የህግ አገልግሎት ለመግዛት የኢኮኖሚ አቅማቸው ለማይፈቅድ ዜጎች እንዲመቻች ለማድረግ የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ አላባቸው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ሁሉም የህብረተሰቡ ክፍል በህግ ስለተረጋገጠላቸው መሰረታዊ መብቶችና ግዴታዎቻቸው እንዲያውቁ ለማድረግ መንግስትና ጠበቆች እንዲሁም የህግ ሙያተኞች ማህበራት በጋራ መረባረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ በወንጀል የፍርድ ሂደት ውስጥ የተያዙና የተከሰሱ ሰዎች መሰረታዊ መብቶቻቸውና ነፃነቶቻቸው እንዲጠበቁ የማድረግ ኃላፊነት የመንግስት እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር መንግስት በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎች እንደተያዙ ወዲያውኑ በሚመለከታቸው የፍትህ አካላት በሁሉም የወንጀለ ፍትህ አስተዳደር ሂደቶች በፈለጉት ወይም በመረጡት የህግ አማካሪ የመወከልና ተገቢውን የምክር አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳላቸው እንዲያዉቁ መደረጉን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡[62]

በተለይም የመክፈል አቅምን በማጣት ምክንያት የህግ ምክር አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ ግለሰቦች በቂ ልምድና ብቃት ያለው የህግ አማካሪ በመንግስት ወጪ

---

[60] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 1 እና 2 ይመልከቱ
[61] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 3ን መመልከት ይቻላል፡፡
[62] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 5ትን ይመልከቱ

እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡[63] በመንግስት የሚመደብላቸውም የህግ አማካሪ ከተከሰሱበት ጉዳይ ውስብስብነት ጋር በሚመጣጠን መልኩ በቂ ልምድና ችሎታ ያላቸው መሆን ይገባዋል፡፡ ችሎታቸውና ልማዳቸው እምብዛም ያልሆነ የህግ አማካሪዎችን መመደብ በዚህ ረገድ በመንግስት ላይ የተጣለውን ኃላፊነት መንግስት በሚገባ እንዳልተወጣው ነው የሚያስቆጥረው፡፡ በርግጥ በአብዛኛው በወንጀል ጉዳዮች ላይ ነው የመክፈል አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች በመንግስት ወጪ ጠበቃን ማቆም የሚገባው፡፡ ይሁን እንጂ ከወንጀል ጉዳይ ዉጪ በሆነ መልኩ ለተያዙ ግለሰቦች በመንግስት በነፃ ጠበቃ የማቆም ግዴታ እንዳለበት ነው ተደንግጎ የሚገኘው፡፡[64] በአለም አቀፍ መርሆዎች የተደነገገው ደረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ በተለይም የተያዙ ሰዎች ጠበቃ የማቆም አቅም በማይኖራቸው ጊዜ መንግስት በተቻለው አቅም ሁሉ ከተያዙበት ጊዜ አንስቶ በ48 ሰዓታት ውስጥ ነው ነፃ የህግ አገልግሎት የሚሰጣቸውን የህግ አማካሪ ሊመደብላቸው የሚገባው፡፡ ከዚህ የምንረዳው በሁሉም የፍርድ ሂደቶች ዜጎች በህግ አማካሪ ሳይወከሉ በፍርድ ሂደት እንዳያልፉ የሚደረግ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አቅም ያጡ ግለሰቦች በድህነታቸው ምክንያት ብቻ የህግ ምክር ሳያገኙ በማንኛውም የፍርድ ሂደት እንዲሳተፉ ወይም ለፍርድ እንዲቀርቡ ከተደረገ የሁሉም ሰዎች ፍትሃዊ፣ሚዛናዊ ግልፅ የሆነ ዳኝነት የማግኘት መብት ተከብሯል ለማለት አያስደፍርንም፡፡

የተያዙ ሰዎች በእስር ወቅት በመንግስት ከተመደበላቸው የህግ አማካሪ ጋር የሚገናኙበትና በነፃነት የሚወያዩበት በቂ እድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እነዚህ ሰዎች ከህግ አማካሪዎቻቸው ወይም ጠበቆቻቸው ጋር የሚያደርጉት ምክክርና ውይይት በየትኛውም መልኩ በህግ አስከባሪ ባለስልጣናት ሊደመጥና ይዘቱም ቅድመ ምርመራ ሊደረግበት አይገባም፡፡[65]

ጥብቅና ከፍተኛ ኃላፊነት የሚያስከትልና በፍትህ አስተዳደር ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ሙያ በመሆኑ ከጠበቆች ከፍ ያለ ስነ ምግባር ነው የሚጠበቀው፡፡ ከዚህም የተነሳ ጠበቆች በግል ህይወታቸውም ጭምር የሙያውን ክብርና ዝና ከሚያጎድፉ ባህሪያት ራሳቸውን ማግለልና በሚገባ መጠበቅ አለባቸው፡፡ ከዚህም አልፍው የሙያ

---

[63] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 6ትን ይመልከቱ
64 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 7ን መመልከት ይቻላል፡፡

[65] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 8ትን ይመልከቱ

ባልደረቦቻቸው የስነ ምግባር ጉድለት እንዳያሳዩ የመምከርና የስነ ምግባር ጉድለት ፈፅመው ሲገኙ ደግሞ ለተገቢው አካል የመጠቆም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ለዚህ ነው ጠበቆች ሁሌም ቢሆን የሙያቸውን ክብርና ዝና በመጠበቅ የፍትህ አስተዳደሩ ዋልታ መሆን ይገባቸዋል የሚባለው፡፡[66] አንድ ጠበቃ የሙያውን ክብርና ዝና ለመጠበቅ የሚከተሉትን እሴቶች ማክበር፣ በተግባርም ማሳየት ይኖርበታል፡፡

- ሙያዊ ነፃነትን፣ ገለልተኝነትን ቅንነትን በስራው ላይ በተጨባጭ ማሳየት፣
- የባለጉዳዩን ምርጫ ፣ፍላጎትን ጥቅም በማስቀደም በርሱ ፍላጎት መሰረት የጥብቅናውን ስራ ማከናወን፣
- የባለጉዳዩን ጥቅም በተቻለ መጠን ሁሉ ለማስጠበቅ ትጋት ማሳየትና ተገቢውን ጥረት ማድረግ፣
- የሙያውን ወይም የራሱን ክብና ዝና በሚያስጠብቅ መልኩ የግል ህይወቱን መምራት፣
- የጥብቅና ስራ የሚጠይቀውን ሙያዊ ኃላፊነትና የስራ ደረጃ አሟልቶ መገኘት፣
- በክርክር ሂደት ለዳኝነት አገልግሎቱ ውጤታማነት ሲባል ፍ/ቤቶች ከፍትሃዊ ውሳኔ እንዲደርሱ ያለበትን ግዴታና ኃላፊነት መወጣት ናቸው፡፡

ጠበቆች የባለጉዳዮች ወኪል ብቻ ሳይሆኑ የፍትህ አስተዳደሩም ዋልታ በመሆናቸው ጭምር ፍርድ ቤቶች በእውነት ላይ እንዲያደርሱና ፍትሃዊና ሚዛናዊነትን የተላበሰ ውሳኔ እንዲሰጡ መርዳት አለባቸው፡፡

ከዚህ አንፃር የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች ስነ ምግባር ደንብ የሚከተሉትን ግዴታዎች በጠበቆች ላይ ጥሏል፡፡[67]

- በምቀኝነት ወይም በክፉ ልቦና ተነሳስቶ ሌላውን ወገን የሚጎዳ ክስ ወይም ክርክር አለማቅረብ፣
- ደንበኛው የወራዳነት ወይም የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈፅም አለማበረታታት ወይም አለመፍቀድ፣

---

[66] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 12

[67] የፌዴራል ነጋሪትጋዜጣ 6ኛ አመት ቁጥር 1 የፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች የስነምግባር ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 56 ይመልከቱ

- ዳኛን ወይም ሌላ የፍ/ቤት ሰራተኛን በህግ መሰረት ከማሳመን ውጪ ሌላ ተገቢ ያልሆነ ማንኛውም አይነት ዘዴ በመጠቀም ተፅህኖ ለማሳደር አለመሞከር ወይም ሌላ ሰው እንዲሞክር አለመገፋፋት ፣
- ሆነ ብሎ ፍ/ቤትን የሚያሳስት የተጋነነ ፅሁፈ ንግግር ለፍርድ ቤት አለማቅረብ፣
- በምስክርነት ቃል ወይም የሰነድ ይዘት ላይ የሀሰት ድርጊት በመፈፀም ፍርድ ቤትን ለማሳሳት አለመሞከር፣
- በግልፅ ለጉዳዮ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ አግባብነት ያለው አስመስሎ ለፍርድ ቤት አለማቅረብ፣
- ለጉዳዮ በምስክርነት መቅረብ የሚገባው ሰው ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ አለማባበል ወይም አለመሞከር
- አንድን ምስክር ተገቢ ባልሆነ መንገድ አለማመናጨቅ፣ አለማስጨነቅ፣ወይም አለማስፈራራት ናቸው።

በጥቅሉ የባለጉዳይን ጥቅም ከማስጠበቅ የተሻገረ ኃላፊነት እንዳለበት አውቆ ፍርድ ቤቱ ከእውነተኛና ፍትሃዊ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ የሚጠበቅበት ሲሆን የጥብቅና ስራውንም በቅን ልቦና ማከናወን ይጠበቅበታል።

ሌላኛውና ዋንኛው የጠበቆች የስነ ምግባር ግዴታ ጠበቆች ከደንበኞቻቸው አንፃር ያለባቸው ግዴታ ነው።[68] በዚህ ረገድ የጠበቆች ዋንኛ ግዴታ የሚሆነው ባለጉዳዮች ዳኝነት ከጠየቁበት የክርክር ጭብጥ አንፃር ያላቸውን መብትና ግዴታ እንዲሁም መብታቸውን ለማስከበርና ግዴታቸውን ለመወጣት ህጉ የሚደነግጋቸውን አካሄዶችና ስነ ስርዓቶች እንዲያውቁ ማድረግ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የባለጉዳዮችን መብትና ጥቅም ለማስከበር እነርሱን ወክሎ ክርክር በማቅረብ መብታቸውና ጥቅማቸው እንዲከበር ዕውቀቱንና የስራ ልምዱን ስራ ላይ ማዋል ነው። ከዚህም በላይ የደንበኛውን ጉዳይ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ የዳኝነት አካላት ዘንድ በመውሰድ የደንበኛውን ጉዳይ በትጋት መከታተል፣ አፋጣኝና ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲያገኝም ሙያዊ ጥንቃቄ ብርቱ ጥረት ማድረግ ይገባዋል። በዚህ ሂደት ውስጥም ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ በየጊዜው ለደንበኛው የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

---

[68] እንዴኤ አ በ1990 የወጣውን የተባበሩት መንግስታት የህግ ሙያተኞችን ሚና መሰረታዊ መርሆዎች አንቀጽ 13

ጠበቆች ሁሌም ቢሆን የደንበኞቻቸው ጥቅም ለማስጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ለደንበኞቻቸው ጥቅም መከበርም በፍፁም ታማኝነት ማገልገል ይጠበቅባቸዋል፡፡[69]

በዚህ ረገድ በጠበቃውና በደንበኛው፣ ወይም በጠበቃው ዘመዶችና በደንበኛው፣ወይም ጠበቃው በወከላቸው የተለያዩ ደንበኞች መካከል የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በጥብቅና አገልግሎቱ ምክንያት ያወቃቸውን የደንበኛውን የግል ወይም የስራ ሚስጥሮችን መጠበቅ አለበት፡፡ ደንበኛው ሳይፈቅድለት በሙያው ምክንያት እጁ የገቡትን ማናቸውንም የደንበኛውን ሚስጥሮች ለሌላ አካል አሳልፎ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ራሱም ቢሆን በህግ በተፈቀዱለት ጥቂት ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር ሊጠቀምበት አይችልም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ጠበቆች ለሌሎች ሶስተኛ ወገኖችም ቅን የመሆን ግዴታ አለባቸው፡፡ በተለይም ሌሎች ተከራካሪዎችን ለማጉላላት በማሰብ አከራካሪ የሆነ ጭብጥ ወይም በሌላኛው ተከራካሪ ላይ ኃላፊነትን ሊያስከትል የሚችል ውጤት የሌለ መሆኑ በግልፅ አኳኋን የሚታይበት ሁኔታ ቅንነትን በማጣት ተገቢ ያልሆነ ክርክር በተቃራኒ ወገኖች ላይ መጀመር የለበትም፡፡[70] ከዚህ አንፃር በተለይም ከዚህ በታች ከተገለፁት ድርጊቶች መቆጠብ አለበት፡፡ እነዚህም፡-

- ተቃራኒ ወገን ማስረጃ እንዳያገኝ ማንኛውንም እንቅፋት መፍጠር ወይም ሌሎች ሰዎች ይህን መሰል አድራጎት እንዲፈፅሙ መሞከር ወይም መረዳት፣
- ማስረጃን ማሳሳት ወይም ሌሎች ሰዎች ይህን መሰል አድራጎት እንዲፈፅሙ መሞከር መርዳት፣
- ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለው ወይም በማስረጃ ሊደገፍ የማይችል ነገር ማቅረብ
- በምስክርነት ካልቀረበ በቀር በግል የሚያውቀውን የጭብጥ ነገሮች መሰንዘር ወይም የጉዳዩን ፍትሃዊነት የአንድን ምስክር ተዓሚነት፣ የተከሳሽን ጥፋተኛ ወይም ተጠያቂ መሆንና አለመሆን አስመልክቶ የግል አስተያየቱን መስጠት
- ደንበኛው ወይም ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ የማይገደዱ ሰዎችን በተመለከተ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ማንኛውንም ሰው ለተቃራኒ ወገን የምስክርነት ቃሉን ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ማስረጃ እንዳይሰጥ መገፋፋት ናቸው፡፡

---

[69] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 15

[70] የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 6ኛ ዓመት ቁጥር 1 የፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች የስነ ምግባር ደንብ የሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀፅ 28 እና 29ን ይመልከቱ፡፡

በመጨረሻም ጠበቆችም ፍትሃዊ ዳኝነት እንዲጎለብት እንዲሁም የደንበኞቻቸው መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ የማድረግ ድርብ ኃላፊነት ሲኖርባቸው እነዚህን ኃላፊነቶች በተጣጣመ መልኩ ነው ማከናወን ያለባቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ለሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች መከበር በትጋት መቆምና መስራት ይኖርባቸዋል፡፡[71] በዚህ ረገድ የደንበኛቸውን ጥቅም ማስጠበቅና ለፍትህ መከበርም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ መካከል የሚታየውን ክፍተት ለማጣጣመና ሚዛናዊ ለማድረግ መጣር አለባቸው፡፡ ጠበቆች ሙያቸው የግለሰቦች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች እንደከበሩና እንዲጐለብቱ የማድረግ ልዩ ኃላፊነት ወይም ግዴታ እንደጣለባቸው በመገንዘብ ይህንን ከፍተኛ የሙያ ግዴታ ለመወጣት ከፍተኛ ስነምግባር መላበስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለፍትህ ሥርዓቱ መጐልበትና ለሰብዓዊ መብቶች መከበርም ዘወትር የበኩላቸውን ድርሻ ለማበርከት መሥራት እንደሚገባቸውና በዚህ ሂደት ውስጥም ለሙያቸው ስነምግባር መገዛት እንደሚጠበቅባቸው ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የሕግ አስከባሪ አካላት የስነምግባር መመሪያዎችን በተመለከተ ያሉ ዓለምአቀፍ መርሆዎች

በተባበሩት መንግሥታት የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የስነምግባር መመሪያ ላይ እንደተመለከተው ከሆነ የሕዝብን ደህንነትና ፀጥታ ለማስከበር የሚደረጉ የሕግ ማስከበር ስራዎች በግለሰቦችም ሆነ በህብረተሰቡ አኗኗር ላይ የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ ከግምት በማስገባት የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የሰብዓዊ መብቶችን ጥበቃ መርሆዎች ተከትለው በጥንቃቄና ሰብዓዊ ክብር ባልተለየው ሁኔታ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ለማድረግ የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የሚመሩበትን የተግባር መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ነው፡፡[72] በተለይም ከህግ አስከባሪ አካላት አገልግሎት የሚያገኙ ዜጐች መሰረታዊ መብቶች እንዲከበሩና ጥቅሞቻቸው እንዲጠበቁ በማድረግ ረገድ ያለው ፋይዳ የላቀ ነው፡፡

---

[71] እንዴኤ አ በ1990 የወጣውን የተባበሩት መንግስታት የህግ ሙያተኞችን ሚና መሰረታዊ መርሆዎች አንቀጽ 14

[72] በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ ቁጥር 34/169 እ.ኤ.አ ዲሴምበር 17/1979 ዓ.ም የፀደቀውን የሕግ አስከባሪ አካላት የስነምግባር መመሪያ መግቢያ ፐራግራፍ 4፣5 እና 7ን ይመለከቱ፡፡

የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት በስልጣናቸው ያለ አግባብ ሳይጠቀሙ የሕግ ማስከበር ኃላፊነታቸውን በአግባቡና ሰብዓዊ በሆነ አሰራር ለማከናወን እንዲችሉ የሚከተሉትን ርምጃዎች መውሰድ ጠቃሚነት እንዳለው ሊታወስ ይገባል፡፡

- የወንጀል ድርጊቶች ታይተውና ተመርመረው ውሣኔ የሚሰጥበት የፍትህ ስርዓት ተቋማት እንደሚያደርጉት ሁሉ እያንዳንዱ ሕግ ለማስከበር የሚደራጅ ተቋማት ሕብረተሰቡን በጠቅላላ እንዲወክል፣ ለሕብረተሰቡ ችግሮች መፍትሄ የሚፈልግና ተጠሪነቱም ለሕብረተሰቡ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡
- የሕግ አስከባሪ ሃይሎችን የመንፈስ ልዕልና በተሳካ ሁኔታ ጠብቆ ማቆየት የሚቻለው መሰረቱ ትክክለኛ የሆነ፣ ሕዝብ የተቀበለውና ሰብዓዊ የሆነ የሕግ ስርዓት እንዲኖር ሲደረግ ነው፡፡
- እያንዳንዱ የሕግ አስከባሪ ባለስልጣን ዓላማው የወንጀል ድርጊቶችን ማስቆም፣ እንዳይፈፀሙ ማድረግና መቆጣጠር እንደመሆኑ፣ እንዲሁም የወንጀል ጉዳዮች የሚታዩበትና የሚመረመሩበት የፍትህ ሥርዓት አካል በመሆኑና የእያንዳንዱ በስርዓቱ ውስጥ የሚገኝ ባለስልጣን ስነምግባር በጠቅላላ በስርዓቱ ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል መገመትና በዚህ ረገድ ሊፈጠር የሚችለውን አሉተዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ ተጨባጭ ርመጃዎችን መውሰድ ተገቢ ነው፡፡

የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት በሚወስዷቸው ርምጃዎች አንፃር በተባበሩት መንግሥታትን የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የተግባር መመሪያዎች መመራት ያለባቸው ከመሆኑም ባሻገር በእነዚህ አካላት የሚወሰዱ ርምጃዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች መታየት የሚኖርባቸው፣ በቅሬታ ሰሚ ቦርድ፣ በፍትህ ሚኒስቴር፣ በፍርድ ቤቶች፣ በዕንባ ጠባቂ ተቋም፣ በዜጎች ኮሚቴ ወይም ከነዚህ አካላት ተውጣጥቶ በተቋቋመ አካል ሊሆን ይገባል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የተግባር መመሪያዎች የሕግ አስከባሪ አካላት በዕለት ተዕለት ሥራቸው ውስጥ ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው መንግሥታት እነዚህን የተግባር መመሪያዎች በብሄራዊ ሕጎቻቸው ሊያካትቷቸው ይገባል፡፡

የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት ሕብረተሰቡን ለማገልገልና ሁሉንም ሰዎች ከሕገወጥ ድርጊቶች ለመጠበቅ በሕግ የተጣለባቸውን ከፍተኛ ኃላፊነት ሁልጊዜም የሙያ ግዴታቸው በሚጠይቀው ሁኔታ ሊወጡ ይገባል።[73] ሙያቸው የሚጥልባቸውን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት ሁሌም ቢሆን ሁሉም ሰዎች ከሕገወጥ ድርጊት ወይም ጥቃት እንዲጠበቁ የማድረግ ልዩ ኃላፊነት አለባቸው።

የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የሕዝብ አገልጋዮች እንደመሆናቸው መጠን ሕብረተሰቡንና ግለሰቦችን ከማናቸውም ዓይነት ጥቃት መከላከል ይጠበቅባቸዋል። የህግ አስከባሪ አካላት በምንልበት ጊዜ የፖሊስ ስልጣን የተሰጣቸው በተለይም የመያዝና የማሰር ስልጣንን ጨምሮ ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት አስፈላጊ ኃይል የመጠቀም ስልጣን ያላቸው ተሹዋሚዎች ወይም ተመራጮች ናቸው። በእኛ ሀገር ሁኔታ የፖሊስ ተቋማትና ማረሚያ ቤቶችን ይጨምራል። በርግጥ የፖሊስነት ስልጣን በተሰጣቸው ጊዜ የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የሚለው አገላለጽ የጦር ሠራዊትና የፀጥታ ኃይሎችንም ሊጨምር እንደሚችል ነው የተባበሩት መንግሥታት የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የስነምግባር መመሪያ የሚመለከተው። እነዚህ አካላት ሕግን ከማስከበር አልፈው የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ በአንድ ማህበረሰብ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት በሚያደርስበት ጊዜ ያንን ሕብረተሰብ ከአደጋ መታደግን ማዕከል ያደረገ ሕዝባዊ አገልግሎት ያበረክታሉ። ለዚህም ነው እነኚህ አካላት ሕግ አስከባሪ ብቻ ሳይሆኑ ሕዝባዊ አገልግሎት [community service] የሚሰጡ ተቋማት ናቸው የሚባለው። ለሕብረተሰቡ የሚሰጥ አገልግሎት በተለይ የግል፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ሌሎች ድንገተኛ ችግሮች ለደረሰባቸው የሕብረተሰቡ አባላት የሚደረገውን ዕርዳታ ይጨምራል። የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሁሉንም ሰዎች ሰብዓዊ ክብርንም ሆነ ሰብዓዊ መብቶችን ሊያከብሩ ይገባል።[74] በዚህ ረገድ የግለሰቦችን መሠረታዊ መብትና ነፃነት ከሚፃረር የኃይል ድርጊት መቆጠብ ይኖርባቸዋል። በተለይም በብሄራዊ ሕጎችና ዓለምአቀፍ ሕጎች ጥበቃ ያገኙትን የሰብዓዊ መብቶች በሚገባ ማወቅና ማክበር እንዲሁም ማስከበር ከሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የሚጠበቅ ሙያዊ ግዴታ ነው።

---

[73] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 1 ያንብቡ
[74] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 2

ስለዚህም አንዱና ዋነኛውም የስነምግባር ግዴታቸው የሰዎችን ሰብዓዊ መብቶች ማክበርና መጠበቅ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ሲባል የሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የሰብዓዊ መብቶችን ለይተው በማወቅ እንዲያከብሩና እንዲያስከብሩ ለማድረግ ስለ ሰብዓዊ መብቶች የተደነገጉ ሀገራዊ፣ ክፍለ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ ድንጋጌዎችንና በነዚህም ውስጥ የሰፈሩ መሰረታዊ መብቶችን እንዲያውቁ ማድረግ የመንግሥት ሃላፊነት መሆን አለበት፡፡

ሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት የኃይል እርምጃን መጠቀም የሚችሉት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ ብቻ ሲሆን ይህም ለሥራው አፈፃፀም በሚያስፈልገው ኃይል ልክ የተወሰነ ይሆናል፡፡[75] ሕግ አስከባሪ ባለስልጣናት በኃይል ሊጠቀሙ የሚችሉት እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ብቻ ነው፡፡ ይኸውም የወንጀል ድርጊት እንዳይፈፀም ለመከላከል ሲባል የወንጀል ድርጊት ፈፃሚዎችን ወይም ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩ ሰዎችን ሕግ በሚፈቅደው መሰረት ለመያዝ ወይም እንዲያዙ ለመርዳት ሕግ አስከባሪዎች ከሁኔታዎች ጋር የተመጣጠነ ሀይል ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ሕጉ ቢያመለክትም ሁኔታዎች ከሚጠይቁት መጠን ያለፈ ኃይል ግን ሊጠቀሙ አይችሉም፡፡

---

80 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 2 ን ይመልከቱ፡፡
81 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 3ን ይመለከቱ፡፡

በብዙ ሀገራት ብሄራዊ ሕጎች ላይ ሕግ አስከባሪዎች ሊጠቀሙ የሚገባውን ኃይል "ተመጣጣኝ የሆነ " በሚል ገደብ የተበጀለት ሲሆን ለዚህ ቃል የሚሰጠው ትርጓሜ በተቻለው መጠን ሁሉ ጠበብ ተደርጐ የሕጉን ዓላማ ለማስፈፀም በቂ የሆነውን ኃይል ለማለት እንደተፈለገ ተወስዶ የሕጉን ዓላማ ከማስፈፀም ጋር የማይመጣጠን የኃይል አጠቃቀምን እንደማይፈቅድ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ከዚህም በመነሳት የሕግ አስከባሪዎች ኃይልን መጠቀም የሚችሉት በጣም ውሱን በሆኑ ሁኔታዎች ብቻ ማለትም ወንጀልን ለመከላከል ወይም የወንጀል ድርጊት የፈፀሙ ግለሰቦችን ይዞ ለሕግ ለማቅረብ በሚያስፈልግበት ጊዜ ነው፡፡ በጦር መሣሪያ

---

[75] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 3

መጠቀም ሌላ አማራጭ ሲጠፋ ሊወሰድ የሚገባው የመጨረሻ አማራጭ ነው ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው፡፡ በተለይም በሕፃናት ላይ በጦር መሣሪያ መጠቀምን ለማስቀረት የሕግ አስከባሪዎች የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው፡፡ የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦች እንዳይያዙ በጦር መሣሪያ የሚከላከሉ ካልሆነ በስተቀር ወይም ለሌሎች ሕይወት አደገኛ ካልሆኑና አነስተኛ የኃይል እርምጃ ተወስዶ ተጠርጣሪዎቹን ለመያዝ ወይም ድርጊታቸውን ለመግታት የማይቻል ካልሆነ በስተቀር በጦር መሣሪያ መጠቀም ተገቢነት የለውም፡፡ የሕግ አስከባሪዎች የጦር መሳሪያን ለመጠቀም የሚያስገድዳቸው ሁኔታ ከተፈጠረና የዚህ አይነቱንም እርምጃ የወሰዱ እንደሆነ ወዲያውኑ ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት ስለሁኔታው ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በህግ አስከባሪ ባለስልጣን ይዞታ ስር የሚገኙ ሚስጥርነት ያላቸው ጉዳዩች ግዴታን ለመወጣት ወይም ፍትህ የሚጠይቀውን ለማሟላት የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ሚስጥርነታቸው እንደተጠበቀ ይቆያሉ፡፡[76] ከያዙት የስራ ኃላፊነት የተነሳ የህግ አስከባሪዎች የሰዎችን የግል ህይወት የሚመለከቱ ወይም ለጥቅማቸውና ለመልካም ዝናቸው ጎጂ ሊሆኑ የሚችሉ መረጃዎችን ያገኛሉ፡፡ እነዚህን መረጃዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊጠብቁ ይገባል፡፡ ለሌሎች ወገኖች የሚገልፁትም የስራ ኃላፊነትን ለመወጣት ወይም ፍትህ ለማስፈን በጣም አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የህግ አስከባሪዎች በስራ አጋጣሚ በእጃቸው የገቡትን መረጃዎች ሚስጥራዊነት በሚገባ መጠበቅ የሙያ ግዴታቸው ነው፡፡

ማንኛውም የህግ አስከባሪ ባለስልጣን የማሰቃየትና ጭካኔ የተሞላበት፣ ሰብአዊነት የሌለውና ሰብአዊ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ሊፈፅም ወይም እንዲፈፅም ማነሳሳት፣ ወይም ሲፈፅም አይቶ ማለፍ የማይገባው ሲሆን ለዚህም በምክንያትነት የበላይ አካል ትዕዛዝን፣ጦርነትን፣የጦርነትን ስጋትን ፣ የሀገር ፀጥታን መደፍረስን ፣ የውስጥ ፖለቲካ አለመረጋጋትን ወይም ማንኛውንም በህዝብ ደህንነትና ፀጥታ ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ አስቸኳይ ሁኔታወችን ቢያቀርብም ተቀባይነት የለውም፡፡[77] እንደዚህ አይነቱን ድርጊት መፈፀም በሰብአዊ ክብር ላይ የወንጀል ድርጊት መፈፀም በመሆኑ የተባበሩት መንግስታት ቻርተርንና የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን የሚጥስ

[76] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 4ን ይመልከቱ፡፡
[77] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 5ን ይመልከቱ፡፡

ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በጥብቅ የተወገዘ ነው፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባሉ የሚገባቸው ሁለት አገላለጾች ከህግ አስከባሪ ባለስልጣናት ግዴታ አንፃር ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ ማጤን አስፈላጊ ነው፡፡

“ማሰቃየት” ማለት ከራሱ ወይም ከሌላ ሶስተኛ ወገን መረጃ ለማግኘት ፣ወይም ፈፅሟል የተባለውን ጥፋት ወይም ድርጊት እንዲናዘዝ ለማድረግ በአንድ ሰው ላይ ሆነ ብሎ የአካል ወይም የአእምሮ ስቃይ የሚያደርስ ድርጊት መፈፀም፣ ራሱ ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን ለፈፀመው ወይም ፈፅሟል ተብሎ ለተጠረጠረው ድርጊት በማስፈራራት ወይም በማስገደድ በመንግስት ባለስልጣን ወይም የመንግስት ስልጣን ይዞ በሚሰራ ሰው ወይም በርሱ አነሳሽነት፣ ስምምነት ወይም አውቆ እንዳላወቀ በመምሰል በሚፈፀም ማንኛውም የማሰቃየት ድርጊት ነው፡፡[78]

“ጭካኔ የተሞላበት፣ ሰብአዊነት የጎደለው ወይም ሰብአዊ ክብርን የሚያወርድ አያያዝ ወይም ቅጣት” የሚለው ሀረግ በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ የተለየ ትርጉም የተሰጠው ባይሆንም በስልጣን ያላአግባብ በመጠቀም በአካል ወይም በአዕምሮ ላይ የሚፈፀሙትን ጭካኔ የተሞላባቸውን፣ ሰብአዓዊነት የጎደላቸውን ወይም ሰብአዊ ክብርን የሚያዋርዱ ድርጊቶች ሁሉ በተቻለ መጠን ለመከላከል እንዲያስችል ተደርጎ ነው ሊተረጎም የሚገባው፡፡ ከዚህ ጋር ተያያዞ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ሌላው ቁምነገር በህግ አግባብ ወይም በፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተመስርቶ በማረሚያ ቤቶች ውስጥ በእስረኞች ላይ የሚፈፀመው የቅጣት እርምጃ አይጨምርም፡፡

ህግ አስከባሪ ባለስልጣናት በቁጥጥራቸው ስር የሚገኙ ሰዎች ጤንነት መጠበቁንና ተገቢውን እንክብካቤ ማግኘታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ በሚያስፈልግበት ጊዜ ሁሉ ወዲያውኑ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡[79] የህግ አስከባሪዎች እስረኞች ወይም በህግ ቁጥጥር ስር ያሉ ሰዎች የህክምና አገልግሎት በጠየቁና ባስፈለጋቸው ጊዜ እንዲያገኙ

---

[78] እ.አ.አ በሴፕቴምበር 10 1984 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ ቁጥር 39/46 ተላልፎ በአባል ሀገራት የተፈረመው ማሰቃየትንና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ሰብዓዊነት የጐደላቸውና አዋራጅ የሆኑ አያያዞችንና ቅጣቶችን ለማስቀረት የተደረገውን ስምምነት አንቀጽ 1 /1/ በዝርዝር እንዲመለከቱ ተጋብዘዋል፡፡

[79] በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ ቁጥር 34/169 እ.አ.አ ዲሴመበር 17/1997 ዓ.ም የፀደቀውን የሕግ አስከባሪ አካላት የስነምግባር መመሪያ አንቀጽ 6ን ይመልከቱ

ማድረግ አለባቸው። ከዚህም አልፈው የእስረኞች ጤንነት እንዲጠበቅ ተገቢውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ ይገባቸዋል።

የህግ አስከባሪ ባለስለጣናት ከሙስና ነፃ ሊሆኑ ይገባል። እንደዚህ አይነቱን ድርጊት በጥብቅ መቃወምና መዋጋት ይኖርባቸዋል።[80] የህግ አስከባሪዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነትና የህዝብ አደራ ከፍተኛ በመሆኑና ህግን ለማስፈፀምም ከየትኛውም የመንግስት አካል ይልቅ በዕለት ተዕለት ተግባራቸው ምክንያት ልዩ ቅርበት ስላላቸው ከሙስናና አድሎአዊ አሰራር መራቅ አለባቸው። ይህንን የማያደርጉ እንደሆነ በህግ ልዕልና ላይ ዜጎች ፅኑ እምነት እንዳይኖራቸው ስለሚያደርግ የህግ ተገዢነትን በእጅጉ ይጎዳል። ለስርዓት አልበኝነትም በር ሊከፍት ይችላል። እንዲሁም መንግስታት በራሳቸው ባለስልጣናት በመዋቅራቸው ውስጥ ሊያከብሩት ያልቻሉትን ህግ ዜጎች እንዲያከብሩላቸው መጠበቅ ስለሚገባቸው ህጉ ሙስና በሚፈፅሙ የህግ አስከባሪዎች ላይም በእኩል ደረጃ ተፈፃሚነት ሊኖረው ይገባል። በሌላ አነጋገር ሙስና የህግ አስከባሪ ባለስልጣናት ካለባቸው የሙያ ግዴታና ከፍተኛ ኃላፊነት ጋር ስለማይጣጣም የህግ አስከባሪዎች ከሙስና እና አድሎአዊ አሰራር ነፃ መሆን አለባቸው።

---

[80] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 7

<u>ዋቢ ጽሁፎች</u>

1. Vincent Barry, philosophy a Text with Readings (2nd, 1983).
2. Robert H.Aronson andDonald T.Weckstein, Professional REsponsibility in a Nutshell,(2d,1991)
3. A.G.Griffith, The Politics of the Judiciary,3rd ed.,1985
4. Paul Mageean, Belfast, The ROLE AND INDEPENDENCE OF PROSECUTORS Northern Ireland 17 th May 2005, Cairo
5. Transparency International, Global Corruption Report 2007
6. UN BANGALORE PRINCIPLES OF JUDICIAL CONDUCT, 2006
7. THE JUDICIAL INTEGRITY GROUP, COMMENTARY ON THE BANGALORE PRINCIPLES OF JUDICIAL CONDUCT,2007
8. International Association of Judges, The Universal Charter of the Judge, 1999.
9. Canadian Guide to judicial conduct.
10. International Association of Prosecutors, Standards of professional responsibility and statement of the essential duties and rights of prosecutors, April 1999.
11. UN Guidelines on the Role of Prosecutors,1990
12. **UN Code of Conduct for Law Enforcement Officials,1979**
13. የተባበሩት መንግስታት የህግ ሙያተኞች ሚና መሰረታዊ መርሆዎች,1990
14. የፌዴራል ነጋሪትጋዜጣ 6ኛ አመት ቁጥር 1 የፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች የስነምግባር ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992
15. ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስነምግባር ስልጠና ማንዋል፣ግንቦት 1999 አዲስ አበባ
16. ፈ.ስጸኮ፣ የሙያ ስነምግባር ምንነት (ያልታተመ)
17. የስነምግባር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም ሰነድ ቅጽ 2

አባሪዎች

አባሪ 1

የፌዴራል ዳኞችን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች

አዋጅ ቁ 24/88

አንቀጽ 5 (3)

የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ዳኞች የሚመሩበትን የስነምግባር ደንብ ያወጣል፡፡

አንቀጽ 8 (1)

ለዳኝነት ለመመረጥ የሚያበቁ ሁኔታዎች

1. ለህገመንግስቱ ታማኝ የሆነ
2. በህግ ትምህርት የሰለጠነ ወይም በቂ እውቀት ያለው
3. በታታሪነቱ በፍትሀዊነቱና በስነምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ
4. በዳኝነት ሙያ ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ እና
5. እድሜው ከ25 አመት ያላነሰ

አንቀጽ 8(2)

ማንኛውም ሰው በመንግስት ህግ አውጪ ወይም አስፈጻሚ ውስጥ ወይም በማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት በአባልነት በሚያገለግልበት ጊዜ አጣምሮ የዳኝነት ስራ ሊሰራ አይችልም፡፡

አንቀጽ 11

ቃለ መሀላ

ዳኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት የሚከተለውን ቃለ መሀላ ይፈጽማሉ፡፡

እኔ....... በዛሬው እለት......ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ተሸሜ ስራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ሀላፊነት በታማኝነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁ፡፡

አዋጅ ቁጥር 25/88

አንቀጽ 27 የዳኞች ከችሎት መነሳት

1. አንድ የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኛ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ከችሎት ይነሳል፡፡
   ሀ. ዳኛው ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፣
   ለ. ዳኞች ከተከራካሪዎች የአንደኛው ወገን ሞግዚት፣ ነገረፈጅ፣ ወይም ጠበቃ በሆነበት ጉዳይ ላይ የተነሳ ክርክር እንደሆነ፣
   ሐ. ዳኛው ክርክር የተነሳበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ወይም በእርቅ መንገድ ያየው ወይም የሚያውቀው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣
   መ. ዳኛው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች ከአንደኛው ወይም ከጠበቃው ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለው እንደሆነ፣
   ሠ. ከዚህ በላይ ከ(ሀ) እስከ (መ) ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ ትክክለኛ ፍትህ አይሰጥም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር፣
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ዳኛው በችሎት ሊቀመጥ የማይገባው መሆኑን ሲያውቅ ከችሎት ተነስቶ ሌላ ዳኛ መተካት አለበት፡፡

ጥር 16/1993 የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የወጣው የዳኞች ስነምግባር ደንብ

አንቀጽ 4. **ህጎችን በትክክል ስራ ላይ ማዋል**

በሚሰጠው ፍርድ ውሳኔና ትእዛዝ ሁሉ በአገሪቱ የወጡት ህጎች በትክክል ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ የዳኛ ተቀዳሚ ተግባሩ ነው፡፡ በተለይም ወደነገሩ ከመግባቱ በፊት ስልጣኑ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡

አንቀጽ 5 **የባለጉዳዮችን መብት በእኩልነት መጠበቅ**

ዳኛ ፍርድ ቤት የሚቀርቡለትን ተከራካሪዎች ሁሉ በእኩልነት ማየትና መብታቸውን በእኩልነት መጠበቅ አለበት፡፡ ስለዚህም የቤተሰብ የሀይማኖት የብሄር የብሄረሰብ

የፖለቲካ የማሕበራዊ ወይም ሌሎች ግንኙነቶቹ በዳኝነት ተግባሩ ላይ ተጽእኖ እንዲያሳድሩ መፍቀድ የለበትም።

አንቀጽ 6. <u>ትጋትና ጥረት ማሳየት</u>

ዳኛ በዳኝነት ስራው ላይ ተገቢውን ትጋትና ጥረት ማሳየት፣ እንዲሁም ስለህግ ያለውን እውቀት ለማዳበር ዘወትር ጥረት ማድረግ አለበት።

አንቀጽ 7 <u>**ቀጠሮ አለማብዛት**</u>

ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ ሁሉ በተቻለ መፍጥነት መቁረጥ አለበት። ስለዚህም በቂ ባልሆነ ምክንያት እንዲጓተት ማድረግ የለበትም።

አንቀጽ 8 <u>**በአሰራሩ የፍርድ ቤቱን ክብር መጠበቅ**</u>

ዳኛ በማናቸውም ጊዜ በአሰራሩና በችሎት አመራሩ የፍርድ ቤቱን ክብር መጠበቅ አለበት።

አንቀጽ 9 <u>ከስራ ባልደረቦቹ ጋር ተግባብቶ መስራት</u>

ዳኛ አብረውት ከሚያስችሉት ዳኞች እና ከሌሎች የስራ ባልደረቦቹ ጋር ተግባብቶ ተባብሮና ተከባብሮ መስራት አለበት።

አንቀጽ 10 <u>በትእግስት ማዳመጥና ነገር ማስጨረስ</u>

1. ዳኛ በችሎት በስርአት የሚነጋገሩትን ጠበቆችና ተከራካሪዎች ሁሉ በትእግስት ማዳመጥና ለጉዳዩ አግባብ ያለው ክርክራቸውን ማስጨረስ አለበት።
2. የባለጉዳዮችን ሰብእና መብታቸውንና ክብራቸውን መጠበቅ ይኖርበታል።

አንቀጽ 11 <u>ተከራካሪዎችን መቆጣጠር</u>

ተከራካሪዎች ተገቢ ያልሆነ ጠባይ ሲያሳዩ ወይም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ሲፈጽሙ ወይም ሳይዘጋጁ ሲቀርቡና ያልረባ ምክንያት እየፈጠሩ ነገር እንዳይቆረጥ ለማድረግ ሲሞክሩ ዳኛው አጥፊዎችን በአግባቡ መገሰጽና ማረም አለበት። አስፈላጊ ሲሆን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት።

አንቀጽ 12 <u>ፍርድ አሰጣጥ</u>

ዳኛ የፍርድ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ በስነስርአት ህጎቹ በተደነገገው መሰረት የነገሩን ጭብጥ የማስረጃውንና የክርክሩን ሁኔታ በመግለጽ አግባብ ያለውን ህግ ጠቅሶ ምክንያቱን በማብራራት መጻፍ አለበት፡፡

አንቀጽ 13 <u>የጥፋተኝነትና የቅጣት አወሳሰን</u>

1. ዳኛ በወንጀል ጉዳይ የጥፋተኝነት ውሳኔ በሚጥበት ጊዜ ተከሳሹ በተከሰሰበት አንቀጽ ፈጸመ የተባለውን የወንጀል ድርጊት፣ ድርጊቱን ለመፈጸም የቀረበውን ማስረጃና የተከሳሹን መከላከያ በብርቱ ጥንቃቄ መመዘን አለበት፡፡
2. ዳኛ የቅጣት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ቅጣቱን በዘፈቀደ ሳይሆን ተከሳሹ ወንጀሉን የፈጸመበትን ሁኔታ፣ ስለቅጣት አላማዎችና አወሳሰን፣ እንዲሁም ስለቅጣት ማክበድና ማቅለል በወንጀለኛ መቅጫ ህግ የተደነገጉት መርሆዎች በጥንቃቄ በመመዘን ለተከሳሹ ጥፋት ተገቢ የሆነውን ቅጣት መወሰን አለበት፡፡

አንቀጽ 14 <u>በሀሳብ የመለየት ሁኔታ</u>

ዳኛ በሀሳብ መለየት መብቱ ቢሆንም የተፋጠነ ፍትህ ለመስጠት እንዲያስችል የልዩነት ሀሳቡን ያለመዘግየት ማስቀመጥ አለበት፡፡ በሃሳብ ተለይቶ በሚጽፈውም አስተያየት ስለጉዳዩ ከመተቸት አልፎ የስራ ጓደኞቹን የሌሎች ግለሰቦችንም ሆነ የህብረተሰብ ክፍሎችን ስሜትም ሆነ ክብር ያለአግባብ የሚነካ አስተያየት መሰንዘር የለበትም፡፡

አንቀጽ 15 <u>የችሎት ሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም መቆጣጠር</u>

የችሎት ሰራተኞችን ስነስርአት እንዳያጓድሉ፣ በስራቸው ላይ ቸልተኝነት እንዳያሳዩ ወይም ስራቸውን ለግል ፍላጎት መጠቀሚያ እንዳያውሉ ዳኛው መቆጣጠርና ተገቢውን ምክርና ተግሳጽ መስጠት ይገባዋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አለበት፡፡

ዳኛ የዳኝነቱን ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ ከንቱ ውዳሴን ሳይሻ በስሜትም ሳይመራ ያላንዳች ፍርሀትና ስጋት በህግ መስራት አለበት፡፡

አንቀጽ 21. <u>የፍርድ ቤት ሰራተኞችን ስነምግባር መቆጣጠር</u>

ዳኛ በፍርድ ቤቱ ሰራተኞቹና በራሱ መካከል መናናቅን የሚፈጥሩ ግንኙነቶችን ከመመስረት መታቀብ አለበት፡፡ እንዲሁም ሰራተኞቹ የፍርድ ቤቱን ክብር እንዲጠብቁና ለባለጉዳዮች ለምስክሮችና ለተገቢ ጉዳይ ወይም አላማ ወደፍርድ ቤቱ ለሚመጡ ሰዎች ሁሉ ትህትና እንዲያሳዩ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

አንቀጽ 22. <u>የስራ ሰአትን ማክበር</u>

ዳኛ የስራ ሰአትን በማክበር ለሌሎች አርአያ መሆን ስለሚገባው በቂ ምክንያት ሳይኖረው ወይም ፍቃድ ሳይቀበል ከስራ ገበታው መለየት የለበትም፡፡

አንቀጽ 23. <u>በውሳኔ ያላለቁ ጉዳዮችን ምስጢራዊ ጠባይ መጠበቅ</u>

ዳኛ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አብረውት ከሚያስችሉት ዳኞች በስተቀር በዝርዝር ጉዳይ ላይ ከማንኛውም ሌላ ሰው ጋር በግል መወያየት ወይም በማናቸውም መገናኛ ብዙሀን መግለጫ ወይም አስተያየት መስጠት የለበትም፡፡

አንቀጽ 24. <u>ከችሎት ስለመነሳት</u>

1. ዳኛ አንድን ጉዳይ እንዳያይ በህግ የተከለከለ ከሆነ ጉዳዩን ማየት የማይገባው መሆኑን እንዳወቀ መቃወሚያ እስኪቀርብበት ድረስ ሳይጠብቅ ምክንያቱን በሚገባ ገልጾ ከችሎት መነሳት አለበት፡፡
2. ዳኛ ያለበቂ ምክንያት የቀረበለትን ጉዳይ አላይም ማለት የለበትም፡፡

አንቀጽ 25<u>. መደለያ አለመቀበል</u>

ለዳኝነት በቀረበ ወይም በሚቀርብ ወይም ለዳኝነት ቀርቦ በተወሰነ ጉዳይ ምክንያት ዳኛ ጉቦ መደለያ ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከባለጉዳይ ወይም ከሌላ ማንኛውም ሰው ላይ መቀበል የለበትም፡፡

አንቀጽ 26. <u>በአማላጅ አለመስራት</u>

ዳኛ በአማላጅ መስራት ወይም እራሱ አማላጅ ሆኖ መቅረብ የለበትም፡፡

አንቀጽ 27. <u>ስልጣንን ለግል ጥቅም አለማዋል</u>

ዳኛ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ስልጣኑንና ክብሩን መሳሪያ ማድረግ የለበትም፡፡

አንቀጽ 28. <u>የዳኝነትን ስራ ከግል ጥቅም ጋር አለማጋጨት</u>

ዳኛ ከዳኝነት ተግባር ክብሩ ጋር የሚጋጭ ወይም የሚቃረን ስራ መስራት አይገባውም፡፡

<u>አባሪ 2</u>

<u>የአቃቤ ህግ የስነምግባር መርሆዎችን በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 44 /1991 የፌዴራል አቃቤያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተወሰዱ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች</u>

አንቀጽ 4

ማንኛውም አቃቤ ህግ ሆኖ የሚሾም

ሀ. በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ

ለ. ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት ታማኝ የሆነ

ሐ. ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በህግ ወይም በዲፕሎም የተመረቀ

መ. በታታሪነቱ በታማኝነቱ በፍትሀዊነቱና በስነምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ እና

ሠ. አድሜው 18 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ

10 <u>ስለአቃቤ ህግ ተጠሪነት</u>

1. አቃቤያነ ህግ ተጠሪነታቸው ለሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ አቃቤ ህግ ከእርሱ ለሚቀጥለው የበላይ ሀላፊ አቃቤ ህግ ተጠሪ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 11 ቃለመሀላ

‹እኔ --------- ለሀገሬ ታማኝ በመሆን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስትንና ሌሎች ህጎችን ላክብርና ላስከበር በፌዴራሉ መንግስት የወጡና ወደፊት የሚወጡ ህጎችን በማስፈጸም የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ልሰራ የስራ ድርሻዬን ህግ በሚደነግገው መሰረት በመፈጸም የሰዎችን ክብርና ሰብአዊ መብት ላክብርና ላስጠብቅ የግል ጥቅም ሳልፈልግ ማንንም በመውደድ በመጥላት ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት አድልዎ ሳላደርግ ማንኛውንም አይነት ተጽእኖ ሳልፈራ በሃቀኝነት በቅንነትና በትጋት ሀላፊነቴን ለመወጣት ቃል እገባለሁ›

አንቀጽ 16 ከመደበኛ የስራ ሰአት በላይ መስራት

1. ስራው የሚመለከተው የበላይ ሀላፊ በአዘዘ ጊዜ ማንኛውም አቃቤ ህግ ከመደበኛው የስራ ሰአት በላይ መስራት ግዴታው ነው፡፡

ስለአቃቤያነ ህግ ግዴታ

አንቀጽ 61 ስለታማኝነት

ማንኛውም አቃቤ ህግ መላ ጉልበቱንና ችሎታውን በታማኝነት ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት ጥቅም ማዋል አለበት፡፡

አንቀጽ 62 ስለእያንዳንዱ አቃቤ ህግ ጠባይ

1. ማንኛውም አቃቤ ህግ የህዝብን አክብሮትና እምነት እንዲያገኝ በመስሪያ ቤቱም ሆነ ከመስሪያ ቤቱ ውጭ በማናቸውም ጊዜ መልካም ጠባይና ስነምግባር እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡
2. በማንኛውም ጊዜ የሙያውን ክብር ለማስጠበቅ የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

አንቀጽ 63. <u>ስለታዛዥነት</u>

1. ማንኛውም አቃቤ ህግ ስራውን ባለው ከፍተኛ እውቀትና ችሎታ መፈጸም አለበት፡፡ የተመደበበትን መደበኛ ስራና ሌላውንም ተመሳሳይ ስራ መፈጸም ግዴታው ነው፡፡
2. አቃቤ ህጉ ከበላይ ሀላፊው የሚሰጠው ትእዛዝ በግልጽ ከህግ ውጭ ካልሆነ በቀር እንደትእዛዙ መፈጸም አለበት፡፡ በማንኛውም አኳኋን የበላይ አቃቤ ህግ ለሚሰጠው ትእዛዝ ህጋዊነት ሀላፊ ነው፡፡

አንቀጽ 64. <u>አቃቤ ህግ ከህዝብ ጋር ስላለው ግንኙነት</u>

1. አቃቤ ህግ የሚፈጽማቸው ተግባሮች በጠቅላለው የመላውን ህዝብ ጥቅም የሚመለከቱ መሆናቸውን ምን ጊዜም መዘንጋት የለበትም፡፡
2. አቃቤ ህግ የሰዎችን ሰብአዊ መብትና ክብር መንካት የለበትም፡፡

አንቀጽ 65 <u>ምስጢር ስለመጠበቅ</u>

ማንኛውም አቃቤ ህግ

1. መረጃው ተራ ወይም በህዝብ ዘንድ የታወቀ ካልሆነ ወይም መደበኛ ስራውን በህጋዊ መንገድ ለመፈጸም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር በስራው አጋጣሚ ወይም ምክንያት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘውን መረጃ ለማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም፡፡
2. ስልጣን ባለው ሀላፊ በአግባቡ ካልታዘዘ በቀር በአሰራር ምስጢር የተባሉትን መረጃዎች ቃለጉባኤዎች የስራ እቅዶችና እነዚህን የመሳሰሉ ምስጢራዊ ጉዳዮች ሁሉ በስራው ላይ ሆነ ከስራ ውጪ ጉዳዩን እንዲያውቀው በደንቡ ለተፈቀደደለት ሰው ካልሆነ በቀር ለሌላ ማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም፡፡

አንቀጽ 66 <u>ገንዘብ ስለመበደር</u>

1. አዘውትሮ ገንዘብ መበደር ክልክል ነው፡፡
2. አቃቤ ህግ በስራው ምክንያት ከሚያጋጥመው ማናቸውም ሰው ገንዘብ መበደር ወይም ለመበደር መሞከር ፍጹም ክልክል ነው፡፡

አንቀጽ 67 <u>ስለስጦታዎች</u>

ማንኛውም አቃቤ ህግ ከስራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስለሰጠው ወይም ወደፊት ስለሚሰጠው አገልግሎት ከማናቸውም ሰው ማናቸውም አይነት ስጦታ ወይም ዋጋ መጠየቅ ወይም መቀበል የለበትም፡፡

አንቀጽ 68 <u>በመንግስት ስራና በግል ጉዳዮች ወይም ጥቅሞች መካከል ስለሚፈጠር ግጭት</u>

1. ማናቸውም አቃቤ ህግ የራሱ የዘመዶቹ ወይም የወዳጆቹ የግል ጉዳይ ወይም ጥቅም ከስራው ወይም በስራው ምክንያት ከያዘው የህዝብ ወይም የግለሰብ ጉዳይ ጋር የሚጋጭ ሆኖ ሲገኝ ይህንን ችግር ለበላይ ሀላፊው ወዲያውኑ በማሳወቅ ጉዳዩ በሌላ አቃቤ ህግ እንዲታይ ማመልከት አለበት፡፡
2. ጉዳዩ የቀረበለት የበላይ አቃቤ ህግም አስፈላጊ የመሰለውን ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

አንቀጽ 69 <u>ስለግል ደብዳቤዎች</u>

1. አቃቤያነ ህግ በመስሪያ ቤቱ አድራሻ የግል ደብዳቤ ሊጽፉ ወይም ከሌላ ሊጻፍላቸው ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ የሚያስፈልገውን የመላላክ ወጪ ጉዳዩ የሚመለከተው አቃቤ ህግ መክፈል አለበት፡፡
2. በመስሪያ ቤቱ አድራሻ የተላከ የማንኛውም አቃቤ ህግ ደብዳቤ ጥቅል ወይም እቃ ቢጠፋ መስሪያ ቤቱ በሀላፊነት አይጠየቅም፡፡

አንቀጽ 70 <u>በመስሪያ ቤቱ መገልገያዎች ስለመጠቀም</u>

አቃቤያነ ህግ ስራቸውን በሚገባ ለመፈጸም ያህል ብቻ በመስሪያቤቱ ልዩ ልዩ መገልገያዎች መጠቀም ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 71. <u>ለሌሎች መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ስለመስራት</u>

1. ማንኛውም አቃቤ ህግ

ሀ. በመደበኛ የስራ ሰአት መላ ጉልበቱን ችሎታውንና አሳቡን በደመወዝ በተመደበበት የመስሪያ ቤቱ ስራ ላይ ማዋል አለበት፡፡ ሆኖም አቃቤ ህጉ በአግባቡ ሲታዘዝ ለሌላ መንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት መስራት አለበት፡፡

ለ. ለመስሪያ ቤቱ የሚያበረክተውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም ለተሰጠው ስራና ሀላፊነት ተቃራኒ የሆነ ወይም ከስራውና ከሀላፊነቱ ወይም ከሙያ ስነምግባር ጋር የማይጣጣም ማናቸውንም የውጭ ስራ ሊሰራ አይችልም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አቃቤ ህግ የውጭ ስራ ለመስራት በቅድሚያ የሚኒስትሩን ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

አንቀጽ 75 <u>የዲሲፕሊን ጥፋቶች</u>

1. የሚከተሉት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

ሀ. ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ

ለ. ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በአማላጅ መስራት

ሐ. ራስን ወይም ሶስተኛ ወገንን ለመጥቀም በጽሁፍ የሰፈረውን መረጃ ሆን ብሎ ወደሀሰተኝነት መለወጥ

መ. ከስራ ጋር ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ገንዘብ መበደር

ሠ. አግባብ ያለውን መረጃ ወይም ፍሬነገር ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ለሚመለከተው ባለማሳወቅ ወይም በመደበቅ ውሳኔውን የሚያዛባ ሁኔታ መፍጠር

ረ. ያለበቂ ምክንያት ስራን በማዘግየት ባለጉዳይን ማጉላላት

ሰ. አእምሮን በሚያደነዝዝ ወይም ሱስ በሚያሲዝ ህገወጥ እጽ መጠቀም

ሸ. ሰክሮ በስራ ላይ መገኘት ወይም በአደባባይ በመታየት የሙያውን ስነምግባርና የመስሪያ ቤቱን ክብር ማጉደፍ

ቀ. ያለበቂ ምክንያት ወይም ያለፈቃድ አዘውትሮ ከስራ መቅረት

በ. በስራ ቦታ ላይ ለሞራልና ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም

ቸ. ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት በመስሪያ ቤቱ ንብረት ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ

ኀ. ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ከባድ ጥፋቶች

ነ. በጽሁፍ ወይም በቃል ከመስሪያ ቤቱ ወይም ከበላይ ሀላፊው የተሰጠውን ግልጽና ህጋዊ ትእዛዝ አለመቀበል ወይም ተግባራዊ አለማድረግ

2. የሚከተሉት ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

ሀ. በስራው ላይ ተገቢ ጥረትና ትጋት አለማሳየት

ለ. ከስራ ባልደረቦች ጋር በመግባባት ተባብሮ መስራት ባለመቻል በስራ ሂደት ላይ እንቅፋት መሆን ወይም

ሐ. አዘውትሮ መበደር

መ. ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ቀላል ጥፋቶችን መፈጸም